# አዲስ ዘመን

ኢፕድ

ሰኞ 82ኛ ዓመት ቁጥር 107 ታኅሣሥ 17 ቀን 2015 ዓ.ም ዋጋ 10.00 ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!










# "የተፈጥሮ ፀጋን በመጠቀም የሌማት ትሩፋትን ውጤታማ ማድረግ አለብን"

- አቶ ደመቀ መኮንን

**በጋዜጣው ሪፖርተር**

አዲስ አበባ፡- የኢትዮጵያ የተፈጥሮ ፀጋ በመጠቀም የሌማት ትሩፋትን ስራዎች ይበልጥ ውጤታማ ለማድረግ ጥረት ማድረግ አለብን ሲሉ ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትር እና የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር አቶ ደመቀ መኮንን ጥሪ አቀረቡ፡፡

በደቡብ ክልል የወተት፣ የዶሮ፣ የስጋና የማር ምርት ማሻሻያ ማስተዋወቂያ መርሐ ግብር በጉራጌ ዞን መስቃን ወረዳ ተካሂዷል፡፡

በሌማት ትሩፋት ክልሉን በቅርበት እንዲደግፉ የተመረጡት ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትርና የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር አቶ ደመቀ መኮንን በመድረኩ ላይ መልዕክት አስተላልፈዋል፡፡

በመልዕክታቸውም ፤ በአርባ ምንጭ ከተማ የተጀመረው ሀገራዊ መርሐ ግብር በተለያዩ አካባቢዎች በማስተዋወቅ ተግባራዊ እንዲሆን እየሰራን እንገኛለን ብለዋል፡፡

አክለውም "የሌማት ትሩፋት" ትርጉም ቤቱ ሙሉ ይሁን ማለት እንደሆነ አንስተው ፥ ይህም ለኢትዮጵያ ሕዝብ አዲስ አይደለም በባህላዊ ምርቃቱ ያውቀዋልም ነው ያሉት ።

በተመጣጠነ ምግብ ጤናው የተጠበቀ ትውልድን ማፍራት ይገባል ያሉት ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትሩ ፥ በአካባቢው ያለውን ፀጋ በመጠቀም የሌማት ትሩፋትን

**የተፈጥሮ ፀጋን ወደ ገጽ 4 ዞሯል**








# "ልዩነቶች ለሰብአዊ መብት ጥሰቶች ምክንያት እንዳይሆኑ ችግሮችን በንግግር መፍታት ያስፈልጋል"

- አቶ አምሃ መኮንን
የሕግ ባለሙያ

**ዘላለም ግዛው**

አዲስ አበባ፡- በታሪክ ያለአግባቡ፣ በፖለቲካ አስተሳሰብ ልዩነትን የፈጠሩ ጉዳዮች ለግጭትና ግጭትን ተከትሎ ለሚከሰቱ የሰብአዊ መብት ጥሰቶች ምክንያት እንዳይሆኑ በንግግር መፍታት እንደሚያስፈልግ የሕግ ባለሙያው አቶ አምሃ መኮንን ገለጹ፡፡

**"ልዩነቶች ለሰብአዊ ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል**



ፎቶ - አሸናፊ ጉደታ

# ከሰላም ስምምነቱ ወዲህ በሽረ እንዳስላሴ ከተማ

- የተሻለ የጸጥታ ሁኔታና የግብይት ሥርዓት ተፈጥሯል
- ሰብአዊ ድጋፍ ያለ ገደብ እየገባ ነው

**አዲሱ ገረመው**

ሽረ እንዳስላሴ፡- ከሰላም ስምምነቱ ወዲህ የተሻለ የጸጥታ ሁኔታ መፈጠሩን፣ ሰብአዊ ድጋፍ ያለ ገደብ እየገባ መሆኑን፣ የተረጋጋ የግብይት ሥርዓት መፈጠሩንና መሰረተ ልማቶች ወደ አገልግሎት መመለሳቸውን ሽረ እንዳስላሴ ከተማ ከተማዋ ነዋሪዎች ገለጹ።

የሽረ ከተማ ነዋሪ አቶ ገብረመድህን ገብረክርስቶስ በስፍራው ላሉት የኢፕድ ዘጋቢዎች እንደገለጹት፣ ከጦርነቱ ጋር ተያይዞ ካሁን ቀደም በከተማዋ ከፍተኛ የጸጥታ ችግር ነበር። የፌዴራል መንግሥት አካባቢውን

**ከሰላም ስምምነቱ ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል**






# በኢትዮጵያ ያገኘችው የዲፕሎማሲ ውጤት በህዝብና በመንግስት ጥንካሬ የመጣ ነው

**ውብሸት ሰንደቁ**

አዲስ አበባ፡- በአሁኑ ወቅት ኢትዮጵያ ያገኘችው የዲፕሎማሲ ውጤት በሀገሪቱ መንግሥትና ሕዝብ ጥንካሬ የተገኘ ነው ሲሉ በሲቪል ሰርቪስ ዩኒቨርሲቲ የአስተዳደርና ልማት ኢንስቲትዩት ረዳት ፕሮፌሰር መሐመድ ዓሊ ገለጹ፡፡

በሲቪል ሰርቪስ ዩኒቨርሲቲ የአስተዳደርና ልማት ኢንስቲትዩት ረዳት ፕሮፌሰር መሐመድ ለኢትዮጵያ

**በኢትዮጵያ ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል**







# ‹‹ኢትዮጵያ ለምስራቅ አፍሪካ አገራት የስንዴ ምርት ልታቀርብ ነው››

**-አቶ ኢሳያስ ለማ**

**በግብርና ሚኒስቴር የሰብል ልማት ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር**

**ሰላማዊት ውቤ**

አዲስ አበባ፡- ኢትዮጵያ በዘንድሮው ዓመት ለኬንያ፣ ደቡብ ሱዳን፣ ጅቡቲን ጨምሮ ለሌሎች የምስራቅ አፍሪካ አገራት የስንዴ ምርትን መላክ እንደምትጀምር በግብርና ሚኒስቴር የሰብል ልማት ዳይሬክተር አቶ ኢሳያስ ለማ አስታወቁ።

አቶ ኢሳያስ በተለይም ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ "በአምስት ዓመት ባቀድነው መሰረት በሦስት ዓመታት አገራዊ ፍላጎቱን እናሳካለን ብለን ግብ በመጣል ተነስተናል፡፡ ባለፉት ሦስት ዓመታት የስንዴ ምርት በአርሶ እና ከፊል አርሶ አደሮች እንዲሁም በሰፋፊ እርሻዎች ሲመረት ከነበረበት በመስኖ ወደ መመረት መሸጋገር ተችሏል" ብለዋል፡፡

ኢትዮጵያ የስንዴ ምርትና ምርታማነትን በማሳደግ፤ የእርሻ ቦታዎችን በማስፋፋት፤ አገራዊ የስንዴ ምርት ፍላጎትን ማሳካት ችላለች። በዘንድሮው ዓመት ደግሞ የስንዴ ምርትን ለውጭ ገበያ ለማቅረብ በስፋት እየሰራች እንደምትገኝ ተናግረዋል።

እስከ ባለፈው ዓመት ድረስ ኢትዮጵያ የስንዴ ምርትን ከውጭ ስታስገባ ቆይታለች ያሉት አቶ ኢሳያስ፤ ከውጭ የሚገባውን የስንዴ ምርት በአገር ውስጥ ምርት በመተካት ከውጭ የሚገባውን ምርት ለማስቀረት ባለፉት ሶስት ዓመታት የስንዴ ምርት ላይ ትኩረት አድርጋ ስትሰራ ቆይታለች ነው ያሉት።

ኢትዮጵያ የስንዴ ምርትን በየዓመቱ እያሳደገች መምጣቷን በመጠቆም፤ ባለፈው ምርት ዘመን የበልግ ወቅትን ጨምሮ 625 ሺህ ሄክታር መሬት በስንዴ ሰብል የተሸፈነ ሲሆን ከዚህ ውስጥ በመስኖ ልማት የተመረተው 355 ሺህ ሄክታር እንደነበር ገልጸዋል።

ዘንድሮ ደግሞ አንድ ነጥብ 32 ሚሊዮን ሄክታር በስንዴ ምርት ለመሸፈን እየሰራች መሆኑንም አመልክተዋል። እስከ አሁንም 700 ሺህ ሄክታር ያህል መሬት በስንዴ ሰብል መሸፈኑን ተናግረዋል።

ስንዴን በማምረት ስራው ከሶስት ሚሊዮን በላይ አርሶ አደሮችና ባለሀብቶች ተሳትፈዋል፣ ኦሮሚያ፣ አማራ፣ ሶማሌና አፋር ክልሎች በምርቱ ላይ የጎላ ተሳትፎ አላቸው፡፡ ምርቱ ጥራቱን የጠበቀ እንዲሆን በስፋት ስንዴን ከሚያጠቃው ዋግና ሌሎች ተባዮች መከላከል ላይ በትጋት እየተሰራ ነው፡፡



ምርቱ የምስራቅ አፍሪካ አገራትን በተለይ ጎረቤት አገራትን፤ ኬንያ፣ ደቡብ ሱዳንና ጂቡቲን ለገበያ መዳረሻነት ታሳቢ ተደርጓል፡፡ የምስራቅ አፍሪካ አገራት በሙሉ ስንዴን ከውጭ የሚያስገቡ ናቸው፡፡ በተለይም ለእነዚህ አገራት በዋናነት የስንዴ ምርት ያቀርቡ የነበሩት ሩሲያና ዩክሬን ነበሩ፡፡

በመንግሥትና በሕወሓት መካከል የተደረገው የሰላም ስምምነት በተለይም በጦርነቱ ምክንያት ከምርት ውጪ የነበሩ 100 የሚጠጉ በየክልሉ ያሉ ወረዳዎች ሙሉ በሙሉ ወደ ምርት ተግባር ፊታቸውን እንዲያዞሩ ለማድረግ መልካም አጋጣሚ መፈጠሩን ዳሬክተሩ አስረድተዋል፡፡

የአመራሩ ቁርጠኝነት፤ አርሶ አደሩ በስንዴ ራስን የመቻልና በሚገኘው ገቢም ፈጥኖ ራስን ለመለወጥ ከፍተኛ ፍላጎት በሕብረተሰቡ ውስጥ መኖሩ የስንዴ ምርትን በስፋት ለማምረት ምቹ አጋጣሚ መሆኑን አቶ ኢሳያስ አንስተዋል።

# በዲማ ሕገወጥ የወርቅ ግብይትን ለመከላከል የተደረገው ጥረት ውጤት እያስገኘ ነው

**ስምስም ምንግሥቱ**

አዲስ አበባ፡- በጋምቤላ ክልል ዲማ ወረዳ በሕገወጥ የወርቅ ግብይት መስፋፋት ለመከላከል የተደረገው ጥረት ውጤት እያስገኘ መሆኑን ክልሉ አስታወቀ፡፡

የጋምቤላ ክልል ማዕድን ሀብት ልማት ቢሮ ዋና የሥራ ሂደት አቶ ሙድ ሎንግ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ በሕገወጥ የወርቅ ግብይት ምክንያት ከጋምቤላ ዲማ ወረዳ ወደብሔራዊ ባንክ መግባት የነበረበት የወርቅ መጠን አሽቆልቁሎ ቆይቷል።

ችግሩን ለመፍታት በፌዴራል ማዕድን ሚኒስቴር፣ ከክልል፣ ከዲማ ወረዳ፣ ከፌዴራል ጉሙሩክ፣ ከቱሪዝምና ከፀጥታ ኃይል የተውጣጣ ቡድን በማዋቀር ከሶስት ወራት በፊት ሕገወጥነትን የመከላከል ሥራ እየተከናወነ ይገኛል ብለዋል፡፡

በዚሁ መሠረትም ቁጥጥር በተደረገበት ወቅት በአማካይ ለብሔራዊ ባንክ ይላክ የነበረውን ከአስር ኪሎ ግራም በታች የነበረ የወርቅ መጠን ወደ 18 ኪሎ ግራም ከፍ ማለቱን ገልጸዋል፡፡

ወርቅ አምራቾች ከአገራዊ ጥቅም ይልቅ የራሳቸውን ፍላጎት በማስቀደም የወርቅ ግብይቱን ለጥቁር ገበያ አሳልፈው በመስጠታቸው የተፈጠረ ችግር እንደነበረም ተመልክቷል፡፡

እንደ አቶ ሙድ ገለጻ፤ ከአካባቢው በዓመት ከአንድ መቶ ኪሎ ግራም በላይ ይላክ የነበረ የወርቅ መጠን በሕገወጥ ግብይት መስፋፋት አሽቆልቁሎ ስድስት ኪሎ ግራም ብቻ የተላከበት ሁኔታ ተፈጥሮ ነበር፡፡



በግብረኃይል ቡድኑ ሕገወጦችን ለሕግ እስከ ማቅረብ በደረሰ እርምጃ የተሰራው ሥራ ጊዜያዊ መፍትሄ ማስገኘት የቻለ ሲሆን፣ ግብረኃይል ቡድኑ የተጠቀመበት የቁጥጥርና ክትትል ስልት በዘላቂነትም በመጠቀም ችግሩን ለመፍታት ጥረት ይደረጋል ብለዋል፡፡

በአካባቢው ያለው የወርቅ ሀብት እንደ ሀገርም እንደ ክልልም ከፍተኛ የኢኮኖሚ ፋይዳ ያለው ነው ያሉት አቶ ሙድ፤ በተለይ እንደክልል ለወጣቶች የሥራ እድል ለመፍጠር ትልቅ ተስፋ እንደተጣለበት አስረድተዋል።

ሀብቱን በአግባቡ በማልማት በሀገር ደረጃ የተቀመጠውን አሰራር ተከትሎ ግብይቱን መፈጸም እንደሚገባ ክልሉ ያምናል ሲሉም ገልጸዋል፡፡

ሕጋዊ መሥመርን የተከተለ ግብይት የክልሉንም ገቢ በማሳደግ ከፍ ያለ አስተዋጽኦ እንደሚያበረክትና ገቢ በአግባቡ መሰብሰብ ከተቻለ መሠረተ ልማቶችን ለማስፋፋት እንደሚውልም አስረድተዋል፡፡

በጉዳዩ ላይም ማዕድን ሚኒስቴር ማንኛውም ልዩ አንስተኛ የወርቅ አምራች በእጁ ያለውን ወርቅ ወደ ብሔራዊ ባንክ እንዲያስገባ የጠየቀ ሲሆን፣ በቀጣይ መንግሥት ጥብቅ ቁጥጥር በማድረግ ወርቅ ወደ ቢሄራዊ ባንክ በማያስገቡት ላይ ህጋዊ እርምጃ እንደሚወሰድ ማሳሰቡን በድረገጹ አስነብቧል፡፡

ሚኒስቴሩ በወርቅ ኮንትሮባንድ ዙሪያ የሚታዩ ችግሮችን ለመከላከል አራት ቡድኖችን አደራጅቶ ወርቅ በሚመረትባቸው አካባቢዎች ማሰማራቱንም በድረገጹ አመልክቷል፡፡



ዶክተር ሊያ ታደሰ

# በእናቶች እና ጨቅላ ሕጻናት ሞት ቅነሳ አበረታች ውጤት ተመዝግቧል

**ዳግማዊት አበበ**

አዲስ አበባ፡- የጤና ባለሙያዎችን ስልጠና በማስፋት እና አገልግሎት አሰጣጡን በማዘመን በእናቶች እና ሕጻናት ሞት ቅነሳ ላይ አበረታች ውጤት መመዝገቡን የጤና ሚኒስቴር አስታወቀ።

የጤና ሚኒስትር ዶክተር ሊያ ታደሰ እንደገለጹት፤ የእናቶች እና የጨቅላ ሕጻናት ሞት ለመቀነስ ባለፉት ዓመታት የጤና ባለሙያዎች ስልጠና በማስፋፋትና አገልግሎት አሰጣጡን በማዘመን ረገድ ከክልል ጤና ቢሮዎች ጋር በቅንጅት በርካታ ሥራዎች ተሰርቷል። በተሰራው ሥራም አበረታች ውጤት ተመዝግቧል።

ኢትዮጵያ የመጀመሪያ ደረጃ የጤና አገልግሎት ሽፋን መቶ በመቶ ለማድረስ ማቀዷን የገለጹት ሚኒስትሯ፤ ከአምስት ዓመት በታች ለሆኑ ሕጻናት የክትባት ሽፋን መቶ በመቶ ለማድረስም መታቀዱንም አክለው ገልጸዋል።

በኢትዮጵያ የጤናውን ዘርፍ እቅድ ለማሳካት ጠንካራና ፍትሃዊ የጤና ሥርዓትን ለመገንባት የጋራ ጥረትና ተጨባጭ እርምጃ ያስፈልጋል ያሉት ዶክተር ሊያ፤ ለዚህም ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ የተለያዩ ፕሮግራሞችን ቀርጾ ተግበራዊነታቸው ከባለድርሻ እና አጋር አካላት ጋር በትብብር እየሰራ እንደሚገኝና እንደሀገር ሁሉን አቀፍ፣ ፍትሃዊ እና ጥራቱን የጠበቀ የጤና አገልግሎትን ለማረጋገጥ ዘርፈ ብዙ የትብብር ስራዎች ይበልጥ መጠናከር አለባቸው ብለዋል።

የሴቶችና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር ተወካይ ዶ/ር ደበበ ባሩድ በበኩላቸው፣ በየትኛውም ቦታና ሁኔታ ላይ የሚገኝ ማንኛውም ሰው ገንዘብ ስጋት ሳይሆንበት መሰረታዊ የጤና አገልግሎት ያለምንም እክል ማግኘት መቻል አለበት ካሉ በኋላ ይህንን እውን ማድረግ ለአገር ሁለንተናዊ ዕድገት ወሳኝ ነው ብለዋል።

ለስኬታማነቱም ሚኒስቴር መስሪያ ቤታቸው ከጤና ሚኒስቴር እና ከአጋር አካላት ጋር በመሆን የተለያዩ ሥራዎችን እያከናወነ መሆኑንም ጠቁመዋል።

ጥናቱን የጤና ሚኒስቴር ከኢትዮጵያ ህብረተሰብ ጤና ኢንስቲትዩት እና ከዓለም አቀፍ ካውንት ዳውን 2030 የጥናት ቡድን ጋር በመተባበር ያጠናው ሲሆን በሪፖርቱ የእናቶች እና ጨቅላ ሕጻናት ሞት ቅነሳ በፈረንጆቹ ከ1990 እስከ 2019 እንዲሁም ከ2016 እስከ 2020 የጤና ትራንስፎርሜሽን እቅድ አፈጻጸም የጥናት እና ምርምር ግኝቶች የሚያብራራ ነው። በጥናቱም በኢትዮጵያ የጤና ስርዓት ባለፉት አስርት ዓመታት ከፍተኛ ለውጥ ማምጣቱ ተገልጿል።

የኢትዮጵያ የ2030 ዕቅዶች ከ100 ሺህ ሰዎች ውስጥ 140 እና ከዚያ በታች የእናቶች ሞት ምጣኔ እንዲቀንስ ማድረግ፣ ከሚወለዱ ህፃናት ከ1ሺህ ውስጥ 12 የሚሆነውን የአራስ ሞት መጠን መቀነስ፣ እናቶች በሰለጠነ የጤና ባለሙያዎች የሚወልዱበትን መጠን 95 በመቶ ማሳደግ መሆኑን ሪፖርቱ ያሳያል።

የጤና ሚኒስቴር ባለፉት 30 ዓመታት የእናቶች እና ጨቅላ ሕጻናት ምጣኔ ቅናሽ ማሳየቱን የሚገለጽ ጥናታዊ ሪፖርት በራሳቸው የትስስር ገጽ አስነብበዋል።

# የጎዳና ሕጻናት የአደንዛዥ “ማስቲሽ” አጠቃቀምና የጤና ችግሮቹ

**መክሊት ወንድወሰን**

አዲስ አበባ፡- የጎዳና ሕይወት በምርጫ የሚገባበት ኑሮ ሳይሆን አማራጭ ሲጠፋ የግዴታ ምርጫ የሚሆን ነው። የጎዳና ላይ ኑሮ በውስብስብ ፈተና የታጀበ ሲሆን ችግሩ ለሕጻናት፣ ለሴቶችና ለአቅመ ደካሞች ግን በእጅጉ የከፋ ነው። የጎዳና ሕይወት በመጠኑ ይበላለጥ እንጂ በየትኛውም አገር የሚስተዋል ክስተት ቢሆንም በታዳጊ አገራት ይብሳል። አሁን አሁን በአገራችንም በተለያዩ ምክንያቶች ወደ ጎዳና መውጣት የተለመደ ክስተት እየሆነ መጥቷል።

በተለይ በአዲስ አበባ ጎዳና ላይ የእለት ተዕለት እንቅስቃሴ ውስጥ ወላጅ እና አሳዳጊ ያጡ ሕጻናትን በየጎዳናው ሲንከራተት ማየት መደበኛ ሆኗል። የጎዳና ሕጻናት፣ የክረምቱ ዶፍ፣ የበጋው አሩር ፣ረሃብና ችግር እየተፈራረቀባቸው አንጀታቸው ታጥፎ፤ ከንፈራቸው ደርቆ ባጭሩ ሰውነታቸዉ ተፈጥሯዊ ይዘቱን ለቆ ማየት እንደ ሰው በጣም ያሳዝናል። የወቅቶች መቀያየር ተፈጥሯዊ ሂደት ቢሆን ለልጆቹ እንደየሁኔታው ምጥና ጭንቀት ይዞ ይመጣል። ያው ያለው አማራጭ መቻል ብቻ ነው።

የጎዳና ኑሮ በብዙ መልኩ በሕጻንነት እድሜ ይዞ የሚመጣው ቀሪው ሕይወታቸውን የሚያበላሽ ከመሆኑም በዘለለ ወዳልተፈለገ የሕይወት አቅጣጫ የሚወስድ መሆኑን የልጆቹ ሕይወት ራሱ ምስክር ነው። ልጆቹ በልጅነት እድሜ ስለሚያስቡ የጎዳና ላይ ኑሮን ያልተገደበ ነጻነት ብሎ ሲናገሩ ይደመጣሉ።

ምክንያቱም ሱስን ጨምሮ ወዳልተፈለገው አስከፊው የሕይወት ጎዳና ለመምራትም ለጊዜው ከልካይ ወይም የሚቆጣጠራቸው አካል የላቸውም። ከልካይ ብቻ ሳይሆን ለእለት ጉርሳቸው፣ ስለሚለብሱት ልብስ፣ ሲታመሙ ወደ ህክምና የሚወስዳቸው፣ በደል ሲደርስባቸው አለኝ የሚሉት ደራሽ ወገንም የላቸውም።

ልጆቹ ተስፋን የሚያደርጉት አንዱ ፈጣሪያቸው ሌላው በሰብዓዊነትና በፈርሃ እግዚአብሔር እጃቸውን የሚዘረጉላቸው ደጋግ ዜጎችን ነው። ያም ሆኖ በለስ ካልቀናቸው ጦማቸውን ማደር ተገደው የሚወስኑት ሌላኛው አማራጫቸው ነው።

በመሃል ከተማዋ ሳይቀር ፊታቸው ገርጥቶ አንጀታቸውን መንገድ ዳር የሚቀመጡ አሊያም እጃቸውን ወደ ሰው የሚዘረጉ ሕጻንነታቸውን ቦርቀው ያልጨረሱ ሕጻናት ማየት ከአንጀት ይሰማል። በተለይ በአሁኑ ጊዜ ኑሮ ጣራ በነካ ሰዓት ሽርፍራፊ ሳንቲሞች ቢያገኙ እንኳ በሕይወታቸው ላይ ለውጥ ያመጣል ብሎ ማሰብ ይከብዳል።

ለዚያ ነው ብዙ የጎዳና ልጆች ረሃብና ብርዱን



**የጎዳና ላይ ህጻናት**

ለመታገስ በጤናቸው ላይ ወስነው “ማስቲሽ” የሚባል ለጫማ ማጣበቂያ የሚውል መርዛማ ኬሚካል የሚጠቀሙት። በእርግጥ የጎዳና ሕይወት በራሱ ለተለያዩ ሱሶች ተጋላጭ የሚያደርግ መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ ለአሁን ግን የማስቲሽ ጤና ቀውሶች ላይ ለማተኮር ወደድን።

“ማስቲሽ”ን ለመጠቀም ያስገደዳቸው ሁኔታና በጤናቸው ላይ ያመጣውን ችግር በተጨባጭ ያመጣውን ችግር ለመረዳት ጥያቄያችንን ይዘን ወደ ጎዳና ተዳዳሪ ልጆች አመራን።

“ከዚህ በፊት በሩጫ ጎበዝ ነበርኩ፤ ጎሮሮዬን ጤና ነበር፤ የመተንፈስ ችግርም አልነበረብኝም። ነገር ግን ሌሊት ሌሊት ብርድ ስለሚያቸግረኝ ጓደኞቼ ምክር ማስቲሽ መጠቀም ስጀምር እንግዳ ነገር በሕይወቴ ማየት ጀመርኩ” ትላለች የሕጻን ቃልኪዳን አበበ (ስሟ የተቀየረ)።

ሕጻን ቃልኪዳን ማሽቲሹን መጠቀም በመጀመሯ የብርዱ ችግር ቢቃለልላትም ለጎሮሮ መጣበቅ እና ለአተነፋፈስ ችግር ተጋላጭ ሆናለች። አሁን ካጋጠማት እንግዳ ከሆኑት በሽታዎች ለመታደግ ማስቲሽ ከመጠቀም ለመላቀቅ ትግል ትጀምራለች። ነገር ግን ከችግሩም በቀላል ለመላቀቅ እንዳለተቻላት ትገልጻለች።

ሕጻን ኦብሳ ባይሳ (ስሙ የተቀየረ) ሌላኛው ጎዳና ተዳዳሪ ሲሆን ማስቲሽ መጠቀም ከጀመረ ዓመታት ማስቆጠሩን ይናገራል። ማስቲሽ ለጤና ጥሩ እንዳልሆነ በራሱ ላይ በማየት ለመተው ሞክሮ ነበር። ነገር ግን ጭንቅላቱን ለደቂቃ እንኳ መሸከም እንዳቃተውና ከባድ የቀን እንቅልፍ እንደጣለበት አጫውቶናል።

በዚህ ምክንያት በቀን በልመና የሚያገኘው ገንዘብ ከ 60-120 ለማስቲሽ ግዥ ለመጠቀም ይገደዳል። ማስቲሹን በምስብበት ወቅት (እሱ ሰንጦዝ ይላል) የተለያዩ ዓይነት ቀለማትና አስፈሪ ነገሮች ያያል። መጣላት መደባደብ ያስከጅላል። የድፍረት ጥግ ይመጣል፤ ብርድም አሳሳቢ አይሆንም ይላል።

ከማስቲሽ ብሎም ከጎዳና ኑሮ ለመላቀቅ ጽኑ ፍላጎት እንዳላቸው ነገሩን። መልካም ሰዎችን ካገኙ ከመማር ወደ ኋላ አይሉም። በተላይ ባህሪያቸውን መረዳት ከሚችሉት ሰዎች ጋር የመኖር ፍላጎት አላቸው። ሰዎች ቢያቀርቡአቸው እና ጓደኛ ቢያደርጉአቸው ደስ ይላቸዋል።

ዶ/ር ዮናስ ላቀውን የአዕምሮ ህክምና ስፔሻሊስት እና በዚሁ ዙሪያ የመጽሐፍ የጻፉ ባለሙያ ናቸው። ወደሚኖሩበት ስልክ በመደወል ጉዳዩን አወራናቸው። የዶ/ር ዮናስ፤ “ጎዳና ላይ መኖር መሰረታዊ ከሆኑት ምግብ ልብስ እና መጠለያ በተገቢው እና በበቂ ሁኔታ የማይሟሉበት ነው፤ እነዚህ ነገሮች አለማሟላታቸው በራሱ ከባድ የሆነ ሥነ ልቦናዊ ተጽእኖ የሚያሳድር ነው። በዛው ልክ ጎዳና ላይ ሚኖሩ ልጆች ለተለያዩ ሱሶችና ተላላፊ በሽታዎች ይጋለጣሉ” ሲሉ አስረዱን።

ከዚህ ቀደም በተደረገ ጥናት ጎዳና ላይ ካሉ ሕጻናት መካከል 90 በመቶ የሚሆኑት ቢያንስ አንድ ሱስ እና የአእምሮ ጤና እክል እንዳለባቸውም አክለው ነገሩን። እነዚህ ሕጻናትም ከሱሱ ጋር ተያይዞ የሚፈጽሙት ወንጀሎች እንዳለም አልሸሸጉትም።

ሱስ አምጪ ዕጾች አደንዛዥ እጽ እና አነቃቂ እጽ በመባል በሁለት እንደሚከፈሉ የተናገሩት ዶ/ር ዮናስ፤ አሁን ላይ የጎዳና ተዳዳሪ ልጆች በስፋት የሚወስዱትን ማስቲሽ በአደንዛዥ እጾች መካከል እንደሚመደብ ይናገራሉ።

“ነገር ግን ቁጥራቸው በማስቲሽ ተጠቃሚዎች ልክ ባይሆንም ሰዎች ሌሎች ሱስ አምጪ የሆኑና ለጤና እጅግ ጎጂ የሆኑ እንደ ቀለም ማቅጠኛና ቤንዚን የመሳሰሉትን ይወስዳሉ። ልጆቹ ማስቲሽን የሚያዘወትሩት ከሌሎች አደንዛዥ ዕጾች አኳያ ሲታይ ዋጋው ርካሽ ከመሆኑም ባሻገር የሕግ ተጠያቂነቱም እምብዛም አያስፈራም። ለዚህ ነው ጎዳና ላይ ያለከልካይ የሚሸመተው” ይላሉ ዶ/ር ዮናስ።

በሱስ አንዴ የተጠቃ ሕጻን ሙላው ሰውነቱ በሱሱ ስለሚወረር በቀላሉ ለመላቀቅ አዳጋች መሆኑን የተናገሩት ባለሙያው፤ አንዳንዴ አዕምሯቸውን ለማዘዝና ለመቆጣጠርም እንደሚቸገሩ ያስረዳሉ። ማስቲሹን በሚወስዱ ሰአት ጥሩና ጥሩ ያልሆነን ትክክልና ትክክል ያለሆነን ነገር የሚለየውን የአእምሮ ክፍል ስለሚቆጣጠረው በአጠቃላይ በትክክል ማሰብና የመወሰን ችሎታን ይጎዳል።

ልጆቹ ለማቆም በሚሞክሩበት ሰአት የተለያዩ አካላዊ፤ ስሜታዊ፤ ሥነልቦናዊ ጫናዎችን ያስከትልባቸዋል። ይህንን ጫና መቋቋም ካልቻሉ ተመልሰው ወደ ቀድሞው እሽክርክሪት ይገባሉ።

ስለሆነም ከማስቲሽ ሱስ ለመውጣት ጊዜ ይፈልጋል። በሚተውበት ጊዜ ድብርት ስለሚከሰት ለዛ የሚረዱ መድሃኒቶችን መውሰድና የሚከታተላቸው ሰው እና የአእምሮ ጤና ህክምና ባለሙያ ያስፈልጋል።

እነዚህን ከፍተኛ ቁጥር ያላቸውን ልጆችን ከጎዳና አንስቶ ወደ ተስተካከለ የኑሮ ሁኔታ ለማምጣት ሥራ ስንሰራ የልጆቹ ሁኔታ ፤ ስለሚወስዱት ሱስ አምጪ እጾች ፤ ስሜቶችም ጭምር በደንብ ለይቶና እቅድ ነድፎ ማስቀመጥ ያስፈልጋል።

“ልጆቹን ከጎዳና በዘመቻ አንስተው በታጠረ ግቢ ብቻ ማኖር ውጤት አያመጣም። በተጨማሪም ችግሩን ከስሩ ለማድረቅ ሁሉም ልጆች በየትምህርት ቤቶቻቸው የአቻ ግፊትን መቋቋም የሚያስችል የግንዛቤ ማስጨበጫ መሰጠት አለበት” ሲሉ ዶ/ር ዮናስ ምክራቸውን ለግሰዋል።

# ዩኒየኑ ስንዴ ለውጭ ገበያ ለማቅረብ መዘጋጀቱን ገለጸ

**ፍሬሕይወት አወቀ**

አዲስ አበባ፡- የስንዴ ምርት ለውጭ ገበያ ለማቅረብ መዘጋጀቱን በአማራ ክልል የመርከብ ሁለገብ የገበሬዎች ህብረት ሥራ ማህበር ዩኒየን አስታወቀ፡፡

የመርከብ ሁለገብ የገበሬዎች ህብረት ሥራ ማህበር ዩኒየን ሥራ አስኪያጅ አቶ ጌታቸው እሸቱ በተለይ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ አርሶአደሮች ስንዴን በዓመት ሁለት ጊዜ ማምረት ችለዋል፡፡

ዩኒየኑ በአሁኑ ወቅትም ስድስት መቶ ሺ ኩንታል የሚደርስ የስንዴ ምርት ለመሰብሰብ የተዘጋጀ ሲሆን፤ ምርቱን ከአገር ውስጥ ፍጆታ ባለፈም ወደ ውጭ ገበያ ለማቅረብ የሚያስችል ሥራ እየተከናወነ ነው ብለዋል፡፡

በአገሪቱ የምግብ ዋስትናን ለማረጋገጥ መንግሥት ለስንዴ ምርት ልዩ ትኩረት ሰጥቶ እየሠራ መሆኑን የገለጹት አቶ ጌታቸው፤ በዩኒየኑ ሥር ከሚገኙ 140 መሰረታዊ ማህበራት መካከል 52ቱ በስንዴ ምርት የተሰማሩ መሆናቸውን ገልጸዋል፡፡

በሀገሪቱ የተመረተውን ስንዴ ሰብስቦ መንግሥት ባስቀመጠው አቅጣጫ መሰረት ወደ ውጭ ገበያ ለመላክ የቅድመ ዝግጅት እየተከናወኑ መሆኑን ጠቁመዋል፡፡



ከተሠሩት የቅድመ ዝግጅት ሥራዎች መካከልም የመጋዘን እጥረት እንዳይገጥምም የዩኒየኑን ምርቱ የሚከማችበትን መጋዘን ማዘጋጀት አስረድተዋል።

ከዚህ በተጨማሪም በአካባቢው በሚገኙና በኢንዱስትሪ ፓርኮች፣ በእህል ንግድና በእርሻ ሰብል ውስጥ ተገንብተው አገልግሎት የማይሰጡ መጋዘኖችን ለስንዴ ማከማቻ ዝግጁ መደረጋቸውንም ተናግረዋል፡፡

ዩኒየኑ የፋይናንስ ችግር እንዳይገጥመው ከክልሉ የግብርና ቢሮ እና የህብረት ሥራ ኤጀንሲ ጋራ በመሆን ከፋይናንስ ተቋማት ጋር የገንዘብ ትስስር ፈጥሯል ያሉት አቶ ጌታቸው፤ በዚህም የክልሉ መንግሥት ዋስትና በመሆን ዩኒየኖቹ ገንዘብ እንዲያገኙ የጋራ ስምምነት ላይ መደረሱን ጠቅሰዋል፡፡

ከተያዘው ወር አጋማሽ ጀምሮም የስንዴ ምርት የሚሰበሰብና መንግሥት በሚያወጣው መስፈርት መሰረትም ከአገር ውስጥ ባለፈ ለውጭ ገበያ የሚቀርብ ይሆናል ብለዋል፡፡

ዩኒየኑ የስንዴ ምርትን ወደ ውጭ ገበያ ለማቅረብ ሁለት አማራጮችን እንደሚጠቀም የተናገሩት አቶ ጌታቸው፤ አንደኛው አማራጭ በክልሉ ከሚገኙ እንደ ጥረት ኮርፖሬት ካሉት የልማት ድርጅቶች አማካይነት ስንዴ ወደ ውጭ ገበያ እንደሚቀርብ አስታውቀዋል፡፡

በሌላ አማራጭም ዩኒየኑም በራሱ መንግሥት የሚያቀርባቸውን ገዢዎች መሰረት በማድረግ ስንዴን ለውጭ ገበያ ለመላክ ከብሔራዊ ባንክ መለያ ቁጥር ወስዶ አስፈላጊውን የቅድመ ዝግጅት ሥራ እያከናወነ መሆኑን አመላክተዋል፡፡

በአማራ ክልል የስንዴ ምርትን በመኸርና በበጋ መስኖ በዓመት ሁለት ጊዜ በማምረት ምርትና ምርታማነትን ማሳደግ መቻሉን የጠቀሱት አቶ ጌታቸው፤ ለተግባራዊነቱም የክልሉ የህብረት ሥራ ኤጀንሲና ግብርና ቢሮ የጋራ መድረክ በመፍጠር የተለያዩ ንቅናቄዎችን እያደረጉ መሆናቸውን ተናግረዋል፡፡

በተያያዘም ዩኒየኑ በአካባቢው የሚገኙ አምራች አርሶ አደሮች ያሉበትን የቅድመ ዝግጅት ሥራ በመጎብኘት ግንዛቤ የማስጨበጥ ሥራ እየሠራ እንደሆነም አስረድተዋል፡፡

# የደምበጫ- ፈረስ ቤት የአስፓልት ግንባታ የባከነውን ጊዜ በሚያሻሽል መልኩ እየተሰራ ነው

**ሄለን ወንድምነው**

አዲስ አበባ፡- ለሁለት ዓመታት በተለያዩ ችግሮች ተጓቶ የነበረው የደምበጫ- ፈረስ ቤት የአስፓልት መንገድ ግንባታ የባከነውን ጊዜ በሚያሻሽል መልኩ ስራው እየተከናወነ መሆኑን የአማራ መንገድ ስራዎች ድርጅት አስታወቀ፡፡

የአማራ መንገድ ስራዎች ድርጅት የፕሮጀክት ማናጀር አቶ ክፍሌ ተስፋ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፣ 69 ነጥብ 8 ኪሎ ሜትር የሚረዝመውን የደምበጫ-ፈረስ ቤት የአስፓልት መንገድ ስራ በ2013 ዓ.ም ሲጀመር በሶስት ዓመት እንዲጠናቀቅ ዕቅድ ተይዞለት ነበር፡፡

ይሁንና በተለያዩ ችግሮች በተለይም በኮቪድ-19 ወረርሽኝ፣ በካሳ አተማመን መዘግየት፣ የግንባታ ግብዓት እጥረትና ዋጋ መናርና እንዲሁም በተያያዥ ችግሮች የተነሳ የመንገድ ግንባታው እስከ ጥቅምት ወር 2015 ዓ.ም ድረስ ከ8 በመቶ በላይ አለማለፉን አስታውሰዋል።

ችግሮቹን ለመቀነስ በተከናወነ ስራ በሁለት ወራት የመንገድ ግንባታው የፕሮጀክቱን አፈጻጸም 14 በመቶ ማድረስ ተችሏል። አሁን ላይ የፕሮጀክቱ ግንባታ ላይ የባከነውን ጊዜ በሚያሻሽል መልኩ እየተሰራ መሆኑን ገልጸዋል።

የባለፈውን ዓመት ደካማ ስራ ሊያካክስ በሚችል ሁኔታ የአፈር ሙሌት እና ተያያዥ ስራዎች እየተሰሩ እንደሚገኝ ጠቁመዋል፡፡

በተጨማሪም የመንገድ ግንባታውን በዋናነት እየሰራ የሚገኘው የአማራ መንገድ ስራዎች ድርጅት በስሩ የሚገኙ ተቋራጮችን እየገመገመ የአቅም ውስንነት ያለባቸውን በሌሎች በመተካት ስራውን አጠናክሮ ቀጥሏል ሲሉ ማናጀሩ አስታውቀዋል።

በሰብ ኮንትራክተርነት ይሰሩ የነበሩት የመንቆረር እና መቅደላ ኮንስትራክሽን ድርጅቶች በገቡት ውል መሰረት ባለመስራታቸው፣ ባላቸው የማሽነሪ እና የአቅም ውስንነት ምክንያት ከግንባታ ስራው እንዲወጡ መደረጉንም ተናግረዋል፡፡

እንደ አቶ ክፍሌ ገለጻ፣ የመንገድ ግንባታው አሁን ያለበትን ደረጃ በማየት በተገባው የውል ስምምነት መሰረት በዚህ ዓመት ማጠናቀቅ ባይቻልም በቀጣይ ሁለት ዓመት ውስጥ ግንባታውን ለማጠናቀቅ ጥረት ይደረጋል፡፡

የደምበጫ ዙሪያ ወረዳ ኮሙኒኬሽን ጉዳዮች ጽህፈት ቤት ኃላፊ አቶ ልንገርህ ይታየው በበኩላቸው፣ የፌዴራል፣ የክልል፣ የዞንና የአካባቢው አመራሮች በጋራ በመሆን ስራው ያለበትን ሁኔታ መገምገማቸውን ገልጸዋል።

ስራው በፍጥነት ተጠናክሮ ወደ ስራ መገባት እንዳለበት አቅጣጫ ተቀምጦ ከባለፈው በተሻለ መንገድ በዚህ ዓመት እየተሰራ እንደሚገኝ ገልጸዋል፡፡

በመንገድ ግንባታው ሂደት ያጋጠሙ ችግሮችን ለመፍታት ከፌዴራል እስከ ዞን ባሉ ባለድርሻ አካላት ተገምግሟል፡፡ በግንባታው ላይ የተስተዋሉ ችግሮችን ከአካባቢው አስተዳደር ጋር በመሆን በጋራ ለመፍታት የሚያስችል ስራ እየተከናወነ ይገኛል ብለዋል።

እንደ አቶ ልንገርህ ገለጻ፣ የካሳ አተማመን ላይ ያለውን ችግር እንዲቀረፍ ጥረት ተደርጓል። ህብረተሰቡም ከፍተኛ ኢኮኖሚያዊ ጠቀሜታ ላለው የመንገድ ግንባታ መጠናከር አስፈላጊውን ድጋፍ እንዲያደርግ የተለያዩ የግንዛቤ ማስጨበጫ ስራዎች ተከናውነዋል።

## "ልዩነቶች ለሰብአዊ...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

አቶ አምሃ ለኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ በታሪክ ያልተግባባንባቸው፣ በፖለቲካ አስተሳሰብ የምንለያይባቸው በርካታ ጉዳዮች በመኖራቸው ለግጭትና ግጭትን ተከትሎ ለሚከሰቱ የሰብአዊ ጥሰቶች ምክንያት እንዳይሆኑ ከምንጩ ማድረግ ያስፈልጋል።

ባለፉት ሁለት ዓመታት በሰሜን ኢትዮጵያ ከተደረገው ጦርነትና በተለያዩ አካባቢዎች ካጋጠሙ የጸጥታ መደፍረሶች ጋር ተያይዞ ለሰብአዊ መብት ጥሰቶች ምክንያት የሚሆኑ ጥያቄዎችና የፖለቲካ አስተሳሰቦች ይጠፈራሉ። እነዚህን ችግሮች በየወቅቱ በንግግር መፍታት ያስፈልጋል ሲሉ አቶ አምሃ ገልጸዋል።

መንግሥት የሕግ የማስከበር ስራ መስራት አለበት ያሉት አቶ አምሃ፤ በተለይ ንጹሃን ላይ አስቀድሞ ጉዳቱ እንዳይደርስ መከላከል ያስፈልጋል ብለዋል።

ነገር ግን የአገር ጸጥታንና የሕዝብን ደህንነት በሕግ ማስከበር ብቻ ማሳካት ስለማይቻል ለጸጥታ መደፍረስ የሚሆኑ ምክንያቶችን በመለየት በንግግር መፍታት ዘላቂ መፍትሄ መሆኑንም አመልክተዋል።

የማንኛውም መንግሥት ቀዳሚ ሃላፊነቱ የዜጎችን ደህንነት መጠበቅ እንደመሆኑ ይህንን ለማድረግ የሚያስችሉ አስፈላጊ ርምጃዎች ይኖራሉ። በሕግ ማስከበር ውስጥ ደግሞ ሊፈጠሩ የሚችሉ ችግሮች እንደሚኖሩ ጠቁመዋል።

በግለሰቦችና በሕብረተሰቡ መብቶች ላይ ሊፈጠሩ የሚችሉ ጫናዎች ሲፈጠሩም በተቻለ መጠን ጫናዎቹን ለማስወገድ ካልሆነ ደግሞ በጣም በቀነሰ ሁኔታ ለመተግበር ጠንካራ የሕግ ማስከበር ሥርዓትና ውይይት እንደሚያስፈልግ አመልክተዋል።

እንደርሳቸው ማብራሪያ፤ ዜጎች ላይ የሰብአዊ መብት ጥሰት ተፈጽሞ ሲገኝ ደግሞ አጥፊዎች መቀጣት አለባቸው። ያለምንም ምክንያት በመንግሥት መዋቅር ውስጥም ሆነ ከመንግሥት መዋቅር ውጭ ያሉ ሰዎች የሚቀጡበትና የሚጠየቁበት ሥርዓት መፈጠር አለበት።

የተለያየ የፖለቲካ አስተሳሰብ ባላቸው አካላት መካከል በሚኖር ፍትጊያ ንጹሃን፣ ሴቶች፣ እናቶችና ሕጻናት በቤታቸው ሆነው ጉዳት እየደረሰባቸው ይገኛል። እነዚህ ወገኖች እንባቸው መታበስ ስላለበት ከውይይቱ ባለፈ ጉዳት ለደረሰባቸው ሰዎች ተገቢውን ካሳና መልሶ ግንባታ በሥርዓት መዘርጋት ያስፈልጋል። ወደ ዘላቂ ሰላም የሚያደርሰው የእነዚህ ድምር ውጤት ነው ብለዋል።

በጦርነት ውስጥ የነበረ አገር ወደ ሰላማዊ ሁኔታ ሲገባ በሽግግር ፍትህ መፍትሄ ማምጣት ይችላል። በዚህም ወደ በጦርነት እና በኢ- ዴሞክራሲ ሥርዓት የተፈጸሙ በደሎች፣ የሰብአዊ መብት ጥሰቶች ምላሽ የሚሰጥባቸው መንገዶች ማመቻቸት ይቻላል ሲሉ አስረድተዋል።

ከዚህ ባለፈ አጥፊዎችን በወንጀል ተጠያቂ ማድረግ፣ ካሳ መክፈል እና ይቅርታ መጠየቅና የተለያዩ ርምጃዎችም የሚወሰዱበት አግባብ እንዳለ ጠቁመዋል።

ከአምስት ዓመታት በፊት በዋናነት በግንባር ቀደም በሕወሓት በሚመራው የኢህአዴግ ሥርዓት ውስጥ በነበረበት ወቅት መጠነ ሰፊ የሰብአዊ መብት ጥሰቶች መፈጸማቸውን አስታውሰዋል።

አልፈን አሁን ያለው ሥርዓትም ፈተናዎች ይዞ መምጣቱ እንደተጠበቀ ሆኖ ከዛ በፊት የነበሩ የሰብአዊ መብት ጥሰቶች የተጎዱ የሚካሱበት፣ የጎዱና ጥፋት የፈጸሙ የሚጠየቁበትና በማሕበረሰቡ ውስጥ የተፈጠረው ቅራኔ የሚታከምበትን ሥርዓት የሚዘረጋና ምላሽ የሚሰጥ አሰራር እንደሚያስፈልግ አብራርተዋል።

## የተፈጥሮ ፀጋን በመጠቀም...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

እውን ለማድረግ መረባረብ አለብንም ነው ያሉት፡፡

በጠቅላይ ሚኒስትር ዐቢይ አሕመድ ይፋ የተደረገው የ 'ሌማት ትሩፋት' መርሐ-ግብር በምግብ ሉዓላዊነትን ማስከበር እና ክብርን ከማረጋገጥ ጋር ቁርኝት አለው ተብሏል ።

በመድረኩ የ 'ሌማት ትሩፋት' መርሐ-ግብር ኢትዮጵያ የምግብ ዋስትዋናን እንድታረጋግጥ ማስቻል፤ በተለይም ስጋ፣ እንቁላል፣ ማር እና ወተት ቅንጦት ሳይሆን ትርፍ ምርት ሆነው እንዲገኙ ማድረግን ታሳቢ ያደረገ መሆኑ ተገልጿል።

በመርሐ ግብሩ ከምክትል ጠቅላይ ሚኒስትር እና የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር አቶ ደመቀ መኮንን በተጨማሪ የብልጽግና ፓርቲ ዋና ጽ/ቤት ኃላፊ አቶ አደም ፋራህ ፣የደቡብ ክልል ርዕሰ መስተዳድር አቶ እርስቱ ይርዳው እንዲሁም የፌደራል እና የክልል ከፍተኛ የስራ ኃላፊዎች ተገኝተዋል።

## ከሰላም ስምምነቱ...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

ከተቆጣጠረና የሰላም ስምምነቱ ከተፈጸመ ወዲህ የጸጥታው ሁኔታ በተሻለ ሁኔታ ላይ በመሆኑ ሕዝቡ የሰላም አየር እየተነፈሰ ነው።

አሁን ሰላምን በተግባር አይተናል ያሉት አቶ ገብረመድህን፣ የሰላም አየሩ ለመላው የትግራይ ሕዝብ ተስፋ ሰጪ መሆኑን ተናግረዋል። የሕዝቡ ፍላጐት ሰላሙ ቀጣይነት ያለው እንዲሆን ማስቻል እንደሆነም ጠቁመዋል።

አቶ ገብረመድህን እንደሚሉት፣ ጤና ጣቢያዎች፣ ሆስፒታሎች፣ ባንክ፣ ስልክ፣ ውሃ የመሳሰሉ መሰረተ ልማቶች ወደ አገልግሎት ተመልሰዋል። ሕዝቡ ከፌዴራል መንግሥት ጐን ቆሞ ሰላሙ ቀጣይ ስለሚሆንበት ሁኔታም በነጻነት እየመከረ ይገኛል።

ሕዝቡ ይበጀኛል ብሎ የተቀበለውን ሰላም አንዳንዶች ለመቀልበስ ቢያስቡም፤ ሰላሙ እውን እንዲሆን የትግራይ ሕዝብ ከመቼውም ጊዜ በላይ ቁርጠኛ እንደሆነ አቶ ገብረመድህን አረጋግጠዋል።

ወይዘሮ ግዴይ መዝገበ በበኩላቸው፣ ሰላሙ ከጨለማ ወደ ብርሃን አምጥቶናል። ለሁለት ዓመታት ዘልቆ የቆየው ግጭት በርዶ ሰላም በመምጣቱ ለትግራይ እናቶች፣ አባቶች፣ ወጣቶችና ሕጻናት ብርሃንን የፈነጠቀ ነው ብለዋል።

በአካባቢው የትራንስፖርት ሁኔታ ችግር እንዳለ በመግለጽ፣ መንግሥት አግልግሎቱን የማስጀመር ስራን በትኩረት ሊያከናውን እንደሚገባም ወይዘሮ ግደይ አንስተዋል።

በግጭቱ ወቅት ህክምና ማግኘት አስቻጋሪ እንደነበር፣ የተረጋጋ የግብይት ሥርዓት ባለመኖሩ፣ ጤፍን ጨምሮ ሌሎች ሸቀጣሸቀጦች በእጥፍ ሲሸጡ እንደነበርና ሕዝቡ የፈለገውን ሸምቶ ለመብላት እንደሚቸገር ጠቅሰው፣ አጠቃላይ ሁኔታዎች ጨለማ እንደነበሩ ያስታውሳሉ። "አሁን ያለው ሁኔታ ብርሃን ነው" ሲሉ ነው የገለጹት።

የፌዴራል መንግሥት ሽሬ ከገባ ጀምሮ የተሻለ የጸጥታ ሁኔታ መኖሩን የገለጹት ወይዘሮ ግደይ፤ ከዛ በፊት የተደራጁ ዘራፊዎች ሕዝቡን ያስቸግሩ እንደነበር ጠቅሰዋል። በአሁኑ ወቅት ምንም አስጊ ሁኔታ እንደሌለም ነው የተናገሩት።

በሽረ ከተማ የቀበሌ 03 ቡድን መሪ አቶ መርእድ አድማሱ፤ የኢትዮጵያ መንግሥት በሰላም ስምምነቱ የገባው ቃል አብዛኛው ተፈጻሚ መሆናቸውን ገልጸዋል።

በተለይ የሰብአዊ ድጋፍ ያለምንም ገደብ በከፍተኛ ቁጥር እየገባ እንዳለና የመጠን ጥያቄ ካልሆነ በቀር ለሁሉም ሕብረተሰቡ ተደራሽ መሆኑን ጠቁመዋል።

የሰብአዊ እርዳታው በመግባቱ ሕዝቡን ከረሃብ መታደግ ብቻ ሳይሆን ገበያውም ተረጋግቷል በማለት፣ ለአብነትም 100 ኪሎ ግራም ስንዴ ይሸጥ ከነበረበት ሰባት ሺህ ብር ወደ ሶስት ሺህ ብር ማውረድ እንደተቻለ ገልጸዋል። በተመሳሳይ 100 ኪሎ ግራም ጤፍ ከ12 ሺ ብር በላይ ይሸጥ የነበረ ሲሆን፤ አሁን ላይ በአምስት ሺህ ብር እየተሸጠ መሆኑንና የሰላም ስምምነቱ የአካባቢውን ኢኮኖሚ ከማረጋጋት አኳያ ትልቅ ሚና እንደነበረው አንስተዋል።

ከሁለት ዓመታት በላይ የተዘጉ እንደ ቴሌ ያሉ መሰረተ ልማቶች በፍጥነት ወደ ስራ ገብተው ሕዝቡን ተጠቃሚ ማድረግ እንደቻሉም ተናግረዋል። የመንግሥት ቁርጠኝነት ለሕዝቡ የሰላም ምንጭ መሆኑን በመጥቀስ፣ ቀጣይ ለሚከናወኑ ተግባራት ሕዝቡ በመተባበርና በመደጋገፍ ስሜት ከመንግስት ጐን እንዲቆምም ጠይቀዋል።

## በኢትዮጵያ የሚታየው...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

ፕሬስ ድርጅት እንደገለጹት፤ አንዳንድ ምዕራባውያን ለኢትዮጵያ በነበራቸው የተሳሳተ ግንዛቤ በሀገሪቱ የራሳቸውን አሻንጉሊት መንግሥት ለማስቀመጥ ያላደረጉት ጥረት አልነበረም፡፡

ሆኖም በሕዝብና መንግሥት በአንድነት በሠሩት ሥራ የምዕራባውያኑ ሴራ ሊከሽፍ ችሏል፡፡ ከምንም በላይ ምዕራባውያን በሰብዓዊ መብት ጥሰት እና በሌሎች ሰበቦች ተጠቅመው እጃቸውን ለማስገባት ይጠቀሙበት የነበረው የሰሜኑ የሀገሪቱ ክፍል ጦርነት ኢትዮጵያ በፈለገችው መልክና ልክ ተጠናቋል ሲሉ ገልጸዋል፡፡

ይህም ኢትዮጵያ ካገኘችው ሰላም በተጨማሪ የዲፕሎማሲ ድሎችን እንድትቀዳጅ ዕድል የከፈተ አንዱ ምክንያት ሲሆን የተገኘው የታየው የዲፕሎማሲ እምርታም በኢትዮጵያ ሕዝብና መንግሥት አንድነትና ጥንካሬ የተገኘ ነው ብለዋል፡፡

አሁን ያለው የዲፕሎማሲ ድል ኢትዮጵያ ታግላ በበላይነት ያመጣችው ድል ነው ያሉት ረዳት ፕሮፌሰር መሐመድ፤ የምዕራቡ ዓለም ኢትዮጵያን ለመጣል ያልፈነቀለው ድንጋይ እንዳልነበር ጠቅሰው የኢትዮጵያ መንግሥት እና ሕዝብ በጋራ፣ በትብብርና በአንድነት የተቃጣባቸውን የጠላት ኃይል ጥቃት በመመከታቸው ምክንያት ድል አድርገዋል ሲሉ አስረድተዋል፡፡

አንዳንድ ምዕራባውያን አገራት በባሕሪያቸው ማንም ይሁን ማን በተቻለ አቅም የራሳቸውን ጥቅም የሚያስከብርላቸው አካል እንደሚፈልጉ የተናገሩት ረዳት ፕሮፌሰር መሐመድ፤ በዚህም ሀገራቱ ከጥቂት ወራት በፊት በሰብዓዊ መብት ስም በኢትዮጵያ መንግሥት ላይ ከፍተኛ ጫና ሲያደርጉ እንደነበር አብራርተዋል፡፡

በአሁኑ ጊዜ ይህ ጫና አልፎ በአሜሪካና በአፍሪካ መሪዎች ጉባዔ ላይ ኢትዮጵያ ተጋባዥ መሆን መቻሏን አንስተው፤ የኢትዮጵያ በዚህ ጉባዔ ላይ መጋበዝ ትልቅ እንድምታ ያለው መሆኑን ተናግረዋል፡፡ በጠላትነት ተፈርጆ የነበረው የኢትዮጵያ መንግሥት በጉባዔው ላይ ተጠርቶ መሳተፉ በራሱ ትልቅ ድል ነው ሲሉም አክለዋል፡፡

እንደ ረዳት ፕሮፌሰር መሐመድ ገለጻ፤ ምዕራባውያን እንደፈለጉ የሚያዙት መንግሥት በኢትዮጵያ ለማስቀመጥ የቱንም ያህል ጥረት ቢያደርጉም አልተሳካላቸውም፡፡ በተጨማሪም የኢትዮጵያ መንግሥት በሰሜኑ የሀገሪቱ ክፍል ያደረገውን ጦርነት በበላይነት በማሸነፉ ኢትዮጵያ የማትበገር አገር መሆኗን እንዲያረጋግጡ ዕድል ፈጥሮላቸዋል፡፡ ይህም ለኢትዮጵያ ዲፕሎማሲ ዕድገት አስተዋፅዖ አበርክቷል፡፡

በተጨማሪም ከቅርብ ጊዜ ወዲህ የኢትዮጵያ መንግሥት በዲፕሎማሲው ረገድ ጠንካራ ሥራ እየሠራ ስለነበር አሜሪካን ጨምሮ የሎች ሀገራትን ልብ ያሸነፈበት ሁኔታ መፈጠሩን አንስተዋል።

አንዳንድ ምዕራባውያን ኢትዮጵያ ከምታደረገው ዲፕሎማሲ አልፎ ተርፎ የአፍሪካ ቀንድ አካባቢ አለመረጋጋት ስለሚታይበት ይህንን አለመረጋጋት ሊፈቱ ከሚችሉ ሀገራት መካከል ዋነኛዋ ኢትዮጵያ መሆኗን በማሰብ ጭምር የዲፕሎማሲ ግንኙነታቸውን እንዳጠናከሩ ገልጸዋል፡፡

# ርዕሰ አንቀፅ

## ስልጡን እና ሀገርን የሚያስቀድም የፖለቲካ አካሄድ ያስፈልገናል!

ኢትዮጵያ የብዙ ሺ ዓመታት የዳበረ ታሪክና ሀብት ባለቤት ነች፤ የሰው ዘር መገኛ እና የሰው ልጆች ስልጣኔ መነሻ፤ የአትንኩኝ ባይነትና የነጻነት ፋና ወጊ መሆኗም የአደባባይ ምስጢር ነው።

ይህንን በሚቃረን መልኩም ለዘመናት እንደ ሀገር የግጭትና የጦርነት፤ ከዚህ የሚመነጭ የድህነትና የኋላቀርነት ተምሳሌት ተደርጋ የምትወሰድ፤ በዚህም ከፍ ያለ ዋጋ ለመክፈል የተገደደች ሀገር ነች።

ግጭትና ጦርነት ፣ ኋላቀርነትና ድህነት የቀደመ ታሪኳን ያሳደፉባት፣ ሕዝቦቿንም አንገት አስደፍተው በዓለም አቀፍ መድረኮች ሙሉ በሙሉ ቀና ብለው እንዳይጓዙ ተግዳሮት የሆነባት ሀገርም ነች።

እንደ ሀገር የቀደመውን ታሪኳን በተሻለ ደረጃ ማስቀጠል ቢያቅታት ፤ የነበረውን ይዛ መጓዝ አለመቻሏ ለብዙ ትውልዶች ጥያቄ የሆነ ፣ በዚህ ትውልድ አዕምሮም የሚመላለስ ትልቅ ሀገራዊ አጀንዳ ነው።

ለዚህ ደግሞ ዘመናት ያስቆጠረው በመንግስትና በሕዝብ አስተዳደር ሥርዓቷ ውስጥ ሰርፆ የገነገነው፣ ኋላ ቀር የፖለቲካ ባህላችን በዋንኛነት ተጠቃሽ እንደሆነም የተለያዩ ጥናቶች ያመላክታሉ።

በሴራ፣ በጥላቻና በመጠላለፍ ላይ የተመሰረተው ይኸው የፖለቲካ ባህላችን ዛሬም ቢሆን ሀገርን እንደ ሀገር ከፍ ያለ ዋጋ እያስከፈለ ስለመሆኑ፤ ችግሩን ፈጥኖ ማረም ካልተቻለ በቀጣይ የሀገር ህልውና ስጋት የሚሆንበት ደረጃ ሊደርስ እንደሚችልም ይታመናል።

በአሸናፊና ተሸናፊ ትርክት ላይ የተመሰረተው ለዘመናት የኖረ ቆሞ ቀር የፖለቲካ ባህል ፤ የቀጣይ ሀገራዊ እጣ ፈንታችን ላይ እያጠለለ ያለው ጽልመት ባለፉት አራት ዓመታት/ከለውጡ ማግስት ጀምሮ ሀገርን በብርቱ ሲፈትን የተስተዋለ ነው።

በእርስ በርስ ጦርነት አንዱ አንዱን ገድሎ፤ካልሆነም አስገብሮ መንግስት የመሆን መቶዎች ዓመታትን ያስቆጠረው ይሄው ባህላችን በቀደሙት ትውልዶች ደም ነፍስ እንደዘራ ሁሉ፤ የዛሬውን ትውልድ ደም የመጠየቁ እውነታም በእነዚህ ዓመታት ታይቷል።

በ21ኛው ክፍለ ዘመን አብዛኛዎቹ ፖለቲከኞቻችን የዘመናዊ ትምህርት ዕድል ተጠቃሚዎች ብቻ ሳይሆኑ፤ የባለ ብዙ ክብር ባለቤት በሆኑበት ሀገራዊ እውነታ አንዳንድ ፖለቲከኞቻችን ከዚህ ኋላ ቀር እና ቆሞ ቀር የፖለቲካ አስተሳሰብ አለመላቀቃቸው ለተራው ሕዝባችን ሳይቀር አጠያያቂ ነው።

አንዳንድ ፖለቲከኞቻችን ከዚህ ትውልድ ተሻጋሪ ችግር ራሳቸውን ከመታደግ ይልቅ አስተሳሰቡ ተጨማሪ የጥፋት አቅም እንዲያገኝ ዘር እና ሀይማኖትን የፖለቲካ መጫወቻ ካርድ አድርገው መምጣታቸው፤ በሀገሪቱ ቀደምት ችግሮች ላይ "በእንቅርት ላይ ጆሮ ደግፍ " ሆኗል፤ እያስከፈለ ያለውም ዋጋ የብዙ ዜጎችን ልብ የሰበረ ነው።

በርግጥ በየትኛውም የዓለም ክፍል የሚገኙ ፖለቲከኞች የፖለቲካ ህሳቤ መሰረቱ የሕዝብ ፍላጎት እንደሆነ ይታመናል፤ከዚህ አንጻር አንዳንድ ፖለቲከኞች ቢያንስ ቢያንስ ህዝባችን ከለውጡ ዋዜማ ጀምሮ ይዞት ለተነሳለትና ብዙ ዋጋ ለከፈለለት መሻቱ ተገዥ መሆን ነበረባቸው።

ለዚህ ደግሞ ከሁሉም በላይ ሀገርና ሕዝብን በትውልዶች መካከል ብዙ ዋጋ ካስከፈለውና እያስከፈለ ካለው የሴራ፣ የጥላቻና የመጠላለፍ ቆሞ ቀር ኋላቀር ፖለቲካ ራሳቸውን ማራቅ ፤ከዚህ አጥፊ የፖለቲካ ጉዞ ራሳቸውን ማቀብ፤ ለዚህም የሚሆን ቁርጠኝነት ማሳየት አለባቸው።

ይህን ለማድረግ ደግሞ አስተሳሰቡ በዘመናት መካከል የቱን ያህል ሀገርን ዋጋ እንዳስከፈለ ፤ ከነበርንበት የከፍታ ስፍራ የቱን ያህል ለዝቅታ ጫፍ እንዳደረገን በነጻ አእምሮ፤ ከፍ ባለ ሕዝባዊ መንፈስ እና ኃላፊነት በአግባቡ መረዳትና የጠራ ግንዛቤ መፍጠር ይፈልጋል።

ኋላ ቀር የፖለቲካ አስተሳሰብ መልኩን እየቀያየረ ዛሬም ዋጋ እያስከፈለን መሆኑንና በዝምታ ካስቀጠልነው መጪውን ትውልድ ተመሳሳይ ዋጋ ሊያስከፍል፤ ከከፋም ሀገርን ለአደጋ ሊዳርግ እንደሚችል አርቆ ማሰብን ይጠይቃል።

ችግሩ ስልጣንና ከስልጣን የሚመነጭን ተጠቃሚነት፤ ከሕዝብና ከሕዝብ ፍላጎት፤ ከትውልድና ከትውልዶች የተሻለ እጣፈንታ አሳንሶ የማየትና በተጨባጭም ያነሰ መሆኑን በተግባር አሳይቶ መገኘት፤ በዚህም ታሪክን ጽፎ ማለፍን የሚጠይቅ ነው!


ኢፕድ

# አዲስ ዘመን

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስኪያጅ**

ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22

**ዋና አዘጋጅ**

አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**

ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ

ወረዳ 06

የቤት ቁጥር 319

ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et

ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**

ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ

ስልክ፡- 011 126 4240

Email:- wendweson.shimelis@press.et

wendwesonshimelis@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**

- ወርቁ ማሩ
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- አልማዝ አያሌው
- እስማኤል አረቦ

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**

ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com

ስልክ - 011-126-43-41

ፋክስ - 011-811-13-15

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**

ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73

ፋክስ - 011-126-58-12

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**

ስልክ - 011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ**

ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


**ነፃ ሃሳብ**

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው፡፡ በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም፡፡

## ራስ-ፈስቅ መፍትሔዎችን በመጠቀም ከራስ ጋር የመታረቅ መልካም ጅምር

ደበል ካሳ

ኢትዮጵያ የብዙ ሺ ዓመታት የዳበረ ሥጋዊና መንፈሳዊ ሃብት ባለቤት፣ ከሁሉም በፊት የነቃች፣ የሰው ዘር መገኛና የሰው ልጆች ስልጣኔ መነሻ እርሾን የጣለች አኩሪ ታሪክ ያላት ታላቅ ሃገር ብትሆንም ቀድማ ወደፊት መጓዝ ያልቻለች መሆኗ ማስረጃ የማያሻው እና ማንም ሊያስተባብለው የማይችለው የኢትዮጵያውን ሁሉ መራራ ሃቅ ነው። እንዲያውም የቀደምትነቷን ያህል በጀመረችበት ፍጥነት መጓዝ ቢያቅጣት እንኳን የያዘችውን አስጠብቃ መቀጠል አቅቷት በብዙ መልኩ ከነበረችበት ተንሸራታ ጀማሪ ኋላቀሪ ሀገር መሆኗን የአሁኑ ታሪካችን ቁልጭ አድርጎ እያሳየን ነው።

ጉዟችን ወደኋላ መሆኑ እጅግ የሚያሳዝን ቢሆንም መሰረታዊው ነገር ግን "መሆኑ" ሳይሆን "ለምን ሆነ?" የሚለው ጥያቄ ይመስለኛል። መሆኑማ በቃ አንድ ጊዜ ሆነ፤ ደግሞም "ላለፈ ክረምት ቤት አይሰራም፣የፈሰሰ ውሃም አይታፈስምና" ቀድመን ጀምረን ኋላ ቀሪ መሆናችንን እያስታመምን ሁሌም "መሆኑ" ላይ ተሰክቶ መቅረቱ ዋጋ የለውም። የሚሻለው "ለምን ሆነ?" የሚለውን የቀዳሚ ኋላቀርነታችንን መሰረታዊ መንስኤ በጥልቀት በመርመርና ወደፊት እንድንጓዝ የኋልዮሽ አስሮ ጠፍንጎ የያዘን ዋነኛ ችግራችን ምን እንደሆነ ማወቅና ለችግሩ ዘላቂ መፍትሔ በማበጀት ከወደቅንበት ተነስተን ታላቋ ሀገራችን እንደጅማሬዋ ከፊት ቀድማ የምትገኝበትን ብልሃት መዘየድ ነው።

ለዚህም በቅድሚያ የችግሩን መንስኤ ለይተን ማወቅ ይጠበቅብናል። ከዚህ አኳያ ለመሆኑ ታላቋን ሀገር ኢትዮጵያን በጀመረችው ፍጥነት ወደፊት እንዳትጓዝ፤ ባለችበት ቆማ እንድትቀርና ይባስ ብሎ በየጊዜው ወደ ኋላ እየተንሸራተተች ቀድሞ ኋላ ቀሪ እንድትሆን ያደረጓት ችግሮች ምንድናቸው? ብለን የጠየቅን እንደሆን በርካታ ምክንያቶችን እናገኝ ይሆናል። ዋነኛው፣ ኢትዮጵያን ባለችበት እያስረገጠ አንዳንዴም የኋልዮሽ እያስጓዘ ከዓለም ቀድማ ከጀመረችው የመሪነት ጉዞ አሰናክሎ አድርቆ ያስቀራት ክፉ ጠላት የስልጣኔና የዕድገቷ አቀንጭራ ግን አንድ

"ለኢትዮጵያ ቀድሞ ሰልጥኖ ከኋላ መቅረት ምክንያቶቹ ሁለት ናቸው" እነርሱም አንደኛው ዘመናዊ ትምህርት ቀደም ብሎ ወደ ኢትዮጵያ እንዳይገባ መደረጉ፤ ሁለተኛው ደግሞ በእርስ በእርስ ጦርነት አንዱ አንዱን በመግደል የሚፈጸም የመንግስት የሽግግር ባህላችን ነው

ነው። እርሱም በመንግስትና በሕዝብ አስተዳደር ሥርዓቷ ውስጥ ሰርፆ የገነገነው፣ ሁልጊዜ የማያድገውና ከዓለም ኋላ ቀርቶ ኋላ የሚያስቀረው ቆሞ ቀሩ የፖለቲካ ባህሏ ነው።

በእኔ ዕምነት ከጥንት ጊዜ ጀምሮ እስከ አሁን ድረስ ከብሉይ እስከ ሐዲስ ታላቂቷ ሀገር ታላቅ መሆን በሚገባት ደረጃ ታላቅ እንዳትሆንና በተነሳችበት ልክ ወደፊት እንዳትጓዝ ከኋላ ሆኖ ሲጎትታት የኖረው የኢትዮጵያ ዋነኛው ችግር በሴራ፣ በጥላቻና በመጠላለፍ ላይ የተመሰረተው ይኸው ኋላ ቀሩ የፖለቲካ ባህላችን ነው። በእርግጥ ይህ የእኔ ብቻ ሳይሆን የሀገሩ "ቀድማ ኋላ ቀሪነት" የሚቆጨውና የወደፊት መጻኢ ዕድሏ የሚያሳስበው ኢትዮጵያዊ ሁሉ የሚጋራው መሰረታዊ እውነታ ነው።

ይህ ጉዳይ ካሳሰባቸው ኢትዮጵያውን መካከል አንዱ የሆኑት "ሰላማዊ ትግል 101" በሚል ርዕስ በ2006 ዓ.ም መጽሃፍ ያሳተሙት በሞያቸው የኤሌክትሪክ መሃንዲሱ አቶ ግርማ ሞገስ አንዱ ናቸው። ከ1967 ዓም ጀምሮ እስከ 1998 በኢሕአፓ አባልነት መቆየታቸውን እና በቆይታቸው ከተማሯቸው በርካታ ቁም ነገሮች በተጨማሪ በህቡዕ ተደራጅቶ ስለሚደረግ የፖለቲካ ትግል አደገኝነት እንዲያስተውሉና በጠብ-መንጃ ስለሚፈጸም የሀገራችን የመንግስት ሽግግር ባህላችን እንዲመራመሩ ዕድል የፈጠረላቸው መሆኑን ይናገራሉ።

ደራሲው ከረጅም ዘመናት ሕዝባዊ ትግል በኋላ ወደ ዲሞክረሲያዊ ሥርዓት ለመሸጋገር በ1997 ዓ.ም ተገኝቶ የነበረው ታሪካዊ ዕድል ሆን ተብሎ መቀልበሱ ሙሉ ጊዜያቸውን ሰጥተው የኢትዮጵያን የመንግስት ሽግግር የፖለቲካ ባህል እንዲመረምሩ አስገድዷቸዋል። "ኢትዮጵያ ቀድማ ሰልጥና ለምን ወደ ኋላ ቀረች ለሚለው ጥያቄ መልስ ለማግኘት ታሪካችን መመርመር ያስፈልጋል" የሚሉት አቶ ግርማ ፤ "ለኢትዮጵያ ቀድሞ ሰልጥኖ ከኋላ መቅረት ምክንያቶቹ ሁለት ናቸው" እነርሱም አንደኛው ዘመናዊ ትምህርት ቀደም ብሎ ወደ ኢትዮጵያ እንዳይገባ መደረጉ ፤ ሁለተኛው ደግሞ በእርስ በእርስ ጦርነት አንዱ አንዱን በመግደል የሚፈጸም የመንግስት የሽግግር ባህላችን ነው ባይ ናቸው ፡፡

ዘመናዊ ትምህርት ወደ ኢትዮጵያ የገባው በምዕራብ አውሮፓ ከተጀመረና የሕብረተሰቡን ባህል መቀየር ከጀመረ ከዘጠኝ መቶ ዓመታት በኋላ ዘግይቶ መሆኑና ሀገሪቱ እርሱን ተከትሎ ለሚመጣ ዘመናዊነትና ስልጣኔ ጀርባዋን ሰጥታ መቆየቷ በዕድገት ወደ ኋላ ለመቅረቷ አንደኛው ምክንያት ነው። የእኛ ትኩረት

ወደ ገጽ7 ዞሯል

ስፖርት እና መዝናኛ

# ፋሽን

## በራስ ወርቅ መድመቅ

**በሙሉጌታ ብርሃኑ**



በዘመናችን ፋሽን የአብዛኛው ሰው የእለት ከእለት የኑሮው አንድ አካል መሆን ከጀመረ ሰነባብቷል። ምን ልብላ? ምን ልጠጣ? ከማለት ባልተናነሰ መልኩ ምን ለብሼ? በምን ላጊጥ? የሚለው ጉዳይ በተለይም በከተሜው ሕዝብ ዘንድ ጎልቶ እየታየ መጥቷል። መቼም ሁሉም ሰው ማለት ይቻላል ቆንጆ ሆኖ በሌሎች ዘንድ መታየትን አይጠላም፣ አይጠላም ብቻ ሳይሆን ይወዳል። ይህን መውደዱም ተፈጥሯዊ ነው ተብሎ ይታመናል። በአንዳንዶች ዘንድ ግን በፋሽን ተውቦ፣አምሮና አጊጦ መታየትን ከመውደድም ያለፈ እንደ ግዴታ የሚታይበት አጋጣሚ ትንሽ አይደለም። "ፏ! ፈሽ! ብለን ካልቀረብን ውሏችን ውሎ መልካችንም መልክ አይመስለንም" የሚሉ የፋሽን ተከታዮች ቁጥር ቀላል አይደለም።

ታዲያ በፋሽን አምሮና ተውቦ የመታየት ጉዳይ ሲነሳ ፋሽን መከተል የራሱ አሉታዊና አዎንታዊ ተፅእኖ አለውና ስንቶቻችን በፋሽን ለመዋብ የምንጨነቀውን ያህል የምንከተለው ፋሽን ከባህልና ማህበረሰባችን አኳያ ተጨንቀን እንዋባለን? ስንቶቻችንስ የሀገራችንን ወግና ባህል፣ ስርአትና ልማድ በጠበቀ መልኩ ፋሽንን እንከተላለን? የሚለው ጉዳይ ብዙ ጊዜ አነጋጋሪ ነው።

አንዳንዴ ከራስ ጸጉር እስከ እግር ጥፍራችን አለባበሳችን ሌሎች ላይ አይተን ከወደድነው አሊያም ከምናደንቀው ሰው በመኮረጅ ሊሆን ይችላል። ከዚያም የወጪ ወራጁ አይን እኛ ላይ መሆኑን ስናይ 'አቤት ምን ያህል ቆንጆ ሆኜ ብታያቸውና ብማርካቸው ነው እንደዚህ የሚያፈጡብኝ..' እያልን በልባችን ስንብሰለሰል፤ የተገላቢጦሽ "አዬ ይሄማ ከአማኑኤል ያመለጠ እብድ መሆን አለበት...ደግሞ ብላ ብላ ላባዋ የረገፈ ዶሮ መስላ መጣች..." የሚል ይገጥመናል። አለባበሳችንን ተመልክቶ ሰው "ከአይን ያውጣሽ፣ ከአይን ያውጣህ" ይለኛል ብለን ስንጠብቅም 'አይንህ ይውጣ' ሊመጣብንም ይችላልና ነገሩ 'ያሉሽን በሰማሽ ገበያ ባልወጣሽ' እንዳይሆንብን የምንከተላቸው የፋሽን ከማህበረሰባችን ስብዕና ጋር የሚሄድ መሆኑን ቀደም ብለን ማሰብ እንደሚገባ ይታመናል።

ፋሽን የዘመናዊነትና የስልጣኔ ምልክት ነው። ፋሽንን መከተልም ክፋት የለውም። መጥፎነቱ ግን በማይጠቅሙን መጤ ፋሽኖች ተከትበን የምንኖርበትን ማህበረሰብ ስርዓት መጠበቅ ካልቻልን ነው። ያኔ የራሱ የሆነ ትልቅ አደጋ አለው። 'ሲያዩት ያላማረ ሲበሉት ያቅራል' የሚለው ማህበረሰባችን ቀድሞ ስብዕናችንን የሚለካው በሚያየው ገጽታ ስለሆነ በውስጣችን ያለውን ጥሩ ነገር ለማሳየት ብንጥር እንኳን አይሆንልንም።

በዘመናችን ወቅቱ የዋጃቸውን ፋሽኖች ከባህልና ወጋችን አኳያ መከተል ከባድ አይደለም። ለዚህ ደግሞ የሀገራችን ቱባ ባህሎች ከማንም በላይ ለፋሽን ምቹ ናቸው። ትልቁ ፈተና የሚገጥመን ማህበረሰባችን ፋሽን የማይወድ ስለሆነ አይደለም። ፈተናው ያለንን አውደ ብዙ ባህል ተጠቅመን ከዘመኑ ጋር የሚጣጣም የራሳችን የሆኑ ፋሽኖችን መፍጠር ሲያዳግተን ነው።

በምእራባውያን የባህል ወረራ ተፅእኖ ውስጥ ወድቀን ከባህልና አይነኬ እሴቶቻችን የሚፃረሩ ፋሽኖችን እንከተል ካልን ከሰፊው ማህበረሰባችን ጋር እንደሚያጋጨን ሳይታለም የተፈታ ነው። የጥንቱ ባህልና ወግ እንደወረደ ሙጭጭ ብለን ስንቀር ደግሞ ከዘመኑ ጋር እንጋጫለን፤ ስለዚህ ቁልፉ የሚገኘው ባህልን ከዘመኑ ጋር የማጣጣም ፈጠራ ላይ ነው። የፋሽን ወረራ የባህል ወረራን የሚያስከትል፣ ጋሻና ጦር ይዘን የማንመክተው ረቂቅ ነገር በመሆኑ በትኩረት ማጤኑ የሁልጊዜም የፋሽን ተከታዮች የቤት ስራ ነው።

ኢትዮጵያ በፋሽን ረገድ የታደለች አገር ናት። ከራያ እስከ ቆቦ፣ ከሶማሌ እስከ ባሌ፣ ከሸሬ እስከ አደሬ፣ ከጎጃም እስከ የም፣ ከጎንደር እስከ አፋር፣ ከጉራጌ እስከ ሀረርጌ ኧረ! ስንቱ ተነስቶ ያልቃል። እኚህን ሁሉ ቱባ ባህሎች ይዘን የሌላውን ከቋመጥን ሀገራዊ ኩራታችን ብቻ ሳይሆን ጥልቁ ማንነታችንም በማይረባ ቅራቅንቦ ይሸፈናል። ዋናው ቁም ነገር ቬሎን ትተን በሀበሻ ቀሚስ እንሞሸር አይደለም፤ ቬሎ ብለን ለሰርግ ጊዜ የምናጌጥበትን ልብስ እንደ ወረደ ከሌላው አለም አምጥተን ከምናጌጥ ከአገራችን ከቱባ ባህሎች ጋር አስተሳስረን እኛን በሚገልጽ መልኩ አሰናድተን ልንደምቅበት አንችልም ወይ? ነው።

በእርግጥ እንደ ምሳሌ ባነሳነው የሰርግ ቬሎ ሙሽሮች በሰርጋቸው ወቅት ማጌጡን በተወሰነ ደረጃ እያስቀሩ መጥተዋል። በከተሞችና ፋሽን ተከታዮች ነን በሚሉ ሰዎች ሳይቀር ከዘመናዊው ቬሎ ይልቅ ሰርጎች በአገር ባህል ልብሶች እየደመቁ መጥተዋል። በዚህ ረገድ ሰፊ ለውጥ እስካሁን ማየት ባይቻልም ጅምሩ አበረታችና ሊያድግ የሚችል ነው።

ይህን ጅምር ለማሳደግና የሚታይ ለውጥ ለማምጣት በሀገራችን እውቅ የፋሽን ዲዛይነሮች የተጀመሩ አበረታች የፈጠራ ስራዎች አሁን አሁን ብቅ እያሉ ቢገኙም የራሳችንን ቱባ ፋሽን በመከተል ሀገራችንን ለአለም ማሳየቱ የእያንዳንዳችን ድርሻ ነው። ቁጥር ስፍር ከሌላቸው ባህሎች እየተቀዱ በዘመናዊ መልኩ እየተፈሸኑ ለገበያ የሚቀርቡ አልባሳቶች ከቅርብ ጊዜ ወዲህ ሰፊ ተቀባይነት ማግኘት እንደቻሉ ይታወቃል። ለዚህም የአገራችን ዲዛይነሮች የፈጠራ ጥበብ ትልቁን አስተዋፅኦ አበርክቷል። በቂ ነው ማለት ግን አይቻልም። ዲዛይነሮች ተጨንቀውና ተጠበው ባህልን ከዘመናዊ ፋሽን ጋር ሲያስተሳስሩ በህዝብ ዘንድ ተቀባይነትን የማግኘት ችግር እንደሌለ መመስከር የሚያስችሉ ማስረጃዎች ብዙ ናቸው። ይህም ዲዛይነሮች የባህል ወረራን የመመከት ትልቅ ጉልበት እንዳላቸው ማሳያ ነው። ኢትዮጵያ በሰርግም ይሁን በሌሎች ኩነቶች የሚዘወተሩ ፋሽኖችን ከባህልና ወግ ጋር አስተሳስራ ለመጠቀም ያላት እምቅ ሃብት ገና አልተነካም። ዲዛይነሮች በዚህ ረገድ የባህር ውሃ በጭልፋ ተቀድቶ እንደማያልቀው ሁሉ እያንዳንዱን ባህል እየፈተሹ በማውጣት በጥበብ እጃቸው ዳብሰውና ዘመኑን ዋጅተው እንዲወጡ ተኝተው ማደር የለባቸውም። ይህንንም የባህል፣ወግና የሞራል ግዴታቸው አድርገው ሊሰሩበት ይገባል።

# ትዝብት/ ማረፊያ

## ጠርጥር ! ከገንፎም ውስጥ አለ ሥንጥር

**መልካምሥራ አፈወርቅ**

ሰውዬው በጠና ህመሙ ሳቢያ ካልጋ ከዋለ ቆይቷል። ችግሩ ስር ሰዷልና በሀኪም ቤት በዕምነትና ሀይማኖት ስፍራዎች ሲንከራተት ከራርሟል። ቆይቶ በሽታው ከአቅም በላይ ሆነ። ውሎ አድሮም ከእጅ ያለ ገንዘብ፣ ከቤት የቆየ ጥሪት ሁሉ ተሟጠጠ፡፡

ወዲህ የታማሚው ስቃይ ፋታ አልሰጠም። ወዲያም የቤት፣ የቤተሰቡ ችግር ቀላል አልሆነም። ይህኔ አንዳንዶች ይበጃል ያሉትን መላ ዘየዱ። ሰውዬው ከቤት ውሎ ህመሙን ከሚያዳምጥ፣ እጆቹን ለእርዳታ እንዲዘረጋ፣ በሚገኘው ገንዘብም የህክምናው ወጪ እንዲሸፈን ተወሰነ።

ውሳኔው መሬት ጠብ አላለም። ሁሉም የሚገኘውን ገንዘብ እያሰበ የታማሚውን ታክሞ መዳን ተመኘ። ሀሳቡን ለመተግበር ጊዜ አልፈጀም። የሰውዬውን የቀድሞ ገጽታና አሁን ያለበትን እውነታ የሚያሳዩ ፎቶግራፎች ተዘጋጁና፣ በሰፋፊ ባነሮች ታተሙ። ጉዳዩ በዚህ ብቻ አልበቃም። ምስሎቹን ለጥፎ የሚያሳይና ታማሚውን አስተኝቶ እርዳታ የሚያሰባስብ ሚኒባስ ታክሲ ጭምር ለመከራየት ታቀደ። የታሰበው አልቀረም። ዝግጅቱ ሲጠናቀቅ በቀን ኮንትራት የሚከፈለው መኪና ቀርቦ ህመምተኛውን ተረከበ፡፡

ሰውዬው በጀርባው ተንጋሎ በስቃይ እየተንገላታ ነው። ከመኪናው አናት ከፍ ብሎ የሚሰማው ሙዚቃ «እኔነኝ ደራሽ ለወገኔ» ይሉትን ዜማ ይደጋግማል። በየመሀሉ ሙዚቃው እየቆመ በድምጽ ማጉያ መልዕክት ይተላለፋል። መልዕክቱን ለሚሰማው ሁሉ ሀዘን ያጭራል፣ ውስጥን ይነካል። አብዛኞች ቆም ብለው ፎቶዎችን ያስተውላሉ፣ በሚያዩት እያዘኑም ያላቸውን ይሰጣሉ፣ ይረዳሉ፡፡

ቀኑን ሙሉ በስቃይ የሚውለው በሽተኛ በእርዳታ ከሚያገኘው ገንዘብ የመኪናውን ኪራይ ሰጥቶ፣ ምሽቱን ከቤት ይገባል። ማግስቱን ሲመለስም የትናንቱ ውሎ እንደነበረው ይቀጥላል። በሙዚቃው መሀልም የተለመደው ቃል ይደጋገማል፡፡

«እዚህ መኪና ውስጥ የምታዩት ወንድማችን አቶ እከሌ እከሌ ይባላል። ሁለቱም ኩላሊቶቹ ከጥቅም ውጭ በመሆናቸውና ለውጭ አገር ህክምናው ይህን ያህል ገንዘብ በማስፈለጉ የእናንተን እጅ ለማየት ተገዷል፣ በመሆኑም ....

አሳዛኙና ልብ የሚነካው ንግግር በዝግታ ይቀጥላል። ፎቶውን ተመልካች፣ መልዕክቱን አድማጭ መንገደኛ ሁሉ ከታላቅ ሀዘን ጋር ከእጅ፣ ከኪሱ፣ከመሀረብ፣ ከቦርሳው የቻለውን ይሰጣል። አንዳንዶች ቀረብ ብለው በዓይናቸው የሚያዩትን ህመምተኛ «እግዜር ይማርህ፣ ያሰብከው ይሳካልህ ይሉታል። ቀኑ በተለመደው ሙዚቃና በጆሮ ገብ መልዕክት ታጅቦ እስከምሽቱ ይቀጥላል። ማግስቱም፣ እንደትናንቱ ሆኖ ያልፋል፡፡

የሰውዬው ሥቃይ አልቆመም። ህመሙ ጸንቷል፣ በሽታው ከፍቷል። በየዕለቱ ውስጡ እየደከመ፣ አካሉ እየዛለ ነው። የሚሰበሰበው ገንዘብ ለታሰበው ዓላማ የዋለ አይመስልም። ያለውን ከመጠቀም ይልቅ በየቀኑ ቦታ እየለወጡ መለመን ጣፋጭ አማራጭ ሆኗል።

ከዕለታት በአንዱ ቀን ታማሚው ስቃዩን መቋቋም ተሳነው፣ ከአልጋ ወርዶ ከመኪና መግባት ቢያቅተው ከቤት ተኝቶ ሊውል ግድ አለ። ሰዎቹ ይህን ሲያውቁ በርትቶ እንዲነሳ ወተወቱት። ፈጽሞ አልቻለም። እንዳሰቡት ሳይሆን ቀርቶ ህመሙ ቀናትን ቆጠረ ። ሰውዬው ከተኛበት አልተነሳም። አንድ ማለዳ ደግሞ ከነወዲያኛው አሸለበ፡፡

የታማሚውን የመዳን ፍላጎት ያወቁ፣ ጥረት ሩጫውን ያዩ በሞቱ አዘኑ፣ አለቀሱ ። ስቃይ ህመሙን የተረዱ ሌሎችም ሞቱን «እፎይታው ነው» ሲሉ አሰቡ ። የሀዘን ቀናት አንድ ሁለት ተብለው ተቆጠሩ። ውሎ አድሮ ለቅስተኛው ተሸኘ ። ሀዘንተኞች ተጽናኑ ። ሟች በነበር እየተወሳ ፣በትዝታ ታወሰ፡፡

ከዕለታት በአንዱ ቀን የሟችን ፎቶና የ«አድኑኝ» መልዕክትን የያዘ ሚኒባስ በአንድ አካባቢ መታየቱ ተሰማ። ቀኑን ሙሉ ህመም ስቃዩን እየተረኩ፣ ስለህክምናው ወጪ የሚለፍፉ ሰዎች አሁንም ስራቸውን ቀጥለዋል። እሱ ሞቶ ቢቀበርም የእነሱ የገንዘብ ፍላጎት ፈጽሞ አላንቀላፋም። በየቀኑ የሚያገኙትን ጥቅም እየለቀሙ እፍታውን መካፈላቸውን ይዘዋል። ቦታ እየለወጡ፣ መረጃ እያዛቡ በሟች ስም ሲነግዱ የቆዩት ስግብግቦች ፖሊስ ደርሶባቸው በቁጥጥር ሥር እስኪውሉ በርካቶችን አታለዋል። ዕምነትና ሞራል የለሽ ሥራቸውም በእውነተኞቹ እርዳታ ፈላጊዎች ላይ ከባድ ተፅዕኖ አጥልቷል።

ይህን ጉዳይ እንደመነሻ ላውጋው እንጂ በከተማችን የሚስተዋለው መሰል ድርጊት ሀቀኛውን ከአጭበርባሪው ለመለየት የሚያዳግት ሆኗል። እርግጥ ነው ኩላሊትና ካንሰር ይሉት በሽታ ጊዜ አይሰጥም። ከስቃዩ ባለፈ ህክምናውን ለመሸፈን አቅም ሲያንስ፣ እጅ ሲያጥር ደግሞ የሰው ፊትን ማየት፣ እርዳታን መሻት ሊያስገድድ ይችላል፡፡

ጉዳዩ እንዲህ መሆኑ ላይ አይደለም። ከቅርብ ጊዜ ወዲህ የሚስተዋለው በመኪና የመለመን ልማድ ለዓይን እስኪያዳግት፣ ለማመን እስኪቸግር እንደባህል ተለምዷል፣ እንደግዴታ ተቆጥሯል። አሁንም ይህን ጉዳይ ሳነሳ የተቸገሩ፤ እርዳታን የሚሹ፣ የሉም እያልኩ አይደለም። ከሚባለው በላይ በችግር ውስጥ ያሉ፣ በህመም የሚሰቃዩ ወገኖች መኖራቸው አይካድም። እንዲህ መሰሎች ባሉበት ግን ሀሰተኞቹ ተከልለው ብዙሀንን እንዳያታልሉ፣ ለእውነተኞቹም ዕንቅፋት እንዳይሆኑ ያሰጋል።

አሁን አሁን በሰፊ የፎቶግራፍ ባነሮች የሚሸፈኑ፣ በአሳዛኝ የ«አድኑን » መልዕክቶች የሚታወቁ መኪኖች በእጅጉ በርክተዋል። የመኪኖቹን ሆድ ጠጋ ብሎ ላየውም ታማሚ ነው የሚሉትን ሰው ከነስቃዩ አስተኝተው የሚያስጎበኙ ጥቂቶች አይደሉም፡፡

ይህ ብቻም አይደለም፣ ከመንገዱ ዳርቻ ከቆመው መኪና ዙሪያ የሚታዩ ወጣቶች ባዶ ካርቶኖችን ይዘው አላፊ አግዳሚውን በልመና ያታክታሉ። እነዚህ ወጣቶች እርዳታ መጠየቃቸው አንድ ጉዳይ ሆኖ መንገደኞች እንዳይራመዱ፣ አልፈው እንዳይሄዱ የሚጠቀሙበት ስልት የሚያሸማቅቅ ነው። አንዳንዴ ወጣቶቹ የሚጠይቁትን ሰው ፍላጎት የሚጠብቁ አይሆኑም። በርቀት ያዩትን መንገደኛ አጠገባቸው እስኪደርስ ጠብቀው በልመና መድረሻ ያሳጡታል። እግረኛው የመጀመሪያዎቹን አልፎ ወደፊት ለመራመድ መንገዱ የዋዛ አይሆንለትም። ሰጥቶ ማለፍ ግዴታና ግዴታ የሆነ ያህል ከፊት ከኋላው የሚከተሉት ባለካርቶኖች ከአእምሮ በላይ ይሆኑበታል።

እርዳታ መጠየቁ በአንድ መስመር ከሁለትና ሶስት በላይ ሊያጋጥም ይችላል። በተለይ በርካቶች በሚያዘወትሩት ቦታ የተለያዩ ሰዎች ተመሳሳዩን ድርጊት ሲፈጽሙት ይስተዋላል። ባለካርቶኖቹ እግረኞቹን አጥብቆ ከመለመን ባለፈ መብራት ይዟቸው የሚቆሙ መኪኖችንም ጭምር በልመና ያስጨንቃሉ፡፡

ከፊት ከኋላ ሆነው ካርቶኖቻቸውን እየነቀነቁ፣ የሚጠይቁት ተለምዷዊ ምዕዋትም በብዙዎች ዘንድ የሚሰለች ሆኗል። አብዛኛው ተመልካች የወጣቶቹን ድርጊት በበጎ የሚያውን ያህል ጥቂት የማይባለው ደግሞ በተከፈለ ልብ ያስተውለዋል። ስለ ህመምና ስቃይ ሲባል ነፍስን መታደጉ መልካም ጉዳይ ሆኖ ከዚህ ጀርባ ሊኖር የሚችልን ማጭበርበርም ከጥርጣሬ ያኖረዋል፡፡

አዎ! ምን አልባትም ወጣቶቹ ጊዜና ጉልበታቸውን የሚከፍሉበት ተግባር ብዘዎች እንደሚያምኑት ከቅንነት የመነጨ ይሆናል። ይህን በማድረጋቸው ታማሚዎችን ታድገው፣ ለህክምናም አብቅተው በምስጋና ተመርቀው ይሆናል፡፡

እንዲህ አይነቶቹ ልበ መልካሞች ሁሌም አእምሯቸውና እጃቸው ከክፉ ድርጊቶች የጸዳ ሆኖ ይቀጥላል። በፈጸሙት በጎ ተግባርም መልካምነታቸው ሲከፍላቸው፣ ሲዘክራቸው ይኖራል፡፡ሁሌም ቢሆን እንዲህ አይነቶቹ ደጋጎች ለደግ ስራ አይቦዝኑም፡፡ለመልካም ሥራ አይዘገዩም፡፡

ከዚህ በተቃራኒ ያሉቱ ግን ሁሌም በጥርጣሬ ዓይን የሚስተዋሉ ናቸው። በየጊዜው የሚሰነዝሯቸው የምፅዋት እጆች መልካም ፍሬን አይዙም። ስራቸው ከምርቃት ይልቅ በእርግማን የተዋዛ፣ በጥቅማጥቅም የታሰረ ነው። ዓላማቸው ትርፍን ማጋበስ ነውና ምንይሉኝን አያውቁም፣ ስለሰው መኖርና መሞት ግድ የላቸውም። ስራቸው ገንዘብ እስካስገኘ ድረስ ያለውን ሞቷል፣ የሞተውን ተነስቷል ለማላት አይቸገሩም፡፡

ወዳጆቼ! በየጊዜው የምናስተውለውና የሚያጋጥመን የማጭበርበር ድርጊት መልኩን እየለወጠ በእኛ ላይ መተግበሩ ብርቃችን አልሆነም፡፡ከዚህ አንጻር በየዕለቱ ለሚያጋጥሙን አዳዲስ ድርጊቶች በርካቶቻችን እውነታውን ብንጠራጠር የሚያስፈርድ አይሆንም፡፡

ከሁሉም ግን ከነገሮች ጀርባ የሚደጋገሙትን ተለምዷዊ ድርጊቶች በሁለት ልቦና ማየት፣ መቃኘቱ አይከፋም። እዚህ ላይ «ሁለት እግር አለኝ ተብሎ ከሁለት ዛፍ አይወጣም»ይሉት አባባል ላይሰራ ይችላል። አንዳንዴ በሁለቱም እግር ከሁለት ዛፍ ለመውጣት መሞከሩም ሊያዋጣ ይችላል። «ጠርጥር ከገንፎም ውስጥ አለ ስንጥር» እንዲሉ ነውና ፡፡

# ራስ-ፈለቅ መፍትሔዎችን. . .

ከ5ኛው ገፅ የዞረ

ሁለተኛው ስለሆነ ስለ እርሱ በደንብ እንመልከት።

ይህን አስመልክቶ አቶ ግርማ የጥናታቸው ውጤት በሆነው በመጽሐፋቸው ከገጽ 33 ጀምሮ ሲያብራሩ፤ “በእንቅርት ላይ ጆሮ ደግፍ እንዲሉ ደግሞ ቢንስ ቢያንስ ከአክሱም ስልጣኔ መውደቅ በኋላ አምባገነኑ ሕወሓት/ኢህአዴግ ስልጣን እስከጨበጠበት 1983 ዓ.ም ድረስ በእርስ በእርስ ጦርነት አማካኝነት በትጥቅ ትግል ስልጣን መያዝ ጀግና የሚያሰኝ ባህል ነበር/ነው” ይላሉ።

ይህም ነፍጥንና ጉልበትን መሰረት ያደረገው የመንግስት ሽግግር ፖለቲካ ባህሏ ኢትዮጵያን እጅና እግሯን ተብትቦ ለስልጣኔና ለዕድገት የምታስብበት መተንፈሻ ጊዜ እንኳን እንዳይኖራት አድርጓት ቆይቷል። ምን ያህል ወይም ስንት ዓመታትን? ለሚለው ጥያቄ ትክክለኛ መልስ ለመስጠት እያንዳንዱ የመንግስት ሽግግር ጦርነት ምን ያህል ጊዜ እንደፈጀ አውሮፓውያኑ እንደሚያርጉት አባቶቻችን ጽፈው ያስቀመጡልን ታሪክ የለም።

“...ምን ያህል ስለ ጦርነት እየዘመርንና የጦርነት ነጋሪትን እየጎሰምን አጠቃላይ ግምት ለማግኘት ግን ምርምራችንን እንቀጥል...”። ለጥናቱ እንዲያመቸን ከአፄ ኢዛና(320 ዓ.ም) ለመንግስት ሽግግር(ለስልጣን) የተደረጉትን የእርስ በእርስ ጦርነቶች በሙሉ ከግምት አናስገባም። ለጊዜው ጥናታችንን ይበልጥ ቀላል ለማድረግ ስንል ከአፄ ኢዛና ወዲህ ተሞክረው ያልተሳኩትን ቁጥር ስፍር የሌላቸው የመንግስት ሽግግር ጦርነቶችንም በሙሉ ወደ ጎን እንተዋለን። ጥናታችን ከአፄ ኢዛና ወዲህ በተደረጉትና በተሳኩ የመንግስት ሽግግር ጦርነቶች ላይ ብቻ ያተኩራል።

“በዚህ መልኩ ስናሰላው በ320 ዓ.ም አፄ ኢዛና ከነገሱበት ጊዜ ጀምሮ አምባገነኑ ሕወሓት/ኢህአዴግ ስልጣን እስከያዘበት 1983 ዓ.ም ጊዜ ድረስ በነበሩት 1662 ዓመታት ውስጥ በተደረጉ የተሳኩ የመንግስት ሽግግር ጦርነቶች ሳቢያ በጦርነትና በመገዳደል ላይ የተመሰረተው የመንግስት ሽግግር የፖለቲካ ባህሏ በግምት ከ360 እስከ 400 የሚደርሱ ዓመታትን እንደ እሳት ለብልቦ በልቶ፣ ስልጣኔ ከውስጥም እንዳታበቅል ከውጭም እንዳትቀስም ኢትዮጵያን እጅና እግሯን ተብትቦ፣ ወደ ፊት እንዳትራመድ አስሮ አስቀርቷታል።” በማለት የጥናት ውጤታቸውን ይገልጻሉ ደራሲው። በዚህ ላይ ያልተሳኩት የመንግስት ሽግግር ጦርነቶችና ሀገሪቱ ከውጭ ወራሪዎች ጋር ያደረገቻቸው በርካታ ጦርነቶች ቢቆጠሩ ደግሞ በጦርነት የባከነው ጊዜ በጥቂቱ ከ500 ዓመታት እንደሚበልጥ ያላቸውን ግምትም ያመላክታሉ። አሳዛኝ ነው!

“ትንሽ ሰላም ጊዜና ጥሩ መሪ ተገኝቶ ብልጭ የሚሉ የስልጣኔ ጅማሮዎች ብዙም ሳይቆዩ በስልጣን ሽኩቻ በሚነሱ የእርስ በእርስ ጦርነቶች ይወድማሉ። ሀገሪቱም እንደገና ተመልሳ ብዙ እርምጃ ወደ ኋላ ትሄዳለች” ይህንን የተመራማሪውን ድንቅ ትዝብታዊ ድምዳሜ- የምርም የሚያስደንቅ ጥናታዊ ምልከታ በአዕምሯችሁ እያሰላሰላችሁ ተከተሉኝ።

አዎ! አውዳሚውና ኋታቹ የፖለቲካ ባህላችን እንዲህ ታሪካችንን እያበላሸ እነሆ ዛሬም ተከትሎናል። እንዳለመታደል ሆኖ በረጅሙ አኩሪ ታሪካችን ውስጥ የተሰነቀረው አሳፋሪው የፖለቲካ ባህላችን ከላይ በተገለጸው መንገድ የዕድገታችንና የስልጣኔያችን ዋነኛው ባላንጣ የሆነው ዕድሜ ልካችንን እየተከተለ ኋላ ሲያስቀረን የኖረው አውዳሚው የፖለቲካ ባህላችን ዛሬም የለቀቀን አይመስልም።

“በእንቅርት ላይ ጆሮ ደግፍ” እንደሚባለው ወትሮም በመገዳደልና በጦርነት ላይ የተመሰረተው ኋላ ቀሩ የፖለቲካ ባህላችን ከ1950ዎቹ ጀምሮ ባለፉት ሃምሳ ዓመታት በተለይም ባለፉት ሃያ ሰባት ዓመታት ደግሞ “የብሔር ብሔረሰቦች መብት” በሚል ሽፋን በሌላ አስቀያሚ በሽታ ተመርዞ ህመሙ ተባብሶበታል። እናም ባለፉት ሃያ ሰባት ዓመታት ውስጥ ለጆሮ የሚከብዱ፣ ለሰሚ የሚያርዱ፣ ኢትዮጵያና ኢትዮጵያዊነትን የማይመጥኑ፣ በጥቅሉ እጅግ በጣም የሚዘግኑና የሚያሳፍሩ ኢ ሰብዓዊ ድርጊቶችንና ተዘርዝረው የማያልቁ ሌሎች ታህተ ሰብዕ ክንዋኔዎችንም በየፈርጁ ለማስተናገድና የታሪካችን አካል ለማድረግ ተገድደናል።

ይህም ነፍጥንና ጉልበትን መሰረት ያደረገው የመንግስት ሽግግር ፖለቲካ ባህሏ ኢትዮጵያን እጅና እግሯን ተብትቦ ለስልጣኔና ለዕድገት የምታስብበት መተንፈሻ ጊዜ እንኳን እንዳይኖራት አድርጓት ቆይቷል

ከዚህ ሁሉ የቁልቁለት ዘመን በኋላ ደግሞ በርካታ ዓመታትን በፈጀና አያሌ መስዋዕትነትን ባስከፈለ የሕዝብ ትግል ከሁለት ዓመታት በፊት በተደረገ ጥገናዊ ለውጥ የብዙዎችን ተስፋ ያለመለመ ታሪካዊ ሊባል የሚችል ሀገራዊ ለውጥ መጥቶ ለዘመናት አስሮ ከያዘን ፖለቲካዊ አዙሪት የወጣን መስሎን ብንደሰትም ዳሩ ከለውጡ ማግስት ጀምሮ በቆየው ችግራችን በአዲስ መልክ መፈተናችን አልቀረም።

የፖለቲካ ባህላችን የጥፋት መሰሪነት የገባቸው ጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ “ሀገራዊ አንድነት ማንነታችን እንዳይለያይ ሆኖ የተጋመደ፣ የተሰናሰለና የተዋደደ መሆኑን አመላካች ነው። “የሀገራችን ብሔሮች እጣ ፋንታ በጋራ ለማደግ የተሰራ ብቻ እንጂ ተለያይተን ወይም ተነጣጥለን ሉዓላዊ ሀገር ሆነን፤ የነጠላ ህልውናችንን አስጠብቀን በሰላም መቆየት አንችልም። ሀገራዊ አንድነታችን የምርጫ ብቻ ሳይሆን የህልውና ማስጠበቅ ጉዳይ ጭምር ነው” የሚል መዳኛ መንገድን አመላክተዋል።

ሆኖም ለብሔር ብሔረሰቦች ራስን በራስ የማስተዳደር “መብት” እና ለህዝቦች “እኩልነት” በሚል ሽፋን የራሳቸውን ጥቅም ለማስቀደም በሚታትሩ፣ እነርሱ ብቻ የበላይ ሆነው ለመኖር በሚፈልጉ ጊዜ ያለፈበት “እኔ አውቅልሃለሆች” የሚመራው የድህረ ዋለልኝና መለስ ፖለቲካችን ከእስካሁኑ በባሱ ሁኔታ ሀገሪቱን ከፉኛ ችግር ውስጥ ከቷታል። የፖለቲካችን ፊታውራሪዎች ዛሬም “ጨቋኝ-ተጨቋኝ” የሃሰት ፍረጃ ፖለቲካቸው “ምናባዊ ተጨቋኝ” ፈጥረው የጭቁን ተቆርቋሪ መስለው ለመጨቆን ባላቸው ድብቅ ፍላጎት በለመዱት የጠላትነትና የፍረጃ ትርክታቸው ህዝብን አለያይተው፣ በጠላትነት አቧድነው ተከፋፍሎ የተዳከመ ህዝብን ያለ ተቃውሞ በበላይነት ቀጥቅጦ ለመግዛት አዛኝ መስለው ሕዝብን ለጦርነት በመቀስቀስ ላይ ናቸው።

ለዚህ እኩይ ዓላማቸው መሳካት ያመቻቸው ዘንድም አንድ ጊዜ ለሀገራዊ አንድነት ሌላ ስም በመስጠትና ከእውነታው በተቃራኒ ለቃሉ አሉታዊ ትርጉም በመፈብረክ፣ የራስን በራስ የማስተዳደር መብትን የሚነፍግ፣ ህገ መንግስታዊ ሥርዓቱን የሚንድ፣ ፌደራላዊ ሥርዓቱን የሚያጠፋ፣ ወደ አሀዳዊ ሥርዓት የሚመልስ፣ ብሔር ብሔረሰቦችንም የሚውጥ...ወዘተ የሚሉ የሃሰት ውንጀላዎችን በስፋት ሲያሰራጩ ከርመዋል።

አሁን ላይ ከራሱ ጥቅም ውጭ ሌላውን ለማዳመጥ የማይፈልገው፤ መግባባት እንዳይኖር ሆን ተብሎ በልዩነቶች ላይ ብቻ ተንጠልጥሎ በጥላቻና በጠላትነት ተረክ የሚመራው የጎራ ፖለቲካ ከዕድገት እንቅፋትነት አልፎ የህልውናዋም ስጋት የመሆን ደረጃ ላይ ደርሷል። ይህም “ትንሽ ሰላም ጊዜና ጥሩ መሪ ተገኝቶ ብልጭ የሚሉ የስልጣኔ ጅማሮዎች ብዙም ሳይቆዩ በስልጣን ሽኩቻ በሚነሱ የእርስ በእርስ ጦርነቶች ይወድማሉ። አገሪቱም እንደገና ተመልሳ ብዙ እርምጃ ወደ ኋላ ትሄዳለች” የሚለውን የፖለቲካ ባህላችን ተመራማሪው አባባል ያስታውሰናል።

በብዙ መከራና መስዋእትነት የተገኘውንና ሀገር ትልቅ ተስፋ የጣለችበት ታሪካዊ ለውጥ ወደፊት ከመራመድ ይልቅ ወደኋላ እንዲመለስ መልካም ነገርን በአጭሩ የመቅጨትና ሁልጊዜ በችጋርና በሃዘን ውስጥ መኖርን የለመደው “የቡዳ ፖለቲካችን” በተቃዋሚነት ቆሞ በእጅጉ እየተዋጋው መሆኑን መታዘብ ይቻላል።

በግለሰቦች ምርጫ ሳይሆን በተፈጥሮ አስገዳጅነት ሰዎች ላይ በተጫነ መንጋ አቧድኖ ጎራ ለይቶ ህዝብን ወደ እርስበእርስ ጦርነት ለማስገባት ላይ ታች እያለ የሚገኘው ከለውጡ ማግስት ጀምሮ በስፋት ሲሰራ የቆየው ይህ ከፍተኛ የጥፋት አጀንዳ በርካታ ማባባያዎች ቢደረጉለትም እጅጉን እየባሰበት ሄዷል። ምክንያቱም ኋላ ቀሩን የመጠፋፋትና የሴራ ፖለቲካ የሚያራምዱ ወገኖች ነጻነትን እንደ ልብ ተንቀሳቅሰው፣ ሃሳባቸውን በነጻ ገልጸው፣ በሃሳብ አሸንፈው የበለጠ ነጻነትንና ዲሞክራሲን ለማምጣት ሳይሆን እየታገሉበት ያለው ያለ ምንም ገደብ የራሳቸውን ርካሽ የፖለቲካ ትርፍ ለማጋበስ ነውና። ያለ ምንም ገደብ አፍራሽ ሃሳባቸውን ለማስፋፋትና በህዝብ ስም የራሳቸውን ጥቅም ለማሳካት ነው ነጻነትን እየተጠቀሙበት ያለው።

በዚህም ያለ ማንም ከልካይ ጥላቻን ይሰብካሉ፣ ህዝብን በህዝብ፣ ሃይማኖትን በሃይማኖት፣ እንዲሁም ህዝብን በመንግስት፣ መንግስትን በህዝብ ላይ ያነሳሳሉ። ከዚህ ድርጊታቸው እንዲታቀቡ ሲነገራቸው “ነጻነታችንን ተገደብን” በማለት ከሳሽ ሆነው ይቀርባሉ። እናም በእኔ ዕይታ ለውጡ ከመጣ ወዲህ እስካሁን ድረስ ባሉት አራት ዓመታት በሀገሪቱ ውስጥ ለተፈጠሩትና እየተፈጠሩ ላሉት ችግሮች ሁሉ ዋነኞቹ ተጠያቂዎች በነጻነት ስም ወንጀል እየፈጸሙ በነጻነት እየኖሩ ያሉት እኒሁ የፖለቲካ ነጋዴዎች ናቸው። በዚህም ለውጡ ያመጣውን ነጻነት በመጠቀም ሀገርን ለማፍረስ በግልጽ ከመፎከር የሀገርን ህልውና አደጋ ላይ እስከጣለ አሳዛኝ ጦርነትና መከራ በሀገር ላይ ተፈጽሟል።

ይህ እንግዲህ በብልሹው የፖለቲካ ባህላችን ምክንያት የተፈጠረ እና ህልውናችን ላይ የተደቀነ ፈታኝ ችግር ነው። ወደድንም ጠላንም ችግሩ የውጭ ወራሪ ጠላት የፈጠረው ሳይሆን ከላይ ለማመላከት እንደሞከርነው በረጅሙ አኩሪ ታሪካችን መሃል ሲወርድ ሲዋረድ ተከትሎን የመጣ አዋራጅ የታሪካችን ክፍል ነው። እናም የራሳችንን ችግር መፍታት የምንችለው እኛው ራሳችን እንጂ ማንም ሊፈታልን አይችልም።

በመሆኑም የራስን ችግር ለመፍታት ከራሳችን በመጣ ተነሳሽነት ከምስረታው የአፍሪካውያንን ችግር በአፍሪካውያን እስከሚለው ራስ-ፈለቅ መፍትሔ የእኛው የራሳችን በሆነው የአፍሪካ ኅብረት አማካኝነት ችግሩን ለመፍታት እየሄድንበት ያለው መንገድ በረጅሙ ታሪካችን ውስጥ ለዘመናት የራሳችንን ችግር በራሳችን ስንፈታ የኖርንበት አንዱ የታሪካችን አኩሪ ዕሴት እንደመሆኑ መጠን ይበል የሚያሰኝ በመሆኑ ዳር ሊደርስ ይገባል።

ይህ ከሆነ ዘንዳ አስራ አንድ ዓመታት በፊት በራሳችን እጆች ተጽፎ ከሁለት ዓመት ተኩል በፊት ኅዳር 2012 ዓ.ም ላይ ቀርቦ የነበረውን ድንቅ አገር በቀል ችግር ፈች ፕሮጀክትም በማስታወስ “የት ደረሰ” ብለን ለመጠየቅ እንገደዳለን። ምክንያቱም በመግቢያችን ላይ እንዳመለከትነው አንድ ችግር በትክክል እንዲፈታ ከተፈለገ መጀመሪያ የችግሩ ዋነኛ መንስኤ ተለይቶ መታወቅ ያለበት ሲሆን “ኢትዮጵያ ከሁሉ ቀድማ ሰልጥና በዕድገት ወደ ኋላ የቀረችበት ዋነኛ ምክንያት በመጠላለፍና በመጠፋፋት ላይ የተመሰረተው የክፍፍል ፖለቲካ ባህሏ መሆኑን አውቆ ችግሩን ከሥሩ ለመፍታት አልሞ የተነሳ ፕሮጀክት በመሆኑ ነው።

ፕሮጀክቱ ሀገራችንን አስሮ ይዞ ለዘመናት ወደ ኋላ ላስቀረን ለዚህ አሳሳቢ ችግር ዋነኛው መፍትሔም “የዛሬን ችግሮች በውይይትና በመቀራረብ በመፍታት የነገ የጋራ መጻኢ ዕድልን በጋራ መገንባት” መሆኑንም አመላክቷል። በጣም በሚያስደንቅ ሁኔታም በፌደራል መንግስቱና በትግራይ ክልል መካከል የተፈጠረውን ችግርና ሊያስከትል የሚችለውን ከባድ ውድመትም አስቀድሞ በትክክል ተንብዮ የነበረም ድንቅ ፕሮጀክትም ነው።

ከተጀመረው የሰላም መፍትሔ ጎን ለጎን ችግሩን በዘላቂነት ለመፍታት “የምንፈልጋት ኢትዮጵያ” ፕሮጀክትም ጥቅም ላይ እንዲውል አበክሬ እጠይቃለሁ! እናም እንዲህ ዓይነቶችን ሀገር በቀል የችግር መፍቻ ዕሴቶችና መፍትሔዎችን በመጠቀም የራሳችንን ችግር መፍታትና ከራሳችን ጋር መታረቅ ይገባናል በማለት የዛሬውን ምልከታዬን በዚሁ አጠናቀቅሁ። መልካሙን ሁሉ ለሀገራችን ያድርግልን!

# የግብርናው ዘርፍ ከመዋቅራዊ ሽግግር አኳያ

**ስምስም መንግሥቱ**

የስምጥ ሸለቆ አካባቢዎችን መሠረት አድርጎ የዛሬ አራት አመት በሶስት ሺ 500 ሄክታር መሬት ላይ የተጀመረው ሀገራዊ የስንዴ ልማት አካል የሆነው የበጋ ስንዴ መስኖ ልማት ተጠናክሮ ቀጥሏል፤ ባለፈው የምርት ዘመን በበጋ መስኖ ስንዴ ልማት የተሸፈነው ማሳ ከ600 ሺ በላይ ሄክታር የደረሰ ሲሆን፣ በተያዘው 2015 በጀት አመት ይህ አሀዝ ከአንድ ሚሊየን ሄክታር በላይ እንደሚደርስ የግብርና ሚኒስቴር መረጃዎች ይጠቁማሉ።

የሀገራዊ ስንዴ ልማቱ አላማ የሀገር ውስጥ የስንዴ ፍላጎትን ማሟላትን፣ በግዥ ከውጭ የሚገባውን ስንዴ በሀገር ውስጥ መተካትን፣ ስንዴ ለወጪ ገበያ በመላክ የውጭ ምንዛሬ ማግኘትን ታሳቢ ያደረገ ሲሆን፣ በተከናወነው ተግባርም በመኸር ወቅት በስንዴ ዘር የሚሸፈነው ማሳ ብዛትም የሚገኘው ምርትም እየጨመረ ይገኛል።

በበጋ መስኖ ስንዴ ልማት በ2013/14 የምርት ዘመን ከ600ሚሊየን ሄክታር በሚበልጥ ማሳ ላይ ስንዴ በመዝራት 26 ሚሊየን ኩንታል ስንዴ ማግኘት ተችሏል፤ በ2015 የበጋ ወቅት ደግሞ ከአንድ ሚሊየን ሄክታር በላይ መሬት በማልማት 52 ሚሊየን ኩንታል ስንዴ ለማግኘት ታቅዶ እየተሰራ ይገኛል።

የግብርና ስራውን ከተበጣጠሰ ማሳ ወደ ኩታ ገጠም ማሳ በመቀየር በቴክኖሎጂ አጠቃቀምና በመሳሰሉት ላይ ለውጥ ማምጣት እየታቸለ ሲሆን፣ በሜካናይዜሽን በኩልም በትራክተር፣ በኮምባይነር የመጠቀሙ ሁኔታ፣ ለመስኖ አገልግሎት የሚውሉ የውሃ መሳቢያ ሞተሮች አቅርቦትና እየጨመረ ይገኛል።

በግብርናው ዘርፍ በስንዴ ልማት፣ በሜካናይዜሽን፣ በኩታ ገጠም እርሻ ማስፋፋትና በመሳሰሉት እየታዩ ያሉት ለውጦች ከግብርናው ዘርፍ መዋቅራዊ ሽግግር/ ትራንስፎርሜሽን/ አንጻርስ እንዴት ይታያሉ? ለግብርናው ዘርፍ መዋቅራዊ ሽግግር እውን መሆን ምን ምን ነገሮች ያስፈልጋሉ? ሽግግሩስ በምን መልኩ ሊገለጽ ይችላል?

በቅርቡ ዋልታ ያነጋገራቸው የኢትዮጵያ ግብርና ባለሥልጣን ምክትል ዳይሬክተር ሀሚድ ጀማል፤ በግብርናው ዘርፍ መዋቅራዊ ሽግግርን (ትራንስፎርሜሽን) ማሳየት የሚቻለው በዘርፉ በሚካሄደው ምርትና ምርታማነትን የማሳደግ ስራ፣ ግብርናው ከሀገር ውስጥ ፍጆታ ባለፈ ለውጪ ገበያ ማቅረብ ሲችል ጭምር መሆኑን ገልጸዋል፡፡

የግብርናው ዘርፍ በኢትዮጵያ መዋቅራዊ ለውጥ እንዲያመጣ በበሬ ጫንቃ የሚከናወነው ግብርና በሜካናይዜሽን ተተክቶ ልማቱ በስፋት መከናወንና በበጋ ጭምርም መሥራት ሲቻል መሆኑን ያመለክታሉ። በተበጣጠሰ መሬት ላይ ይከናወን የነበረን ልማት ኩታገጠም (ክላስተር) የስንዴ ልማት በማካሄድ ውጤታማነቱን ማሳየት መቻሉንም አመልክተዋል።

በኢትዮጵያ እየተከናወነ ያለው የግብርና ልማት ገበያ ተኮር መሆኑንም ምክትል ዋና ዳይሬክተሩ ጠቅሰዋል። አብዛኞዎቹ የአፍሪካ ሀገራት ስንዴን ከውጭ እንደሚገዙም ተናግረው፣ ይህም ለኢትዮጵያ የገበያ መዳረሻ በመሆን ሊያገለግል እንደሚችል ይናገራሉ። ሀገሪቱ ገበያዋን ወደ ጎረቤት ሀገሮች በማስፋት ተጠቃሚነቷን ማሳደግ እንደምትችል፣ የስንዴ ልማቱ ለሌሎችም የሰብል ልማቶች ልምድ የሚቀሰምበት መሆኑን ይገልጻሉ።

የኢትዮጵያ ግብርና ትራንስፎርሜሽን ኢንስቲትዩት ምክትል ዋና ዳይሬክተር አቶ ይፍሩ ታፈሰ በተለይ ለአዲስ ዘመን ጋዜጣ ፤ የግብርናው ድርሻ በአብዛኛው በሌሎች ዘርፎች እየተተካ መጥቷል ሲሉ ይገልጻሉ። በሀገር ውስጥ አጠቃላይ ምርት ውስጥ የግብርናው ድርሻ ሲታይ ወደ31 በመቶ ወርዷል ያሉት አቶ ይፍሩ፣ ከ20 አመት በፊት 50 በመቶ ገደማ የነበረው በአጠቃላይ የሀገር ውስጥ ምርት ግብርና የነበረው ድርሻ ቀንሷል። አሁን ወደ አገልግሎቱ፣ ኢንዱስትሪው እየሄደ መሆኑን የግብርናው ሚና እየታየ መጥቷል ሲሉ ያብራራሉ፡፡

እንደ እሳቸው ገለጻ፤ አጠቃላይ ሀገራዊ ምርት የሚለካው በግብርና፣በኢንዱስትሪና በአገልግሎት ዘርፎች ነው። የሶስቱ ድርሻ እየተሸጋሸገና አንዱ ሌላውን እየተካው ሲሄድ በመቶኛ ነው ድርሻቸው የሚገለጸው። ለአብነት በአሜሪካ የግብርና ድርሻ ሶስት በመቶ ብቻ ነው። ሌላው የአገልግሎትና የኢንዱስትሪው ድርሻ ነው።

ሽግግር የሚመጣው የግብርናው ድርሻ እያነሰና በኢንዱስትሪው፣በአገልግሎቱ ሲተካ ነው ያሉት ምክትል ዋና ዳይሬክተሩ፣ ከዚህ አንጻር በኢትዮጵያ ተጨባጭ ሁኔታ ግብርናው ጥሩ በሚባል ደረጃ ላይ ደርሷል እንጂ መዋቅራዊ ሽግግር ግን አላካሄደም ወይም ትራንስፎርም አልሆነም ሲሉ አቶ ይፍሩ ይናገራሉ።

የግብርና መዋቅራዊ ሽግግሩን ለማምጣት ምርታማነትን የሚያቀላጥፉ ሥራዎች መሰራት አለባቸው ያሉት አቶ ይፍሩ፤ በባህላዊው የአስተራረስ ዘዴ ቀናት የሚወስደው ሥራ በሜካናይዜሽን ከታገዘ በሰአት ውስጥ ማጠናቀቅ እንደሚቻል ይናገራሉ፤ ይህ ሲሆን በኋላቀር የአስተራረስ ዘዴ የሚባክነውን የሰው ኃይል ወደ ኢንዱስትሪውና ሌላ የሥራ ዘርፍ እንዲሰማራ ማድረግ እንደሚቻል አመልክተዋል፡፡

እንደ እርሳቸው ገለጻ፤ አርሶ አደሩ ልጁን ትምህርት ቤት በመላኩና በተለያየ ምክንያት እያጋጠመው የመጣውን የሰው ኃይል ችግር መፍታት የሚቻለው ግብርናው በሜካናይዜሽን ታግዞ ሲሰራ ነው። ግብርናው ሲዘምን የመሥራት ፍላጎትም ይነሳሳል።

በሀገሪቱ እንደ ማረሻ፣ምርት መሰብሰቢያ፣መውቂያ የመሳሰሉት የግብርና ሜካናይዜሽን አቅርቦት ዝቅተኛ በመሆኑ፣ የኢትዮጵያ የግብርና ሥራ በሬ ጠምዶ ከማረስ አልተላቀቀም። በምርጥ ዘር አቅርቦትና በቴክኖሎጂ አጠቃቀም ትልቅ ሥራ ተሰርቷል የሚባለው የበጋ መስኖ ልማት ከተጀመረ ወዲህ ባለው እንቅስቃሴ ነው።

በሌሎች ሰብሎች ልማትም በቆሎ ላይ የተሻለ ሲሆን፣በምርጥ ዘር አቅርቦትም ጭምር መልካም የሚባል ውጤት ተመዝግቧል። ጤፍን ጨምሮ በሌሎች ሰብሎች የተሻለ ውጤት ለማስመዝገብ ምርጥ ዘር፣ ማዳበሪያ፣ ፀረተባይና ሌሎችንም ግብአቶች እንዲሁም በሜካናይዝሽን አቅርቦት ላይ ጠንካራ ሥራ ይጠበቃል።

በተበጣጠሰ የአርሶ አደር መሬት ላይ የሚከናወን ልማት የትም አይደረሰም። አርሶ አደሩ መሬቱ የኔ ነው የሚል አስተሳሰብ ስለሚኖረው በውጤታማነቱ ላይ አሉታዊ ተጽእኖ መኖሩ አይቀርም ያሉት አቶ ይፍሩ፣ በሰፊ መሬት ላይ ማልማት ወይንም ኮሜርሻላዝ ማድረግ እንዲሁም ጠፍ መሬትን ለልማት ምቹ በማድረግ የግሉን ዘርፍ በግብርናው ዘርፍ ማሳተፍ ይጠበቃል። ይህ ሲሆን፣ የግብርናው መዋቅራዊ ሽግግር ወይንም ትራንስፎርሜሽን እውን ይሆናል ሲሉ ያመለክታሉ፡፡

አቶ ይፍሩ ይህን ሁሉ ለመፈጸም ዘርፉን ከሚመራው አካል ብዙ ሥራ ይጠበቃል ሲሉም አስገንዝበዋል። ለአብነት የኢትዮጵያ ግብርና ትራንስፎርሜሽን ኢንስቲትዩት ተመራማሪዎች በምርምር ምርጥ ዘር በስፋት እንዲያወጡ የገንዘብና የባለሙያ ድጋፍ ያደርጋል። በምርምር የተገኘው ዘር ጥቅም ላይ እንዲውልም አርሶ አደሩ መንደር በመሄድ ስለአጠቃቀሙ የማሳየትና የማላመድ እንዲሁም የማነቃቃት ሥራ ይሰራል። ከአመት በፊት በምርምር የወጡ የተሻሻሉ ቦራና እና ቦሰት የተባሉ የጤፍ ዝርያዎች ምንጃር አካባቢ ለሚገኙ አርሶ አደሮች በግላቸው ለሙከራ ሰጥተው ለአካባቢው ሥነምህዳር ተስማሚ ሆኖ የተገኘውና በአርሶ አደሩም የተመረጠው የቦራ ዝርያ ያለው ጤፍ መሆኑን መረዳት ተችሏል ሲሉ አብራርተዋል፡፡

ኢንስቲትዩቱ ለምግብ ፍጆታና ለፋብሪካ ግብአት ቅድሚያ በሚሰጣቸው ላይ ትኩረት በማድረግ በምርጥ ዘር አቅርቦት በአስር የሰብል አይነቶች ላይ ድጋፍ እያደረገ መሆኑን ጠቅሰው፣ ከእነዚህም መካከል ጤፍ፣ ስንዴ፣ የቢራ ገብስ፣ በቆሎ፣ ሰሊጥ፣ አኩሪ አተር እንደሚጠቀሱ ያመለክታሉ። በተመሳሳይ በአትክልትና ፍራፍሬ አቮካዶ፣ ማንጎ፣ ሙዝ፣ቲማቲም ዝርያዎች ላይ ድጋፍ አድርጓል ይላሉ። ኢንስቲትዩቱ የአምስት አመት እቅድ ነድፎ ወደ ሥራ ከገባ ሁለት አመታት ተቆጥረዋል ያሉት አቶ ይፍሩ፣ ሥራውን ለማጠናከር ደግሞ ‹‹ቴን ኢን ቴን››የሚል የአስር አመት እቅድ ቀርጿል ብለዋል፡፡

አዳዲስ ዝርያዎች ላይ ትኩረት ማድረግ ነባር ዝርያዎች እንዲዘነጉ አያደርግም ወይ? በሚል ለተነሳላቸው ጥያቄ በሰጡት ምላሽም አንዴ ከተለመደ ነገር የመውጣት ችግር ካልሆነ በስተቀር ምርታማ ለመሆንና የአርሶ አደሩም ኑሮ እንዲሻሻል ለተያዘው ሥራ አማራጮችን መፈለግ እንጂ በነበረ ነገር መቀጠል አዋጭ እንደማይሆን ገልጸዋል። በተሻሻሉ ዝርያዎች እንደ ስጋት የሚነሳው የበሽታ አለመቋቋምን በተመለከተ መፍትሄም አብሮ የሚዘጋጅ መሆኑና አሳሳቢ እንዳልሆነም ተናግረዋል።

የምርምር ብቃትን እያሳደጉ ተለዋዋጭ የሆነውን በሽታ መቋቋም እንደሚያስፈልግም ጠቁመዋል፡፡ነባር ዝርያዎችም እንዳይጠፉ ተገቢው ጥበቃ እንደሚደረግና እየተደረገ መሆኑንም ገልጸዋል፡፡

የአፍሪካ ግብርናን ትራንስፎርም ለማድረግ የሚያስችል የፖሊሲ አቅጣጫዎችን በመጠቆም፣መልካም የሆኑ የቴክኖሎጂ ተሞክሮዎች ከአንዱ ወደሌላው እንዲሸጋገሩ፣ተመራማሪዎች በዘርፉ የምርምር ሥራ እንዲሰሩና ለምርምር ሥራ እገዛ በማድረግ፣ቴክኖሎጂዎች እንዲመቻቹና በሌሎችም የሀገራቱን አቅም በመፍጠር እየደገፈ የሚገኘው አግራ የተባለ ዓለምአቀፍ ድርጅትም በኢትዮጵያ በግብርና ማምጣት ለሚፈለገው መዋቅራዊ ሽግግር ስራ ድጋፍ እያደረገ ይገኛል፡፡

ዶክተር ጥላሁን አመዴ በዚህ ተቋም ውስጥ ይሰራሉ። እርሳቸው ከሚሰሩባቸው 15 ሀገራት መካከል ፈጣን የግብርና ልማት የሚታየው በኢትዮጵያ ውስጥ እንደሆነ ዶክተር ጥላሁን ይጠቅሳሉ። በሀገሪቱ አነስተኛ ምርት የሚታይበት ሰብል እንዳለም ተናግረው፣ በእጥፍ እድገት ያስመዘቡ የሰብል አይነቶች መኖራቸውንም ነው የጠቆሙት። አጠቃላይ ምርት መጨመሩንም ጠቅሰው፣ በኢትዮጵያ የምግብ ዋስትናን የማረጋገጥ ጥያቄ ግን ገና ምላሽ እንዳላገኘ አስታውቀዋል።

ይሄ የሆነው በሁለት ምክንያቶች ነው ሲሉም ዶክተር ጥላሁን ይጠቁማሉ። አንዱ ምርት ያደገው በመኸር በሚከናወን የግብርና ሥራ መሆኑን ይገልጻሉ። በአየር መዛባት ዝናብ በወቅቱ ባለመገኘቱ፣ የአየር ለውጡንም አርሶ አደሩ ባለመገንዘቡ በተፈጠሩ ምክንያቶች በበልግ በኢትዮጵያ ውስጥ እስከ 30 በመቶ ይገኝ የነበረው ምርት ቀንሷል ሲሉም አብራርተው፣ በዚህ ምክንያት የምግብ ዋስትና ማረጋገጥ ላይ መድረስ አልተቻለም ሲሉ አስታውቀዋል፡፡

የአፈር ልማትና የአካባቢ ጥበቃ እንዲሁም የውሃ ሀብቱን በአግባቡ መጠበቅ ሌላው የትኩረት አቅጣጫ መሆን እንዳለበትም ዶክተር ጥላሁን ተናግረዋል። በዝናብ ከሚመረተው የበለጠ በመስኖ የሚለማው ውጤታማ እንደሆነ የሌሎች ሀገሮች ተሞክሮ እንደሚያሳይም አመልክተው፣ ይህ የሚሆነው በመስኖ የሚከናወን ልማትን መቆጣጠርና አስፈላጊ የተባሉ ግብአቶችንም ማቅረብ ስለሚቻል እንደሆነ ጠቁመዋል።

ዝናብ ጠብቆ የሚከናወን የግብርና ሥራ ከቁጥጥር ውጭ የሚሆንባቸው አጋጣሚዎች የበዙበትና ስጋት የተሞላበት መሆኑን ይናገራሉ። በኢትዮጵያ የበጋ መስኖ ስንዴ ልማት ጥሩ ማሳያ ቢሆንም ሥራው ገና በሚባል ደረጃ ላይ ነው ያለው ይላሉ። ልማቱ በመኸር ልማት ላይ በሚሳተፍ የኤክስቴንሽን ባለሙያ እየተመራ መሆኑንም ጠቅሰው፣ በመስኖ በኩል የተለየ አቅም መገንባት እንደሚያስፈልግ አስገንዝበዋል። አመራረቱም ገበያው በሚፈልገውና አርሶ አደሩ ለማምረት ፍላጎት ባደረበት ላይ መመስረት እንደሚኖርበትም ያመለክታሉ፡፡

ዶክተር ጥላሁን የግብይት ፋይዳም ያነሳሉ። አርሶ አደሩ ምርቱን በፈለገ ጊዜ እንዲሸጥ የምርት ማከማቻ መጋዘን ሊመቻችለት እንደሚገባ፣ እሴት የተጨመረበት ምርትም እንዲያመርት መበረታታት እንዳለበት ጠቁመው፣ በአጠቃላይ የልማቱን አማራጭ ለአርሶ አደሩ መተውና ገበያው እንዲመራው ማድረግ ይገባል፣ ግብርናውን የሚያግዝ ፋይናንስ(የገንዘብ አቅም) መኖር አለበት ሲሉም ያስገነዝባሉ፡፡

አርሶ አደሩ የገንዘብ አቅም ሲኖረው ቴክኖሎጂን ቶሎ ለመቀበልና፣ ለመጠቀም፣ ወደ ኢንቨስትመንት ለማደግ እድል ይፈጥርለታል ያሉት ዶክተር ጥላሁን፣ እነዚህ ሁሉ ሲከናወኑ ነው የግብርና ትራንስፎርሜሽንን ማምጣት የሚቻለው ሲሉ ገልጸዋል።

እሳቸው የሚሰሩበት ተቋም በዘርፉ ልምድ ያላቸው ኢትዮጵያውያን ምሁራን መንግሥትን በፖሊሲና በተለያየ መንገድ እንዲረዱ በማድረግ፣አርሶ አደሩ እጅ የሚገኙ 30 እና 40 አመታት ያስቆጠሩ ዝርያዎች እንዴት ይተኩ በሚሉና ተያያዥ ጉዳዮች ላይ በተለያየ መንገድ እያገዘ ይገኛል ብለዋል።

የግብርና ሜካናይዜሽን በመንግሥት ብቻ ማሟላት እንደማይቻልም አመልክተው፤ በግብርናው ላይ የግሉ ዘርፍ መግባት አለበት ይላሉ። መንግሥት የሜካናይዜሽን ማሽነሪዎች ከቀረጥ ነፃ እንዲገቡ በተለያየ ማበረታቻ ሊያግዝ እንደሚገባ ገልጸው፣ የመንግሥት ሥራ መሆን ያለበት አገልግሎቱን መቆጣጠር ብቻ እንደሆነም ጠቁመዋል፡፡

ከ2003 ዓ.ም አንስቶ ተግባራዊ በተደረጉት በሁለቱ የእድገትና ትራንስፎርሜሽን እቅዶች በግብርናው ዘርፍ መዋቅራዊ ሽግግር ለማምጣት ጥረት ቢደረግም የተባለውን ሽግግር ግን እውን ማድረግ ሳይቻል መቅረቱ ይታወቃል።



የስንዴ ልማቱ በኩታ ገጠም ማሳዎችና በሜካናይዜሽን ድጋፍ እየተከናወነ ይገኛል

ማህበራዊ

# አስኳላ

# ‹‹ፕሌይ ማተርስ›› የተማሪዎች ተስፋ

**አስናቀ ፀጋዬ**

ናትናኤል ከፍያለው በአየር ጤና ሁለተኛ ደረጃና መሰናዶ ትምህርት ቤት የ12ኛ ክፍል ተማሪ የነበረ ሲሆን፤ የከፍተኛ ትምህርት ተቋም ፈተና ወስዶ ውጤት እየተጠባበቀ ይገኛል። የአዲስ አበባ ከተማ ህፃናት ፓርላማ አባልም ሆኖ ሲሰራ ቆይቷል።

ቀደም ሲል እርሱ ሲማር በነበረበት ወቅት በአብዛኛው የመማር ማስተማር ሂደቱ መምህራን ተኮር ነበር። በእርሱ ጊዜ ከተማሪው ይልቅ የመምህራኑ ሚና ይጎላል። ትምህርቱ አብዛኛው የሚሰጠውም አስተማሪው በፈለገው መንገድ እንጂ በተማሪው ፍላጎት አይደለም። እርሱም በዚሁ የማስተማር ስልት ትምህርቱን ለዓመታት ሲከታተል ቆይቷል።

መምህራን በጨዋታ መልክና ተማሪ ተኮር የማስተማር ስነ-ዘዴን በመከተል ትምህርትን ለተማሪዎቻቸው ባለመስጠታቸው በተማሪ ናትናኤል የትምህርት አቀባበል ላይ እምብዛም ችግር አልተፈጠረም። ምክንያቱም ተማሪ ናትናኤል ሊገጠመው የሚችለውን ችግርም በራሱ ጥረት ለማለፍ ሞክሯል። እንዲያውም እርሱ የህፃናት ፓርላማ አባልና የክፍል ተወካይ በመሆኑ ትምህርት አሰጣጡ እንዲስተካከል አስተማሪዎችን የመጠየቅ እድሉ ነበረው።

ከዚህ በተቃራኒ ከእርሱ ጋር ሲማሩ የነበሩ አብዛኛዎቹ ተማሪዎች በተለመደው የአስተማሪ ተኮር የማስተማር ስነ- ዘዴ ብዙም ተጠቃሚ አልነበሩም። መማር ማስተማሩ ተማሪዎችን ያሳተፈ አልነበረምናም በብዙ ተማሪዎች ውጤት ላይ አሉታዊ ተፅእኖ አሳድሯል።

‹‹በቀጣይም ወደ ዩኒቨርሲቲ ስገባ ተመሳሳይ የማስተማር ስነዘዴ ይገጥመኛል የሚል ስጋት አለኝ›› የሚለው ተማሪ ናትናኤል፤ ይህ ሁኔታ ከቀጠለ እኔን ጨምሮ ሌሎች ተማሪዎች በቀጣይ ምን አልባት ችግሮች ሊያጋጥሙን ይችሉ ይሆናል። እናም የዩኒቨርሲቲ መምህራን ከቀደመው የተሻለና ተማሪን ያሳተፈ የማስተማር ስነዘዴን ቢከተሉልን ሲል ሀሳቡን ያስቀምጣል። ለዚህም መምህራን ከተማሪዎቻውም ጭምር ሃሳብ መውሰድ እንደሚገባቸው ይጠቅሳል።

ተማሪ ናትናኤል አባል ሆኖ የሚሰራበት የአዲስ አበባ ከተማ የህፃናት ፓርላማ ድምፅ ለሌላቸው ህፃናት ድምፅ ሆኖ ያገለግላል። በተለይ ደግሞ በተለያየ መልኩ የጉልበት ብዝበዛ ለሚደርስባቸውና ትምህርታቸውን ለመከታተል ችግር ለሚገጥማቸው ህፃናት ወኪል ሆኖ ይሰራል። ህፃናት መብታቸውንና ግዴታቸውን በእኩል መንገድ እንዲያስኬዱም በተለያየ መልኩ ስራዎችን ያከናውናል። ተማሪ ተኮር የማስተማር ስነ-ዘዴ ተግባራዊነትም ፓርላማው በትኩረት የሚያየው ጉዳይ ነው።

ከተለመደው መምህር ተኮር የማስተማር ስነ-ዘዴ ለመውጣት ‹‹ፕሌይ ማተርስ›› የተሰኘ ጨዋታንና ተማሪን መሰረት ያደረገ የማስተማር ስነ-ዘዴ ፕሮጀክት በኢትዮጵያ በአራት ክልሎች ውስጥ ማለትም በጋምቤላ፣ ቤኒሻንጉል ጉሙዝ፣ አፋርና ሱማሌ በሚገኙ የስደተኞች መጠለያ ጣቢያዎች እ.ኤ.አ በ2020 ይፋ ሆኗል።

ፕሮጀክቱም በስደተኛ መጠለያ ጣቢያዎች ውስጥ የሚገኙ እድሜያቸው ከሦስት እስከ 12 እና ከዚያ በላይ የሆኑ ስደተኞችንና ስደት ተቀባይ ማህበረሰብ ልጆችን ተጠቃሚ አድርጓል። በኢንተርናሽናል ሬስኪዩ ኮሚቴ፣ዋር ቻይልድ፣ ፕላን ኢንተርናልና ሌሎች ግብረሰናይ ድርጅቶች ሲደገፍም ቆይቷል።

ይህ ፕሮጀክት ኢትዮጵያን ጨምሮ በታንዛኒያና ዩጋንዳ የስደተኞች መጠለያ ጣቢያዎች የሚገኙ ከ800 ሺህ በላይ የሚሆኑ ስደተኞችንና የስደት ተቀባይ ማህበረሰብ ልጆችን ተጠቃሚ የሚያደርግ መሆኑም ተነግሯል። ይህንኑ ፕሮጀክት በተለያዩ የሀገሪቱ ትምህርት ቤቶች ለማስፋትና በተለያዩ ችግሮች ምክንያት ከትምህርት ገበታቸው ለተፈናቀሉ ተማሪዎች ተደራሽ ለማድረግ ብሎም በአዲሱ ስርአተ ትምህርት ውስጥ ለማካተት ሥራዎች እየተከናወኑ ይገኛሉ።

በትምህርት ሚኒስቴር የመምህራንና ትምህርት አመራሮች መሪ ስራ አስፈፃሚ ዶክተር ሙሉቀን



ወይዘሮ አለሚቱ ኡሙድ



ተማሪ ናትናኤል ከፍያለው፤

ንጋቱ እንደሚሉት፤ ፕሌይ ማተርስ ፕሮጀክት ተማሪ ተኮር የማስተማር ስነዘዴን በመጠቀም የስደተኞችንና የተቀባይ ማህበረሰቡን ልጆች አጠቃላይ ትምህርትን፣ ደህንነትንና እድገትን ለማሻሻል ተሰናድቷል። ፕሮጀክቱ በዋናነት በትምህርት ላይ በተለይ ደግሞ መምህራንና ህፃናት ላይ አተኩሮ ይሰራል። ዋነኛ ዓላማውም በጨዋታ መልክ የማስተማር ስነዘዴ ህፃናት ትምህርታቸውን እንዲከታተሉ ማስቻል ነው።

የማስተማር ስነ- ዘዴው በኢትዮጵያ በቅድመ መደበኛ ትምህርትና የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ላይ ተማሪን ማእከል ከሚያደርገው የትምህርት ስርአት ጋር አብሮ የሚጣጣም ነው። ስለዚህም በአዲሱ ስርአተ ትምህርት ተካቶ እንዲሰራበት በተለያዩ ደረጃዎች ውይይቶች እየተካሄዱ ይገኛሉ።

መንግስትም የመምህራን ተማሪ ተኮር የማስተማር ስነ ዘዴን የመጠቀም አቅማቸውን ለማሻሻል በአገልግሎት ላይ ላሉ መምህራን የቅድመ አገልግሎት ስልጠና እና ቀጣይነት ያለው የሙያ ማጎልበቻ ስልጠና እድሎችን የማመቻቸት ሥራ እያከናወነ ይገኛል። ይህም በተለይ ልጆችን ያማከለ ቴክኒኮችን በመጠቀም ትምህርቶችን በብቃት ለማድረስ የሚያስፈልጉ ዝቅተኛ የትምህርት ደራጃ ፣ስልጠናና የማስተማር ስነ-ዘዴ እውቀት ለሌላቸው በስደተኞች መጠለያ ጣቢያዎች አካባቢ ላሉ መምህራን ጠቃሚ እንደሚሆን ተረጋግጧል።

እንደ ሥራ አስፈፃሚው ገለፃ፤ የፕሌይ ማተርስ አካሄድ ስልታዊና ተቋማዊ እንዲሆን ለማድረግ ፕሮጀክቱ እየተተገበረ ባለበት አራት ክልሎች ትግበራ ላይ ባለው በተከታታይ የመምህራን ሙያ ማሻሻያ ፕሮግራም ውስጥ በመምህራን ልማት መርሃግብር፣ በመንግስት ተከታታይ ሙያዊ ልማት ማእቀፍ ውስጥ ተማሪ ተኮር ማስተማር ስነዘዴ ማካተት የሚቻልበትን እድሎች ይቃኛል።

የስደተኞችና ከስደት ተመላሾች አገልግሎት ምክትል ዋና ዳይሬክተር አቶ ሙሉአለም ደስታ እንዲሚናገሩት፤ ፕሮጀክቱ ተግባራዊ በሚደረግባቸው ቦታዎች ላይ ስደተኞችን ተቀብለው የሚያስተዳድሩት ክልሎች ናቸው። መንግስትም የአካታችነት መርህን በመከተል ስደተኞች ከአካባቢው ስደት ተቀባይ ማህበረሰብ ጋር ተቀላቅለው ትምህርታቸውን እንዲከታተሉ ያደርጋል። እየተደረገም ይገኛል።

በዚህ ሂደት ታዲያ በርካታ ውጣውረዶች አጋጥመዋል። ለአብነትም እስካሁን እድሜያቸው ለትምህርት ከደረሱት ህፃናት መካከል 46 ነጥብ 7 ከመቶው ስደተኞችና ጥገኝነት ጠያቂዎች ብቻ ናቸው የትምህርት እድል እያገኙ ያሉት። ትምህርቱን ደግሞ ለሁሉም ስደተኞችና ጥገኞች ተደራሽ ለማድረግ ትልቅ ሃብት ይጠይቃል። መንግስትም ለስደተኞች የራሱ የሆነ በጀት የለውም፤ ሀብቱንም መሸፈን አይችልም። ከዚህ አኳ ያ በጀት እየተገኘ ያለው ከተባበሩት መንግስታት ድርጅት ከፍተኛ የስደተኞች ኮሚሽንና ሌሎች አጋር ረጂ ድርጅቶችን በመቀስቀስ ነው።

በዚህ የፕሮጀክት ትግበራ ትልቁ ክፍተት የሀብት ችግር ነው። በተለይ ደግሞ ባለፉት ሁለት ዓመታት ፈንድ ለማፈላለግ እጅግ አዳጋች ነበር። ይህም በትምህርት አሰጣጡ ላይ ብቻ ሳይሆን በሚሰጡ ሌሎች አገልግሎቶች ላይም አሉታዊ ተፅእኖ አሳድሯል። ትምህርቱም በቀነሰ ቁጥር በትምህርቱ ሴክተር ላይ የሚፈጥረው የራሱ አንድምታ ይኖረዋል።

የትምህርት ምገባም የዚሁ ፕሮጀክት አንዱ አካል በመሆኑና ይህ ምገባ ሲቀንስ ተማሪዎች ምግብ የማያገኙ ከሆነ ከትምህርት ገበታቸው ይቀራሉ። ቤተሰቦቻቸውም የምግብ ድጋፍ የማያገኙ ከሆነ ልጆቻቸው በሌላ የሥራ መስክ ላይ እንዲሆኑ ያደርጓቸዋል። እናም ተማሪዎች ከትምህርታቸው ይስተጓጎላሉ።

ምክትል ዋና ዳይሬክተሩ እንደሚገልፁት፤ ከ183 ሺህ በላይ ስደተኛና ጥገኝነት ጠያቂ ተማሪዎች በስደተኞችና ከስደት ተመላሾች አገልግሎት ተቋምም ሆነ በክልሎችም ባሉ የትምህርት ስርዓት ውስጥ ገብተው ትምህርታቸውን እየተከታተሉ ይገኛሉ።

እንደአጋጣሚ ፕሮጀክቱ ስደት ተቀባይ ማህበረሰብ ውስጥም ጭምር ተግባራዊ ስለሚደረግ እነሱንም ይበልጥ ያሳትፋል የሚል ተስፋ አለ። ስደተኞቹ የተለያየ ባህል፣ ቋንቋ፣ እምነትና የኑሮ ዘይቤ ያላቸው እንደመሆናቸው መጠን ፕሮጀክቱ በራሳቸው መንገድ ትምህርታቸውን በጨዋታ መልክ እንዲማሩ ከፍተኛ እገዛ እያደረገላቸው ይገኛል።

የሴቶችና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስትር ዴኤታ ወይዘሮ አለሚቱ ኡሙድ በበኩላቸው እንደሚሉት፤ ፕሌይ ማተርስ የተሰኘው ፕሮጀክት የተጀመረው ህፃናት ትምህርታቸውን ወደው እንዲማሩ ነው። በተለይ ደግሞ በአራቱ ክልሎች የትምህርት ጥራት ጉዳይ ችግር ውስጥ ያለ በመሆኑ ጥራትን ከማረጋገጥ አንጻር ፕሮጀክቱ ትልቅ ፋይዳ አለው።

በአራቱ ክልሎች በሚገኙ የስደተኞች መጠለያ ጣቢዎች ውስጥ ያሉ ስደተኛና ስደት ተቀባይ ማህበረሰብ ልጆች በአብዛኛው ማንበብና መፃፍ አይችሉም። የዚህ ፕሮጀክት ተግባራዊ መሆን ደግሞ በተለይ ልጆች በጨዋታ መልክ ትምህርቱን እንዲረዱት የሚያደርግ ነው። ስለዚህ ፋይዳው የጎላ ነው።

በሌላ በኩል ደግሞ ተማሪ ተኮር የማስተማር ስነ-ዘዴው በአዲሱ ስርዓተ ትምህርት ውስጥ ቢገባ ቅድመ መደበኛና አንደኛ ደረጃ ላይ የሚገኙ ተማሪዎችን እውቀት ይጨምራል። ስለሆነም የሴቶችና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴርም ከሚሰራባቸው ጉዳዮች ውስጥ አንዱ የህጻናት ትምህርት ነውና ያሉትን ክፍተቶች ፕሮጀክቱ የሚያሟላ መሆኑን ያምናል። ስለዚህም አስፈላጊነቱ አጠያያቂ አይደለም። በቀጣይ ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ በህፃናት ላይ ለሚሰራው ሥራም ትልቅ ድርሻ ይኖረዋል።

እንደሚኒስትር ዴኤታዋ ገለፃ፤ ከፕሮጀክቱ ጋር በተያያዘ ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ፕሮጀክቱን ብቻ ሳይሆን እንደሀገር የአስር ዓመት እቅድ አዘጋጅቶ እየተንቀሳቀሰ ይገኛል። ከአስር ዓመቱ እቅድ ውስጥ ደግሞ ራሱን የቻለ አዲስ መዋቅር አቋቁሟል። ይህንኑ መዋቅር የሴቶች፣ ህፃናትና ማህበራዊ ጉዳይ በሚባለው ቢሮ ውስጥ በማካተት የአረጋውያን፣ የአካል ጉዳተኞችና ተጠቂ የህብረተሰብ ክፍሎችን ያቀፈና የቤተሰብ ጉዳይ በዚህ ውስጥ ተካቶ እየተሰራ ይገኛል።

የህፃናትን ስብእና የመቅረፅ፣ ሀገራቸው ወደው የዲሞክራሲ ስርዓቱን ተለማምደው እንዲያልፉ በትምህርት ቤቶችና ክበባት ውስጥ ከቀበሌ እስከ ፌደራል ድረስ የህፃናት ፓርላማዎችን የማቋቋም ሥራዎችም ተሰርተዋል። በዚህም ተስፋን ሊያለመልሙ የሚችሉና ትውልድን በአዲስ መልኩ የመፍጠር ሁኔታዎች እየታዩ መጥተዋል።

አስተማሪ ተኮር የማስተማር ስነ ዘዴ ረጅም ዓመታትን የተሻገረና በኢትዮጵያ በሁሉም ትምህርት ቤቶች ተግባራዊ ሲደርግ የቆየ የማስተማር ስነ ዘዴ ነው። አሁን ጊዜው ተቀይሯል። ከአስተማሪው ጥቂት ብቻ ነው የሚጠበቀው። ሁሉንም ፈትፍቶ ለተማሪው እንዲያጎርስም አይጠበቅም። በመማር ማስተማር ሂደት ሚናውን የሚጫወተው ተማሪው ነው። ለዚህ ደግሞ ተማሪ ተኮር የማስተማር ስነ ዘዴን መጠቀም ግድ ይላል።


ወቅታዊና ልዩ ልዩ

# ወቅታዊ

# ‹‹ በውጭ ጉዳይ ዲፕሎማሲ እንደሚሰራ ሁሉ የፕሬስ ዲፕሎማሲም ያስፈልጋል ››

\- አቶ ማዕረጉ በዛብህ

ጋዜጠኛ፣ ዲፕሎማትና መምህር



ፎቶ - ፀሀይ ንጉሴ

አስቴር ኤልያስ

ጋዜጠኛና ዲፕሎማቱ አቶ ማዕረጉ በዛብህ የአዲስ ዘመን ጋዜጣ ዋና አዘጋጅ ሆነው ከመስራታቸው አስቀድሞ የዛሬይቱ ኢትዮጵያ አዘጋጅ ነበሩ። በማስታወቂያ ሚኒስቴር፣ በቱሪዝሙ ውስጥ ደግሞ የፕሮሞሽን መምሪያ ኃላፊ፣ ከዚያ በኋላ ትምህርታቸውን በፖለቲካው ዘርፍ በማሳደግ በጄኔቭ ቀጥሎም በእንግሊዝ በዲፕሎማሲው ዘርፍ ኢትዮጵያን ከ18 ዓመት በላይ አገልግለዋል። ወደአገር ቤት ተመልሰው ደግሞ በውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር የአውሮፓ ጉዳዮች ምክትል ኃላፊ ሆነው ሰርተዋል። በተጨማሪም ለረጅም ዓመት በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ እንዲሁም በዩኒቱ ዩኒቨርሲቲ ጋዜጠኝነትን አስተምረዋል። ከዚህ ጎን ለጎን ‹‹ጋዜጠኝነት ጽንሰ ሐሳቡና አተገባበሩ›› እና ‹‹በጋዜጠኝነት ሙያ አንዳንድ ርዕሰ ጉዳዮች›› በሚሉ ርዕሶች ሁለት መጽሀፍት እንዲሁም ‹‹የእኔ እንጉርጉሮ›› በሚል ርዕስ የግጥም መድብልም ጽፈው ለአንባቢያኑ አበርክተዋል። የዛሬው የወቅታዊ እንግዳችን መምህር፣ ጋዜጠኛና ደራሲም ሲሆኑ በጋዜጠኝነቱና በመገናኛ ብዙሃኑ ዙሪያ ስላለው ወቅታዊ ሁኔታ አነጋግረናቸው እንደሚከተለው አጠናቅረን አቅርበነዋል፡፡

**አዲስ ዘመን፡- አሁን ያለው ጋዜጠኝነት በእናንተ ዘመን ከነበረው ጋር ሲነጻጸር ምን ይመስላል በሚለው ጥያቄ ቃለ ምልልሳችንን እንጀምር?**

**አቶ ማዕረጉ፡-** ጋዜጠኝነት እንደ ሌሎች የሙያ አይነት ሁሉ እየተቀየረ መጥቷል። በተለይ በቴሌቪዥኑ በኩል ሰፋ ያለ እንቅስቃሴ እየተካሄደ መሆኑ የሚታይ ነው። በእርግጥ የስራውን ጉዳይ ለማነጻጸር ያስቸግራል። እኔ የሰራሁበት የሚዲያ ዘርፍ ሕትመት ላይ ነው፤ ይህ የሕትመት ሚዲያ ውጤት አሁን አሁን በከተማችን አዲስ አበባ ውስጥ እምብዛም አይታይም ማለት ያስደፍረኛል። ለምሳሌ አዲስ ዘመንን በመዲናችን ውስጥ አይቼ አላውቅም ማለት እችላለሁ። በጥቅሉ ከተማ ውስጥ ምንም ጋዜጣ ማግኘት አይቻልም። በመሆኑም ይህ ትልቅ ግደፈት ነው ባይ ነኝ።

በአሁኑ ወቅት በስፋት እየታዩ ያሉት የኤሌክትሮኒክስ ሚዲያ በተለይም ቴሌቪዥን ነው። አንደኛ ብዙ የጋዜጠኝነት ስራ የሚካሄደው ቴሌቪዥን ላይ ሲሆን፣ እሱም አብዛኛውን ጊዜ ውይይት ነው። እኔ በሰፊው በዩኒቨርስቲ ውስጥ ከማስተምረው የትምህርት አይነት አንዱ ደግሞ ቃለመጠይቅ (ኢንተርቪው) ነበር። ቃለ መጠይቅ ማድረግ ትልቅ ሙያ ነው። አንድ ጋዜጠኛ አንድ እንግዳ ጋብዞ ቃለምልልስ ከማድረጉ በፊት ቃለ ምልልሱን ለማድረግ ስለጋበዘው እንግዳ በሰፊው ሊያውቅ ይገባል። ሁለተኛ ደግሞ ሊያነጋግረው ስለሚፈልገው ሙያ ጋዜጠኛው በሰፊው እውቀት ሊኖረው ይገባል፡፡

አሁን አሁን እያየሁት ያለው ቃለ ምልልስ ግን በተለይ በቴሌቪዥን ላይ የሚካሄደው ቃለ ምልልስ አድራጊው እንደቀላል ነገር አውርቶ በመጨረሻም ‹‹እድል ልስጥዎት የሚጨምሩት ነገር ካለ›› ሲል ይደመጣል፤ በመጀመሪያ ደረጃ ‹‹እድል ልስጥዎ›› መባሉ በራሱ አግባብነት ያለው አባባል አይደለም። ቃለ ምልልስ የሚደረገው ሰው የጋዜጠኛው እንግዳ ነው፤ እንግዳ እስከሆነ ድረስ ተገቢውን ክብር መስጠት ተገቢ ነው። በተለይ ደግሞ አብዛኛዎቹ ቃለ ምልልስ የሚደረግላቸው ሰዎች በእድሜም፣ በትምህርትም፣ በስራም ከፍተኛ ቦታ ላይ ያሉ ሰዎች ስለሆኑ አክብሮትም ያስፈልጋል።

ሌላው ቃለ ምልልስ አድራጊው ጋዜጠኛ የሚጠቀመው አንድ ቋንቋ አለ፤ እሱም ‹‹መልካም›› የሚል ነው። ይህ አባባል ለእኔ አስቂኝ ነው። መልካም ማለት ልክ አንድ አስተማሪ ተማሪውን ‹‹ይህን አደረግህ እንዴ! እንግዲያውስ መልካም›› እንደሚለው አይነት ይመስላልና ‹‹እሽ! አመሰግናለሁ›› በሚባሉ ቃላት ነው መተካት ያለበት። ደግነቱ የሕትመት ሚዲያ ላይ ችግር የለም። ምክንያቱም ለተደራሲያኑ አይታይምና ነው። በቴሌቪዥን ሲሆን ግን የሚደረገው የቃለ ምልልስ መስተጋብር ስለሚታይ በዛ በኩል ጥንቃቄ ማድረጉ ተገቢ ነው። ይህ አንዱ አሰራር ነው።

ሌላው የቋንቋ ግድፈቱ በጣም ያሳፍራል። ይህ በአማርኛም በእንግሊዝኛም ሳይቀር ነው። በ‹ው› ካብዕ እና በ‹ው› ሳድስ ያለው ልዩነት የማይታወቅበት ዘመን ላይ ደርሰናል። ‹ምሳዬን በላሁ› ለማለት ‹ምሳዬን በላው› ይባል ተጀምሯል። እንዲህ እየተባለ ይጻፋል፤ በቴሌቪዥን ላይም በዚሁ መልክ ይነገራል። ከዚህ አንጻር የሚደረግ ጥንቃቄ የለም፡፡

በእኛ ዘመን ብዙ የተማርን ባንሆንም፤ በእውነቱ ከሆነ ጥንቃቄው በጣም የሚያስደስት ነበር። ጥናትና ንባብ በእጅጉ ይደረግ የነበረበት ዘመን ነው። እኔ አስቀድሜ እንደገለጽኩልሽ ያስተማርኩት ብዙ ዓመት ነው። የተማሩትም የት እንደሄዱ አላውቅም። አንዳንዴ ሳስብ ያስተማርናቸው ልጆች የት ሔደው ነው እላለሁ። እነዚህ ነገሮች በአግባቡ በክፍል ውስጥ ስናስተምር እንደቆየን አውቃለሁ።

በሌላ በኩል የቀደመውን ጋዜጠኝነትና የአሁኑን ለማነጻጸር ያህል አሁን ያለው እድል ከቀደመው በጣም የተሻለ ነው። በዛው ልክ ከኛ ዘመን ጋር ሲወዳደር ነጻነቱም ሰፊ ነው። የአሁኖቹ ጋዜጠኞች የፈለጉትን አይነት መጻሕፍት ያገኛሉ። ስለተለያዩ ሰዎች የሚነበብ ነገር ለማግኘት በጣም ቀላል ነው። ለምሳሌ ስለእኔ ብዙ የተጻፉ ነገሮች አሉ። እዚህ ላይ ማውራት የፈለግኩት ስለእኔ ሳይሆን ስለተለያዩ ሰዎች የተጻፉ በርካታ ነገሮች አሉና በዛው ልክ ተያያዥ የሆኑ ነገሮችን ማንበብ ይቻላል ለማለት ነው። ስለዚህ በቃለ ምልልስ አድራጊውና በተደራጊው መካከል የሚደረገው ቃለ ምልልስ ላይ የመጀመሪያው ቃለ ምልልስ መምሰል የለበትም። በዚህ ወቅት የጋዜጠኛውንም እውቀት የሚያሳይ መሆን አለበት፡፡

በትምህርት ከሆነ ደግሞ የአሁኖቹ ጋዜጠኞች የበለጠ በመማራቸው እድለኞች ናቸው ማለት ያስችላል። ብዙዎች በሚያስብል ደረጃ ዲግሪ ያላቸው ናቸው። ነገር ግን ጥረታቸው ያንን ያህል አይደለም። የአሁኖቹ ጋዜጠኞች የተማሩትን ያህል ብዙ ሆነው አይታዩም። በእርግጥ አልፎ አልፎ እጅግ ጎበዝ የሆኑ ጋዜጠኞች የሉም ለማለት ግን አይደለም።

አብዝቼ የምገልጽልሽ ስለ ቴሌቪዥኑ ነው፤ ስለ ሕትመት ሚዲያውማ አስቀድሜ እንደጠቀስኩልሽ ጋዜጣ በከተማው ውስጥ ስለሌለ ምንም የማውቀው ነገር የለም ማለቱ ይቀላል። በተለይ እኔ ከዛሬይቱና ከአዲስ ዘመን በተጨማሪ በሔራልድ ጋዜጣ ላይም ሰርቻለሁ። ከዚህም የተነሳ ሔራልድ ጋዜጣን ማየትና ማንበብ እፈልጋለሁ። በቋንቋ በኩል አዲስ ዘመን እንኳን ደህና ነው።

ለምሳሌ አንድ ነገር ልጥቀስ፤ ዲፕሎማሲያችን በጦርነቱ ተዳክሟል እየተባለ ሲነገር ነበር። ዲፕሎማሲው የሚሰራው አንደኛ አንድ ዲፕሎማት ተሹሞ ወደሌላ አገር ሲሄድ የሚያነበውና የሚያዳምጠው ከሚኖርበት አገር ያሉትን የሕትመተ ውጤቶችንና በብሮድካስት የሚተላለፉትን መረጃዎች ነው። የተለያየ መረጃ የሚያገኘው ከዚያ ነው። በእርግጥ በስራ ላይም ሊያገኝ ይችላል። ነገር ግን ዋና መረጃውን የሚያገኘው በየዕለቱ ከሚወጡ ጋዜጦችም ጭምር ነው። በየዕለቱ የሚወጡ ጋዜጦች ደግሞ በአጥጋቢ መልክ ካልተዘጋጁና ደረጃቸው ከፍ ያለ ካልሆነ አያነባቸውም፤ ይንቃቸዋል። ስለዚህ የሚያዘነብለው ወደራሱ ግምትና ሰዎች ወደሚሉት ነገር ነው። ለአገሩ የሚልከው ደግሞ በዛ መልኩ ያገኘውን መረጃ ይሆናል ማለት ነው።

የእርሱ አገር ደግሞ ኢትዮጵያን የሚያውቋት እሱ በላከው ሪፖርት ነው። ያ ሪፖርት ጥሩ ካልሆነ እንዲሁም ኢትዮጵያን በጥሩ ገጽታ የማያስቀምጣት ከሆነ ገጽታዋ በእነርሱ ዘንድ ጥሩ አይሆንም ማለት ነው። ስለዚህ ይሄ የራሳችን ስህተት ነው፤ በአሁኑ ወቅት በምዕራቡ ዓለም የሚንጸባረቀው ችግር ላይ የራሳችንም ስህተት አለበት። ምክንያቱም ተገቢውን መረጃ በአግባቡ እስካላገኙ ድረስ ማለት ነው። በዚህ ጉዳይ ልምድ ያላቸው ጋዜጠኞች ያፈስፈልጋሉ ማለት ነው፡፡ልክ በውጭ ጉዳይ ዲፕሎማሲ እንደሚሰራ ሁሉ የፕረስ ዲፕሎማሲ ያስፈልጋል እላለሁ። ይህን ሳየው ድክመት ያለ ይመስለኛል።

ይህን አይነቱን አካሄድ ሳየው በቀደመው ጊዜ የነበረው ጥረት ብዙ ነበር ያሰኘኛል። ሰዎች በጣም ይጥሩ ነበር። አብረውኝ ይሰሩ የነበሩ ጋዜጠኞች ምን ያህል ይደክሙ እንደነበር አስታውሳለሁ። ሌላው በቀደመው ጊዜ የአስተያየት ጽሑፍ ነበር። አሁን ይህ የለም ማለት ይቻላል። በተለይ ደግሞ በእንግሊዘኛ የሚጻፍ የአስተያየት ጽሑፍ የለም። ጋዜጠኛው ራሱ ዝም ብሎ ዜና መጻፍ ብቻ ሳይሆን በየዕለቱ የአስተያየት ጽሁፍ መጻፍ ይገባዋል።

አሁን ዲፕሎማሲያችን ‹‹ወደቀ›› የተባለው አንድም በዛ ነው። ቋንቋ የሚችል ኢትዮጵያዊ ጋዜጠኛ በእንግሊዝኛ ያለውን ወቅታዊ ሁኔታ ለምን አይጽፍም? በእርግጥ የምዕራባውያን ጋዜጠኝነት የመረጃ እጦት የለበትም፤ የእነርሱ ጋዜጠኝነት በርዕዮት ዓለምና በምዕራቡ ዓለም ጥቅም ላይ የተመሰረተ ስለሆነ ነው እንጂ መረጃ የማጣት ጉዳይ አይደለም። ቢሆንም ቅሉ የእኛ ጋዜጠኞች በቂ መረጃ ማቅረብ አለባቸው። እሱ ሳይሆን ቀርቶ የእኛ ጋዜጠኞች የሚጽፉት አነስተኛ ከሆነ ለውጪው እንዴት አድርጎ ነው የሚደርሰው? ስለዚህ አንዱም የራሳችን ችግር ነው።

**አዲስ ዘመን፡- ጋዜጦችን በመዲናችን አዲስ አበባ አላገኛኋቸውም ብለውኛል፤ ለዚህ ምክንያቱ ምንድን ነው ይላሉ?**

**አቶ ማዕረጉ፡-** ላለመኖራቸው ምክንያት የሚመስለኝ ስሕተት መስራት ነው፤ ምክንያቱም ጋዜጦቹ ከታተሙ መዳረስ አለባቸው። ጋዜጦቹ የሚገኙት አራት ኪሎ ብቻ ነው፤ ምሳሌ የእኔ መኖሪያ ከአራት ኪሎ በብዙ ርቀት ላይ ቢሆን ጋዜጣ ለመግዛት ብዬ አራት ኪሎ ድረስ ለመሄድ አልችልም። ነገር ግን ጋዜጣ ገዝቶ ማንበብ ደግሞ እፈልጋለሁ፤ ሳስበው የትራንስፖርቱ ሁኔታና ርቀቱ ይታየኝና እተወዋለሁ። ስለዚህ ይህ ‹ምናለ በከተማው ውስጥ በየቦታው ስርጭቱ ቢኖር› የሚያሰኝ ነው።

**አዲስ ዘመን፡- የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት የሚያሳትማቸውን ጋዜጦች ወደተለያዩ ክልል ከተሞች ያደርሳል፤ በአዲስ አበባ ከተማም የማሰራጫ ሱቆች አሉት።ይሄ በቂ ሳይሆን እና ስርጭቱም አነስተኛሲሆን ይችላል። ለዚህ ታድያ መፍትሄው ምን መሆን አለበት.?**

**አቶ ማዕረጉ፡-** በእርግጥ በኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት የቦርድ አባል የሆንኩት ገና በቅርቡ ነው፤ ድርጅቱን የመጎብኘት እድል አግኝቻለሁ። እየሰራ ያለው ስራ ይበል የሚያሰኝና የሚበረታታ ነው፤ በተለይ ደግሞ በተለያዩ ቋንቋዎች እያሳተማቸው ያሉ መጻሕፍትን አይቼ ተደንቄያለሁ። ከዚህ ጋር ደግሞ የጋዜጦች ማከፋፈያ ማዕከላት ማቋቋም በጣም አስፈላጊ ነው። ምክንያቱም የሕትመት ሚዲያ ከብሮድካስቱ የሚለይበት ብዙ መንገድ አለ። ሁለቱም የየራሳቸው ጥቅም አላቸው። የየራሳቸው ድክመትም አላቸው። የሕትመት ሚዲያው የሕትመት ውጤቱን መግዛቱ፣ መሸከሙ ብሎም ማንበቡም ከባድ ስለሆነ ውጣ ውረድ አለው። ስለዚህ የብሮድካስቱ ደግሞ በቀላሉ መስማት ያስችላሉ፤ ነገር ግን ቀሪ መረጃ በእጅ ላይ አይኖርም። ስለዚህ ፕሬስ ተጽዕኖ ሊኖረው የሚችለው ሁለቱ አንድ ላይ ሲሆኑ ነው። እውነት ለመናገር ጋዜጣ ለማሳተም መንግስት ብዙ ገንዘብ እንደሚያወጣ አያለሁ። ፕሬስ እያቀዳቸው ያሉ ትልልቅ እቅዶች አሉት፤ ከዚህም ውስጥ አንዱ ማተሚያ ቤት እንዲኖረው ይፈልጋልና ይህ

# ወቅታዊ

ትልቅ ስራ ነው። ስለዚህ የጋዜጣ ማሰራጫ ጣቢያዎችም ያስፈልጉታል ባይ ነኝ።

**አዲስ ዘመን፡- ጋዜጠኝነት እንደሙያ ነጻ ነው ሲባል ምን ማለት ነው? በእርግጥ ምዕራቡ ዓለም እንደሚለው ነጻ ሲባል የሚችል ጋዜጠኝነት አለ?**

**አቶ ማዕረጉ፡-** ጋዜጠኝነት በምዕራቡ ዓለም እንደሚባለው ነጻ ነው ለማለት ያስቸግራል። በመጀመሪያ ደረጃ ምዕራቡና እኛ የተለያየን ነን። በኢኮኖሚ፣ በባህልም ሆነ በታሪክ እንለያያለን። ለእነርሱ ትልቅ የተባለ ጉዳይ ምናልባት ለእኛ ያን ያህል ላይሆን ይችላል። በተቃራኒው ደግሞ እኛ ትልቅ ጉዳይ የሚመስለን ነገር ለእነርሱ ምንም ላይሆን ይችላል። ዞሮ ዞሮ ሁሉም ነገር ከእድገት ጋር ይሄዳል። እድገት የሚባለው ደግሞ ወደድንም ጠላንም በምዕራቡ ዓለም አስተሳሰብ የተቃኘ ነው። እድገት የሚለካው በኢኮኖሚ፣ በትራንስፖርት፣ በሳይንስ፣ በቴክኖሎጂና በእነዚህ መሰል ነገሮች ነው እንጂ በታሪክና በባህል አይደለም።

ስለጋዜጠኝነት ከተነሳ በጣም ሳቢ የሆነ ጉዳይ አለ፤ ይኸውም የእኛ ጋዜጠኝነት አገር በቀል መሆኑ ነው። እንደሚታወቀው ብዙዎቹ የአፍሪካም ሆኑ የኢስያ አገሮች ጋዜጠኝነትን ያገኙት ከቅኝ ገዥዎቻቸው ነው። ለምሳሌ ኬንያን ብትወስጂ በጣም ደረጃውን የጠበቀ ጋዜጣ አላቸው። እነዚህ በምዕራቡ ዓለም የሚቃኙ ናቸው። እንደዛ ሊሆን የቻለው ምዕራባውያኑ (ቅኝ ገዥዎቻቸው) ሲወጡ ጥለውት የሄዱት መሰረት ወይም ሌጋሲ ነው። እነርሱም በቅኝ ግዛት ውስጥ ስለነበሩ ያቺኑ አስቀጥለው መሄድ ቻሉ፡፡


አሁን የኢትዮጵያ ጋዜጠኝነትና የምስራቅ አፍሪካም ሆነ የምዕራብ አፍሪካ ጋዜጠኝነት የተለያዩ ናቸው። እኔ እንዳጋጣሚ ናይሮቢ ሔጀለሁ፤ ኢስት አፍሪካን ስታንዳርድን አንብቤዋለሁ፤ አይቻዋለሁ። ‹‹The Press of Africa: Persecution and Perseverance›› የዚህ መጻሕፍ ጸሐፊ የሚለው የኢትዮጵያ ጋዜጠኝነት ከሌላው አፍሪካ ጋር የሚስተካከል አይደለም። ለዚህ ደግሞ በምክንያነት የሚያስቀምጠው የጃንሆይን ታሪክ ብቻ ነው ይዞ የሚወጣው የሚል ነው። ይህን ያለው ደግሞ እኔ የጻፍኩትን አርቲክል ወስዶ ነው። ይሁንና ለዛ አርቲክል እውቅና ሳይሰጠው በመጻሕፉ ላይ ያቀረበው ራሱ እንደጻፈ አይነት አድርጎ ነው፡፡አርቲክሉን የጻፍኩት እኔ ስሆን፣ የወሰደውም እንግሊዝ አገር ከሚታተም አንድ መጽሔት ላይ ነው። አርቲክሉን ሲወስድ ምንም እንኳ ጸሐፊው ማዕረጉ ነው ባይልም በተወሰነ መልኩ ብቻ ስሜን ጠቅሶታል።

**አዲስ ዘመን፡- በእርስዎ እተያይ በአሁኑ ወቅት ያሉ ጋዜጠኞች ነጻ ሆነው መስራት የሚያስችላቸው መደላድል አለ ብለው ያስባሉ?**

**አቶ ማዕረጉ፡-** ነጻነት አንጻራዊ ነው፤ ፍጹም የሆነ ነጻነት የለም። ይህ በምዕራቡም ዓለም ቢሆን ማለት ነው። ምክንያቱም አንድ ጋዜጠኛ በሚሰራው በድርጅቱ የኤዲቶሪያል ፖሊሲ መሰረት የማይጽፍ ከሆነ ይከሰሳል። ከፍ ያለ የገንዘብ ቅጣት ሊጣልበት ይችላል፤ ከስራም ሊባረር ይችላል። ስለዚህም ፍጹም የሆነ ነጻነት የለም። ስለዚህ ነጻነት ሲባል አንጻራዊ ነው።

በሌላ በኩል ደግሞ በአሁኑ ሰዓት ያለው የፖለቲካው ተጽዕኖ ብቻ አይደለም። የባህልም የታሪክም ተጽዕኖ አለ። ስለዚህም ነጻነት የሚገደበው በብዙ መልክ ነው። ከዚህ ባሻገር ጋዜጠኝነት ሲባል በራሱ እንደ ሙያ ብስለት ያስፈልገዋል። ለምሳሌ በፖለቲካው ጉዳይ የተለያዩ የተፎካካሪ ፓርቲዎችን በመውሰድ መተንተን ይቻላል ብዬ አስባለሁ። ይሁን እንጂ በዚህ መልኩ የሚሰራ ጋዜጠኛ እምብዛም አላይም፤ ለምሳሌ አንድ ጋዜጠኛ ስለአንድ ነገር ለመጻፍ ሲነሳ ስለጉዳዩ በአግባቡ መረዳትና ማወቅ ይገባል፡፡

ለምሳሌ ከሁለት ዓመት በፊት ባጋጠመን ጦርነት ላይ በምዕራቡ ዓለም የነበረን ምስል መንግስት ራሱ ጦርነቱን እንደጀመረው ተደርጎ ሲወራ ነበር። በእርግጥ ይህ የሆነው በአንድ በኩል ጠንካራ የሆነ የሚዲያም ድጋፍ ስለሌለ ነው። ለአብነት ያህል በሔራልድ ትክክለኛውን ዜና መጻፍና እውነታውን ማሳወቅ የግድ የሚል ነው። ወደ ኢትዮጵያ ብሮድካስቲንግ ኮርፖሬሽን ሲመጣ ደግሞ እንግሊዝኛ ቀድሞውኑ የታለና ነው ? በኛ ዘመን እንግሊዝኛ የሚነገረውም የሚጻፍበትም ከአማርኛ ጋር እኩል ነው። ለምሳሌ አንድ ወረቀት በአንድ ሰው እጅ ላይ የሚታይ ከሆኑ ከፊት ለፊቱ አማርኛ ካለ ከጀርባው እንግሊዝኛ ነው። በአሁኑ ወቅት በእንግሊዝኛ የሚጽፍ ሰው የለም ማለት ያስደፍራል። እኔ ለረጅም ዓመት አርታኢ ሆኜም ስለቆየሁ አማርኛም ሆነ እንግሊዝኛ ሲሳሳት በጣም አዝናለሁ፡፡



**የምዕራቡ ፍልስፍና፣ የኢኮኖሚ እንዲሁም የምዕራቡ የፖለቲካ ስርዓት ካልሆነ በስተቀር ሌላ ስርዓት እንዲኖር አይፈልግም። እንደ ኢትዮጵያ አይነት አገሮች ብቅ ሲሉ የሚደነግጡት ለዚህ ነው**

**አዲስ ዘመን፡- በኢትዮጵያ ያሉ መገናኛ ብዙኃን ኃላፊነታቸውን በአግባቡ እየተወጡ ነው ማለት ይቻላል? ያሉበትስ ደረጃ ምን ላይ ነው ይላሉ?**

**አቶ ማዕረጉ፡-** ኃላፊነትን ከመወጣት አኳያ እኔ እርካታ የለኝም። ብዙ ሊሰራ እንደሚችል እገምታለሁ። ቀደም ሲል ጥቂት ሰዎች በትንሽ ትምህርት ብዙ ነገር መስራት ችለዋል ብዬሻለሁ። በአሁኑ ወቅት ግን ከዩኒቨርሲቲ ወጣሁ የሚለው ሰው ብዙ ነው። በርካታ የተመቻቸ ነገርም አለ፤ ቴክኖሎጂው በራሱ የሚያግዝ ነው። በእኛ ጊዜ የጋዜጣውን ዲዛይን መስራቱ በራሱ በጣም ከባድ ነበር። እኔ ለምሳሌ አዲስ ዘመን ላይ አንድ ትልቅ ነገር የሰራሁት ዳሚውን (የጋዜጣውን ገፅታ ወረቀት ላይ መሰራት) የማስተምረው እኔ ነበርኩ። ምክንያቱም እኔ ዳሚ የተማርኩት ስኩል ኦፍ ጆርናሊዝም እንግሊዝ አገር ነው። አሁን ግን ዳሚውን መስራት በጣም ቀላል ነው፤ ምክንያቱም የሚሰራው በኮምፒውተር ነው። እንደዚያም ሆኖ ፎቶግራፍ ያለካፕሽን (መግለጫ) ይወጣል። መግለጫ የሌለው ፎቶ ደግሞ ምንም ትርጉም የለውም።

በብሮድካስት ሚዲያው ላይ የማየው ችግር አስቀድሜ ለመጥቀስ እንደሞከርኩት የጋዜጠኛው የእውቀት ጥልቀት ችግር ነው። ሁሉንም ማለቴ ግን አይደለም። እውቀት ያላቸው ስለሚሰሩት ስራ ባለሙያ ናቸው እስከሚያስብል ድረስ የሚያውቁ አስደናቂ የፕሮግራም አዘጋጆች አሉ። ስለዚህ ጥረት ነው የሚያስፈልገው።

**አዲስ ዘመን፡- የምዕራባውያን ትልልቆቹ ሚዲያዎች የአገራቸውን ፍላጎት ለማስጠበቅ ለአገራቸው ወግነው ይቆማሉ፤ ከዚህ አንጻር በአገራችን ላይ ተጽዕኖ ሲፈጥሩ ይታያል፤ በኢትዮጵያ ያሉ ሚዲያዎች አገራቸውን ከማስበለጥና ከማዳን አኳያ ስራቸው ምን ይመስላል?**

**አቶ ማዕረጉ፡-** ይህ በጣም ወሳኝ ጥያቄ ነው፤ በእውነት ከሆነ የሚያሳዝነኝ ነገር እሱ ነው። ከዚህ አኳያ በበቂ ሁኔታ አይሰሩም። ለምሳሌ የሰሜኑ ጦርነት በሚገባ አልተገለጸም። ለዚህ ደግሞ ዋናው ችግር ቋንቋ ካለማወቅ ነው። ሌላው ደግሞ በሕትመት እና በብሮድካስቱ ሚዲያ መካከል ቅብብሎሽ መኖር አለበት። በሕትመት ሚዲያው አንድ ጥሩ አርቲክል ከተጻፈ አርቲክሉ በብሮድካስት ሚዲያም መተላለፍ አለበት። በተመሳሳይ በብሮድካስት ሚዲያው ጥሩ ውይይት ከተደረገ ውይይቱ በሕትመት ሚዲያው እንዲሁ መጻፍ አለበት። ይህ ቅብብሎሽ የለም፤ ቢኖር ጥሩ ነው። ይህ ግን የሚጠቅመው ጥልቀት ያለው ጽሑፍ የሚጽፉ ጋዜጠኞች ሲኖሩ ነው፤ ከሌሉ ግን የውጭ ሰው እንዲጽፍ ማድረግ ይቻላል፡፡

**አዲስ ዘመን፡- መንግስት የመገናኛ ብዙኃኑን በነጻነት እንዲሰሩ እያደረገ ነው ብለው ያምናሉ?**

**አቶ ማዕረጉ፡-** አገራችን በጠቅላይ ሚኒስትር ዶክተር ዐቢይ አሕመድ በመመራት ላይ ትገኛለች፤ መንግስት ደግሞ አንድ ዓላማ አለው። ይኸውም ልማትና አገርን ማሳደግ ነው። ኅብረብሔርነትን መያዝ ነው፤ ምክንያቱም አገሪቷ ከዚህ አንጻር ብዙ ፈተና አለባት። እነዚህን የመንግስት ዓላማዎች የሚቃወም ሚዲያ እስካልሆነ ድረስ የሚዲያዎቹን ሐሳብ የሚገድብ መንግስት አይመስለኝም። በእርግጥ ይህንን ለማወቅ ውስጡ መሆን ይገባል። ከዚህ አኳያ የብሮድካስቱ ላይ እንደማየው የሚጠየቀው ጥያቄ ብዙ ሊያናግር የሚችል ነውና የነጻነት አለመኖር ችግር ያለ አይመስለኝም።

የነጻነት ችግርማ በእኛ ጊዜ ነበር። በጃንሆይ ጊዜ ብዙ ነገሮች ነበሩ። እያንዳንዱ ሚኒስትርም ሆነ ጄነራል አኩራፊ ነው። ጠርቶ ለምን ሆነ የሚል ነው። በደርግም ጊዜ ቢሆን እንዲሁ ነው፤ ያስፈራል። በአሁኑ ወቅት ግን እንዲህ አይነት ነገር አለ ብዬ አላምንም። ምክንያቱም ነጻነቱ አለ። መነጋገር የሚገባው ያለውን ነጻነት መጠቀም ያለባቸው እንዴት ነው በሚለው ላይ ነው። ለምሳሌ መጻሕፍት እየታተመ ነው፤ ነገር ግን ቅድመ ግምገማ የሚባል ነገር የለም። ስለሆነም ነጻነቱ አለ።

**አዲስ ዘመን፡- የሽግግር ወቅት ላይ ከመሆኑ አንጻር አሁን ያለውን ሁኔታ የሚገመግሙት እንዴት ነው?**

**አቶ ማዕረጉ፡-** ይህ የመረጃ ጉዳይ ከባህልም ጋር የተያያዘ ነው። ዋናው ምክንያት ፖለቲካ ነው። ምክንያቱም አንድ መስሪያ ቤት ውስጥ የሚሰራ ሰው በራሱ ፈቃድ ተነስቶ ስለመስሪያ ቤቱ ወይም ስለ አንድ ጉዳይ ለመግለጽ ይፈራል። የበላይን ይፈራል። በሌላ በኩል ደግሞ እንደባህል የተያዘ ነገር አለ፤ ፊት ለፊት መነጋገርና መወያየት ብዙ አላዳበርንም፤ ከኋላ በሐሜት መልክ ነው የሚቀርበው። ስለዚህ ሰው ለቃለ መጠይቅ ፈቃደኛ አይሆንም።

የአሁኑ ትውልድ ባለስልጣናቱ ማለቴ ነው በነጻነት መናገር አለባቸው፤ ግን ባህሉ እየጎተታቸው ነው፤ ሲጠየቁ እንዲያው ደስ ሊላቸው ይገባል፤ ምክንያቱም የሰሩትን ስራ ነው የሚናገሩት፤ ግን ባህል ሲጎትታቸው ይታያል፤ በአጼ ኃይለስላሴ ጊዜም ቢሆን በደርግም ጊዜ በጣም ከባድ ነበር፤ በኢህአዴግም እንዲሁ ነው፤ ማን ፈቀደልህ ይባላል፤ ሳትታዘዝ እንደፈለክ መፈንጨት አትችልም ይባላል፡፡

ከዚህ አይነት አካሄድ መውጣት የሚቻለው በማደግ ነው፤ ቴክኖሎጂው ሲያድግና ትምህርት ሲስፋፋ የሚመጣ ጉዳይ ነው። በመጀመሪያ በየቦታው ሕዝብ ውይይት ሲያደርግ ነው። አንዳንዴ ውይይቶች አሉ፤ የተወሰነ ቡድን ብቻ ከመጋበዝ ደግሞ እንደእኔ አይነቶችም አሉና ብንጋበዝ የምናበረክተው ነገር ይኖራል። ውይይቱ ሲስፋፋ ያንን ለመሸፈን ይሰራልና ሚዲያም ያድጋል።

**አዲስ ዘመን፡-ባለፉት ሁለት ዓመታት ኢትዮጵያ ውስጥ ከነበረው ጦርነት ጋር ተያይዞ ከምዕራቡ ዓለም በኢትዮጵያ ላይ ሲደርስ የነበረው ተጽዕኖ ገሃድ የወጣ ነው፤ ከእነዚህም መካከል አንዱ የምዕራቡ ዓለም የተቀናጀ ዘመቻ ነበርና ይህን እርስዎ እንዴት ነበር ያዩት?**

**አቶ ማዕረጉ፡-** ይህ በጣም ጥሩ ጥያቄ ነው፤ በምዕራቡ ዓለም ነጻነት አለ ይባላል፤ ነገር ግን የሚገዛቸው ነገር አለ፤ ነጻ ነን ይበሉ እንጂ ከምዕራቡ አስተሳሰብ ነጻ ሊሆኑ አይችሉም። ዓለም በምዕራቡ ዓለም ሞኖፖሊ እንዲሆን ለማድረግ የተደረገ ዘመቻ ባለፈው 50 እና 60 ዓመት በጣም ከባድ ነው። ስለዚህ የምዕራቡ ሚዲያ የጦርነት አይነት ሚዲያ ነው።

የምዕራቡ ፍልስፍና፣ የኢኮኖሚ እንዲሁም የምዕራቡ የፖለቲካ ስርዓት ካልሆነ በስተቀር ሌላ ስርዓት እንዲኖር አይፈልግም። እንደ ኢትዮጵያ አይነት አገሮች ብቅ ሲሉ የሚደነግጡት ለዚህ ነው። ለምሳሌ አሁን ያስደነገጣቸው በኢትዮጵያ ያለው የአሁኑ መንግስት ነጻ ሆኖ ማሰብ የሚችል ነው። በነጻነት የሚያስብ፤ በነጻነት የሚሰራ ነው። የኢትዮጵያ መንግስት ከኋላ የሚያዝዘው ምንም የሌለው ነጻ የሆነ መንግስት ነው።

ምዕራባውያኑ ጠንካራ መንግስት እንዲኖር አይፈልጉም። ስለዚህም በመንግስት ላይ ትልቅ ትግል ሲያካሄዱ ነበር እንጂ የሕወሓት መሪዎች እነርሱን ስለሚጠቅሟቸው አይደለም፤ እንደማይጠቅሟቸውም ያውቃሉ። ጫናው የመጣውም ነጻ የሆነው የኢትዮጵያ መንግስት ቀና ብሎ መሄድ ሲጀምር ወዴት እየሄደ ነው ከሚል ስጋት ነው፤ ምዕራባውያኑ መጫን የሚሹት ያቺኑ የእነርሱን አስተሳሰብ ነው፤ ከስሜት ነጻ የሆነ ዜና ወደዓለም እናደርሳለን የሚል አስተሳሰብ ይዘው የተነሱ ቢሆኑም ከስሜትና ከራስ ጥቅም የጸዳ አይደለም። ሌላው ቀርቶ ጦርነቱን የጀመረው ሕወሓት እንደነበር እንኳን በወቅቱ አለመግለጻቸው አንዱ ማሳያ ነው። ለምሳሌ ይህ ትልቅ ጉድለት ነው። ከእኛ ውጪ ምንም አስተሳሰብና ርዕዮተ ዓለም አይኑር ባዮች ናቸው። ኢትዮጵያ የምዕራቡ ዓለም መራኮቻ አይደለችም። ይህን እያወቁ መጥተዋል። በጠቅላይ ሚኒስትሩ በኩል አራት ዓመት ሙሉ ነጻ የመሆንና የማደግ ጥረቱ አለ፤ በአሜሪካ ለሽልማት ድረስ እንዲበቁ ያደረጋቸው እሱም ጭምር ነው። የዚህ መንግስት ችግሩ በጣም ሩህሩህነት እና ደግነቱ ነው። ከዚህ በኋላ ጠንክሮ መስራትና ኢኮኖሚውንም ማሳደግ ነው።

**አዲስ ዘመን፡- ስለሰጡን ሰፊ ማብራሪያ ከልብ አመሰግናለሁ፡፡**

**አቶ ማዕረጉ፡-** እኔም አመሰግናለሁ፡፡

# ዓለም አቀፍ



## በደቡብ አፍሪካ ነዳጅ የጫነ ተሽከርካሪ ሆስፒታል አቅራቢያ ፈንድቶ በርካታ ሰዎች ሞቱ

ከደቡብ አፍሪካዋ ጆሃንስበርግ ከተማ በስተምሥራቅ በሚገኝ አንድ ሆስፒታል አቅራቢያ አንድ ግዙፍ ነዳጅ የጫነ ተሽከርካሪ ፈንድቶ በርካታ ሰዎች ለሞት እና ለጉዳት ተዳረጉ። ነዳጅ የጫነው ተሽከርካሪ (ቦቴ) ቅዳሜ ጠዋት ከጆሃንስበርግ ከተማ አቅራቢያ በምትገኘው ቦክስበርግ ከተማ ውስጥ ከሚገኘው የቶምቦ መታሰቢያ ሆስፒታል 100 ሜትር ርቀት ላይ ካለ መተላለፊያ ድልድይ ስር ሆኖ ነው ፍንዳታው የተከሰተው።

በፍንዳታው ቢያንስ ስምንት ሰዎች ሕይወታቸውን ያጡ ሲሆን፣ በርካታ ቁጥር ያላቸው ደግሞ የተለያየ መጠን ያለው ጉዳት እንደደረሰባቸው የአገሪቱ መገናኛ ብዙኃን ዘግበዋል። ለሆስፒታሉ እጅግ በጣም ቅርብ በሆነ ቦታ ላይ ባጋጠመው በዚህ የነዳጅ ጫኝ ተሽከርካሪው ፍንዳታ ምክንያት፣ የሆስፒታሉ አንደኛ ክፍል ጣሪያ በመፍረሱ ህሙማን እንዲወጡ ተደርጓል።

የደቡብ አፍሪካ መገናኛ ብዙኃን እንደዘገቡት የፈነዳው ተሽከርካሪ የሲሊንደር ጋር የጫነ ነበር።

"ጋዝ የጫነው ከባድ መኪና ከመሬት በታች ባለ ትንሽዬ ድልድይ በኩል ለማለፍ ሲሞክር ተቀርቅሮ መንቀሳቀስ ባለመቻሉ በተፈጠረ ሰበቃ ምክንያት እሳት ተፈጥሮ ፍንዳታው ተከስቷል" ሲሉ የአደጋ መከላከያ መሥሪያ ቤት ቃል አቀባይ ዊሊያም ንትላዲ ተናግረዋል።

ፍንዳታውን ተከትሎ የተነሳውን የእሳት ቃጠሎ ለመቆጣጠር የእሳት አደጋ ተከላካይ ሠራተኞች ጥረት በሚያደርጉበት ጊዜ፣ ሌላ ከባድ ፍንዳታ ተከስቶ አንድ የእሳት አደጋ ማጥፊያ ተሽከርካሪን እና ሁለት መኪኖችን ሲያወድም በስፍራው በነበረ ግለሰብ የተቀረጸ ቪዲዮ አሳይቷል። ማይክል ኩሊንጂ የተባለ የዓይን እማኝ ፍንዳታው "የቦምብ ይመስል ነበር" ሲል ከድልድዩ ስር እሳት መመልከቱን ለሮይተርስ የዜና ወኪል ተናግሯል።

ሌላ በስፍራው የነበረች ጄን ማሪ ቦይሰን የተባለች የዓይን እማኝ ደግሞ ቅዳሜ ጠዋት አንድ ሰዓት ከመሆኑ በፊት ከባድ የእሳት ነበልባል እንደተመለከተችና ፍንዳታውም የመሬት መንቀጥቀጥ የተከሰተ እንደመሰላት ለሮይተርስ ገልጻለች። አደጋውን ተከትሎ ወዲያውኑ የተቀረጹ የቪዲዮ ምስሎች በቃጠሎ የተጎዱ እና ግራ የተጋቡ ሰዎች ከፍንዳታው ቦታ አቅራቢያ ባለ በሚገኝ የመኖሪያ ሰፈር ውስጥ ወድቀው ማሳየታቸውን ቢቢሲ ዘግቧል።

## አሜሪካውያን በአዲስ ዓመት ዋዜማ በከባድ የአየር ሁኔታ እየተፈተኑ ነው

ከፈረንጆች ገና እና ከአዲስ ዓመት መባቻ በፊት ባሉት ቀናት በአሜሪካ ከተከሰተው ከባድ ቅዝቃዜ እና የክረምት ወጀብ ጋር በተያያዘ ቢያንስ 12 ሰዎች መሞታቸው ተነገረ። በረዷማው እና ከፍተኛ ቅዝቃዜን የያዘው ወጀብ 200 ሚሊዮን በሚሆኑ አሜሪካውያን የዕለት ከዕለት ሕይወት እና እንቅስቃሴ ላይ ተጽእኖን አሳድሯል ተብሏል።

በዚህም ሳቢያ ከአንድ ነጥብ 5 ሚሊዮን የሚልቁ ሰዎች የኤሌክትሪክ ኃይል አቅርቦት የተቋረጠባቸው ሲሆን፣ በሺዎች የሚቆጠሩ የአውሮፕላን በረራዎች አርብ ዕለት ተሰርዘዋል። ይህ ከባድ የቅዝቃዜ ወጀብ ከአሜሪካዋ ቴክሳስ ግዛት እስከ ካናዳዋ ኩቤክ የሚዘልቅ 3ሺህ 200 ኪሎ ሜትሮችን በሚሸፍን ቦታ ላይ የተከሰተ ነው።

የከባቢ አየር ግፊት ሲቀንስ የሚከሰተው ከፍተኛ አውሎ ንፋስ (ቦምብ ሳይክሎን) በአሜሪካ እና በካናዳ ድንበር ላይ ባለው የታላላቅ ሐይቆች አካባቢ ከፍተኛ እና በረዶ የቀላቀለ ንፋስን አስከትሏል። ከአሜሪካ በተጨማሪ ይህ ከባድ የአየር ሁኔታ በካናዳ የኦንታሪዮ እና የኩቤክ ግዛቶች ውስጥ በመቶ ሺዎች የሚቆጠሩ ሰዎችን ከኤሌክትሪክ አገልግሎት ውጪ አድርጓቸዋል።

እንዲሁም የተቀሩት የካናዳ አካባቢዎች በከባድ ቅዝቃዜ ውስጥ የሚገኙ ሲሆን፣ ከባድ የክረትም ወጀብ ሊከሰት እንደሚችል ማስጠንቀቂያ ተሰጥቷቸዋል። የአሜሪካ ብሔራዊ የአየር ንብረት አገልግሎት አርብ ዕለት ያወጣው የአየር ሁኔታ አመላካች መረጃ፣ ተቋሙ እስካሁን ካወጣቸው "ከፍተኛው የክረምት ማስጠንቀቂያ እና ምክር" መካከል አንዱ እንደሆነ ተነግሯል።

ኤልክ ፓርክ በተሰኘችው የአሜሪካ አነስተኛ ከተማ የቅዝቃዜው መጠን ከዜሮ በታች 45 ዲግሪ ሴንቲ ግሬድ የደረሰ ሲሆን የሚችጋን ቅዝቃዜ ደግሞ ከታች ወርዷል። ቅዝቃዜው አርብ ዕለት ከዜሮ በታች 17 ዲግሪ ሴንቲ ግሬድ ደርሶ የነበረ ሲሆን፣ ምሽት ላይ አካባቢው በበረዶ ተሸፍኖ ነበር።




ቢቢቢ ያነጋገራት ኤሚሊ የተባለች የመጠጥ ቤት ሠራተኛ "በጣም ቀዝቃዛ ነው። አስቸጋሪ ጊዜ እያሳለፍን ነው" ብላለች። በደቡባዊ ዳኮታ ግዛት ውስጥ ያሉ ነዋሪዎች ነዳጅ ስላለቀባቸው ሙቀት ለማግኘት ሲሉ ልብሶችን በእሳት እያነደዱ መሆናቸውን የማኅበረሰቡ ባለሥልጣን ተናግረዋል።

በፔንስለቬኒያ እና ሚችጋን ከፍተኛ በረዶ ሊጥል እንደሚችል ትንብያ ተሰጥቷል። በተመሳሳይ በቡፋሎ እና ኒው ዮርክም ከፍ ያለ መጠን ያለው በረዶ ይጥላል ተብሏል። ብሔራዊው የአየር ተንበያ ተቋም እንዳለው ከስምንት ሚሊዮን የሚልቁ ሰዎች በከባዱ የክረምት ወጀብ ማስጠንቀቂያ ውስጥ ይቆያሉ። በኒው ኢንግላንድ፣ በኒው ዮርክ እና በኒው ጀርሲ የባሕር ዳርቻዎች ላይ ጎርፍ ተከስቷል።

ቀላል አየር ሁኔታ የሚያስተናግዱት ሉዊዚያና፣ አላባማ፣ ፍሎሪዳ እና ጆርጂያ ጠንከር ያለ ቅዝቃዜ ሊያስተናግዱ እንደሚችሉ ማስጠንቀቂያ እንዳደረሳቸው የቢሲሲ ዘገባ ያመለክታል።

## ከኢፌዴሪ ትምህርት ሚኒስቴር ጋር በመተባበር በየሳምንቱ ሰኞና ዓርብ የሚታተም

# የመውጫ ፈተና እና ተጠባቂ የቤት ሥራዎች

የትምህርት ጥራትን ለማሻሻል በያዝነው ዓመት ሊተገበሩ ከታቀዱት ሥራዎች መካከል በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የሚሰጠው የመውጫ ፈተና አንዱ እንደሆነ ይታወቃል። አቶ ሰኢድ መሀመድ በትምህርት ሚኒስቴር የከፍተኛ ትምህርት ብቃት እና ጥራት ማሻሻያ የዴስክ ኃላፊ ናቸው። እርሳቸው ከፋና ብሮድካስቲንግ ኮርፖሬት ጋር ባደረጉት ቆይታ እንደገለጹት ፤እንደ ትምህርት ሚኒስቴር ይህንን የመውጫ ፈተና በዚህ ዓመት ተግባራዊ ለማድረግ በርካታ እንቅስቃሴዎች እና ሥራዎች እየተሰሩ ናቸው። ከዝግጅቶቹ መካከልም ፈተናውን በተሳካ መልኩ ለመስጠት ከወዲሁ ቅድመ ዝግጅቶች እየተደረጉ ሲሆን፤ ለዚህም በየትምህርት መስክ የሚመረቁ ተማሪዎች ምን አይነት ብቃት ይጠበቅባቸዋል? የሚል ከክህሎት፣ እውቀት እና አመለካከት አንጻር ተለይተው ተዘጋጅተዋል።

ብቃትን ለመለካት የሚያስችሉ እና መስፈርትን መሠረት ያደረጉ ጥያቄዎችን ለማዘጋጀት የሚያስችል ብሉ ፕሪንት ከዚህ ሳምንት ጀምሮ ለማድረግ እንቅስቃሴ እየተደረገ ነው። ሌላው ከመውጫ ፈተና ጋር ተያይዞ የሚደረግ ነገር ቢኖር ተማሪዎች በራሳቸው ቅድመ ዝግጅት አድርገው ውጤታማ እንዲሆኑ የማድረግ ኃላፊነት ያለ እንደ መሆኑ ሁለቱንም የቤት ሥራ ጎን ለጎን በመሥራት ውጤታማ እንዲሆን ማስቻል ነው። የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ተማሪዎች ይህን ፈተና በተሳካ መልኩ ለማለፍ አቅም የሚያገኙበትን ነገር እንደ ትምህርት ሚኒስቴርም ይሁን በከፍተኛ ተቋማቱም እየተሠራበት ነው።

አቶ ሰኢድ እንደሚሉት፤ ፈተናውን በኦን ላይን ለመስጠት እቅድ ያለ ሲሆን፤ እስከ አሁንም ከሁለት መቶ 50 ሺህ የማያንሱ የተፈታኞች ቁጥር ከግል እና ከመንግሥት ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ተሰብስቧል። ለተማሪዎቹ ፈተናውን በኦን ላይን ለመስጠት የሚያስችል መሠረተ ልማት እና ግብዓት በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ምን ያህል አለ? የሚለውም ዳሰሳ ተሠርቷል፡፡በዚህም በቂ መሠረተ ልማት እና አቅም እንዳለ ተረጋግጧል፡፡

በቅድመ ምረቃ የሚመረቁ ሁሉም ተማሪዎች የመውጫ ፈተናው ይመለከታቸዋል፤በመደበኛ እና መደበኛ ያልሆኑትን ተማሪዎችን ጨምሮ ሁሉም ፈተናውን በዚህ ዓመት ይወስዳሉ ያሉት አቶ ሰኢድ፤ ተማሪዎች ብቁ ናቸው ተብለው እንዲወጡ የሚጠበቅባቸው ሚናም ብቃትን መሠረት ያደረገ ፈተና መሆኑን ታሳቢ በማድረግ ራሳቸውን መፈተሽ አለባቸው፡፡እኔ እንደተመራቂ ተማሪ ምን ዓይነት ብቃት ይጠበቅብኛል? የሚለውን ከፈተሹ በኋላ በቂ ዝግጅት ማድረግ ከተማሪዎች የሚጠበቅ እንደሆነም ያስረዳሉ፡፡ሌላው ደግሞ ከሚማሩበት ከፍተኛ ትምህርት ተቋም ጋር በጋራ በመሆን የቲቶሪያል ትምህርት እንዲሰጣቸው ማድረግ፣ ማንበብ እና በትምህርት ሚኒስቴር የሚሰጠውን የመውጫ ፈተና ከመውሰዳቸው በፊት ተቋማቱ የሞዴል ፈተናዎችን እያዘጋጀላቸው ቢወስዱ መልካም የሚባል እንደሆነ በመጠቆም፤ ሞዴል ፈተናውም እውቀትን፣ ክህሎትን እና አመለካከትም በለየ መልኩ ስለሚዘጋጅ የተማሪዎችን ዝግጅት እና ክፍተታቸው የትኛው እንደሆነ ለመለካት ስለሚያስችል በዚህ መልኩ መዘጋጀት ይጠበቅባቸዋል ሲሉም አቶ ሰኢድ ይገልጻሉ፡፡

በተጨማሪም ተማሪዎቹ ራሳቸውን በስነ ልቦና ማዘጋጀት የሚጠበቅባቸው ሲሆን፤ የመውጫ ፈተናን አክብዶ ከመመልከት ይልቅ እስካሁን ሲማሩ የነበረ እንጂ ሌላ አዲስ ነገር አለመኖሩን በመገንዘብ ፈተናውን መሥራት እንደሚችሉ በራሳቸው ተማምነው ወደ ፈተናው እንዲገቡም የዴስክ ኃላፊው ይመክራሉ፡፡

እንደ አቶ ሰኢድ ገለጻ፣ በአሁኑ ወቅት ምሩቃኑ ፈተናውን እንዳይወድቁ ወይም በብቃት እንዲያልፉ ለማድረግ ትምህርት ሚኒስቴርም ይሁን ከፍተኛ ተቋማት እየሠሩ ይገኛሉ። እንዲሁም የትምህርት ማህበረሰቡ እና ወላጆችም ለዚህ ትልቅ ኃላፊነት አለባቸው። የመጀመሪያው ዙር ትምህርታቸውን ጨርሰው ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት የሚያመጡትን ዝርዝር በማየት ፈተናው እንዲወሰድ ይደረጋል። ፈተናውን በዓመት ሁለት ጊዜ ለመስጠት የታቀደ መሆኑ የጠቆሙት አቶ ሰኢድ፤የኦን ላይን ሲስተሙ እንደታሰበው ሆኖ ከተገኘም በዓመት ከሁለት ጊዜ በላይ ለመፈተን እቅድ እንዳለም ያብራራሉ፡፡



አቶ ሰኢድ መሀመድ

ነገር ግን ይህ ዕድል ሳይሳካ ቢቀር ተማሪዎቹ ፈተናውን በድጋሚ የሚፈተኑበት ዕድል ተመቻችቶላቸዋል። ስለሆነም መቼ ይፈተናሉ? ከተባለም በተፈታኞች ፍላጎት ላይ የተመሰረተ ሲሆን፤ ለፈተናውም ብቁ ነኝ ብለው ሲያምኑ ከመጀመሪያ ዙር ፈተና በኋላ ፈተናውን በድጋሚ መውሰድ ይችላሉ፡፡

በአጠቃላይ የመውጫ ፈተናውን ለመስጠት በቂ የሚባሉ ወራቶች ያሉ በመሆናቸው ከወዲሁ የመውጫ ፈተና ምንድን ነው? ዓላማው ምንድ ነው? እነማናቸው የሚወስዱት? የሚለውን ማወቅ እንደተጠበቀ ሆኖ የመውጫ ፈተናውን የሚወስዱ ተማሪዎች ውጤታማ እንዲሆኑ ሁላችንም የራሳችንን ሚና መወጣት አለብን ያሉት አቶ ሰኢድ፤ ተቋማትም ቢሆኑ ተማሪዎቻቸውን ለመውጫ ፈተና ለማዘጋጀት የቤት ሥራዎቻቸውን በትክክል መውሰድ አለባቸው፡፡ወላጆችም በከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ውስጥ በመደበኛም ይሁን መደበኛ ባልሆኑ መርሀ ግብር የሚማሩ ልጆቻቸውን የመውጫ ፈተናውን በብቃት መወጣት እንደሚችሉ በስነ ልቦና ከማዘጋጀት ጎን ለጎን በትምህርታቸው ውጤታማ እንዲሆኑ ድጋፍ እና ክትትል ማድረግ ይጠበቅባቸዋል።

# ስፖርት




## ዋልያዎቹ የቻን ዝግጅታቸውን ይጀምራሉ

**ብርሃን ፈይሳ**

መስከረም አጋማሽ ላይ የተጀመረው የቤትኪንግ ኢትዮጵያ ፕሪምየር ሊግ 13ኛ ሳምንቱ ላይ የደረሰ ቢሆንም ከዛሬ ጀምሮ ይቋረጣል። ምክንያቱ ደግሞ የኢትዮጵያ ብሄራዊ ቡድን ለአፍሪካ ሃገራት ቻምፒዮንሺፕ (ቻን) ውድድር ዝግጅት የሚጀምርበት ወቅት በመሆኑ ነው። ቡድኑ ከነገ ጀምሮ የሚሰባሰብ ሲሆን፤ ጥሪ ከተደረገላቸው ተጫዋቾች መካከልም ከቡድኑ ጋር የሚቀጥሉት 28 ተጫዋቾች ተለይተው ታውቀዋል።

አልጄሪያ ዘንድሮ ለ7ኛ ጊዜ የምታዘጋጀው የአፍሪካ ሃገራት ቻምፒዮንሺፕ (ቻን) በመጪው ወር መጀመሪያ ሳምንት አንስቶ ይካሄዳል። በሃገር ውስጥ ሊጎች የሚጫወቱ የእግር ኳስ ተጫዋቾች ብቻ የሚሳተፉበት የቻን ውድድር መቃረብን ተከትሎም ተሳታፊ ሃገራት ብሄራዊ ቡድኖቻቸውን ማዘጋጀት ጀምረዋል። ከእነዚህ ሃገራት መካከል አንዷ የሆነችው ኢትዮጵያም ከነገ ጀምሮ ወደ ዝግጅት የምትገባ ይሆናል። ለዝግጅቱም ሲባል በድሬዳዋ እየተካሄደ የሚገኘው የቤትኪንግ ኢትዮጵያ ፕሪምየር ሊግ ከዛሬ ጀምሮ የሚቋረጥ መሆኑን የኢትዮጵያ እግር ኳስ ፌዴሬሽን አስቀድሞ ማሳወቁ ይታወሳል። ከነገ ጀምሮ ባለው ቀንም ለቡድኑ ጥሪ የተደረገላቸው ተጫዋቾች ወደ ዝግጅት የሚገቡ ይሆናል።

ኢትዮጵያን የሚወክለው ብሄራዊ ቡድን የመጀመሪያ ዙር ጥሪ የተደረገለት ባለፈው ህዳር ወር 2015ዓ.ም ሲሆን፤ የዋልያዎቹ ዋና አሰልጣኝ ውበቱ አባተ የ42 ተጫዋቾችን ዝርዝር ማስታወቃቸው የሚታወስ ነው። ይህም የሆነው ለውድድር ቅድመ ዝግጅት እንዲረዳ እና ተጫዋቾች በየክለባቸው በውድድር ላይ እያሉ ተገቢውን ክትትል እና ዝግጅት ለማከናወን እንዲያግዛቸው መሆኑንም በወቅቱ አሳውቀው ነበር። በኢትዮጵያ እግር ኳስ ፌዴሬሽን በተያዘው መርሃ ግብር መሰረትም ከነገ ጀምሮ ለቡድኑ ከታጩት ተጫዋቾች መካከል አብረው የሚቀጥሉት የ28ቱ ተጫዋቾች ዝርዝር ይፋ የተደረገ ሲሆን ከነገ ጀምሮ ሪፖርት በማድረግ ዝግጅቱ የሚጀመር ይሆናል።



**ዋልያዎቹ የቻን ዝግጅታቸውን ውጪ አገር ሊያደርጉ እንደሚችሉ ተጠቁሟል፤**

የኢትዮጵያ እግር ኳስ ፌዴሬሽን የኮሚዩኒኬሽን ዳይሬክተር አቶ አብርሃም ገብረማርያም፤ አስቀድሞ ጥሪ የተደረገው ተጫዋቾች በሊግ ተሳትፏቸው አቋማቸውን ጠብቀው ብቃታቸውን እያሳደጉ እንዲቆዩ በሚል መሆኑን ገልፀዋል። የኢትዮጵያ ብሄራዊ ቡድን የአሰልጣኞች ቡድን በድሬዳዋ ሲካሄድ በቆየው ፕሪምየር ሊግ ተገኝተው ተጫዋቾችን ሲመለከቱ መቆየታቸውንም አክለዋል። በግምገማቸው መሰረትም የቡድኑን ቁጥር በመቀነስ ከነገ ታህሳስ 18/2015ዓ.ም ጀምሮ በመሰባሰብ በቀጥታ የቻን ዝግጅታቸውን የሚጀምሩ ይሆናል። ፌዴሬሽኑም ለዝግጅቱ አስፈላጊ የሆነውን ድጋፍ በማድረግ ላይ እንደሚገኝ ጠቁመዋል።

ዝግጅቱም ከኢትዮጵያ ባሻገር ከአልጄሪያ የአየር ሁኔታ ጋር ለመጣጣም እንዲያስችል ከሃገር ውጪ ለማድረግ መታሰቡን ዳይሬክተሩ አመልክተዋል። ለጊዜው ሞሮኮን ጨምሮ በሌሎች ሃገራት ዝግጅት ለማድረግ እንቅስቃሴ በመደረግ ላይ ቢሆንም የተረጋገጠ ነገር የለም።

ፌዴሬሽኑ ከአስተዳደራዊ ድጋፍ ጎን ለጎን ለቡድኑ ቅድመ ዝግጅት እና ከውድድሩ ጋር ተያያዥ ለሆኑ ወጪዎች ከፍተኛ የፋይናንስ አቅም የሚያስፈልግ በመሆኑ የኢፌዴሪ መንግስት የ50 ሚሊዮን ብር የገንዘብ ድጋፍ እንዲያደርግለት ጠይቆ በመጠባበቅ ላይ እንደሚገኝ ይታወቃል። ይኸውም ለሁለት ሳምንት ለሚደረገው ዝግጅት የሚውል ወጪ፣ ለጉዞ፣ በአልጄሪያ በሚኖረው ቆይታ ለሚኖሩ ወጪዎች እና ሌሎችም እንዲውል ገንዘቡ እንደተጠየቀ ዳይሬክተሩ አስረድተዋል። ቡድኑ በአፍሪካ ዋንጫ ተሳትፎ ባደረገበት ወቅት ከ35 ሚሊየን ብር በላይ ከመንግስት ድጋፍ መጠየቁን ያስታወሱት የኮሚኒኬሽን ዳይሬክተሩ፤ መሰል የዓለም አቀፍ ውድድሮች ተሳትፎ ሲኖር ድጋፍ መጠየቅ የተለመደ መሆኑን ተናግረዋል። በመሆኑም መንግስትም እንደ ከዚህ ቀደሙ ድጋፍ ያደርጋል በሚል ፌዴሬሽኑ እየጠበቀ ይገኛል።

የአፍሪካ እግር ኳስ ኮንፌዴሬሽን (ካፍ) ከሚመራቸው ውድድሮች መካከል አንዱ የሆነው ቻን፤ ዘንድሮ ለመጀመሪያ ጊዜ የተሳታፊዎችን ቁጥር አሳድጎ በ18 ብሄራዊ ቡድኖች መካከል ይከናወናል። ሃገራቱ በአምስት ምድብ የተከፈሉ ሲሆን፤ ኢትዮጵያ በምድብ አንድ ከአዘጋጇ አልጄሪያ፣ ሊቢያ እና ሞዛምቢክ ጋር ተደልድላለች። በየሁለት ዓመቱ የሚካሄደው ይህ ውድድር በመጪው ጥር 5 -27/2015 ዓ.ም ድረስ የሚከናወን ይሆናል፡፡

ሰሜን አፍሪካዊቷ ሃገር አልጄሪያ ለውድድሩ የሚሆኑ አራት ስታዲየሞችን ያዘጋጀች ሲሆን፤ የመክፈቻው ስነስርዓትም በደቡብ ምስራቅ አቅጣጫ በሚገኘውና ከ40ሺ ደጋፊዎች በላይ የመያዝ አቅም ባለው ባራኪ ስታዲየም እንደሚከናወን ታውቋል። ውድድሮቹ ከሚካሄዱባቸው ስታዲየሞች መካከል አንዱ ሚሉድ ሃደፊ ሲሆን፤ ከ40ሺ ሰው በላይ የመያዝ አቅም አለው። ቻዲድ ሃምላዊ ስታዲየም ከ22 ሺ በላይ ሰዎችን ሲቀበል፤ በሃገሪቷ በግዝፈቱ ሁለተኛ የሆነውና «ግንቦት 19/1956» ተብሎ የሚጠራው ስታዲየም ደግሞ 56 ሰዎችን ያስተናግዳል።


### ለሁለተኛ ጊዜ የወጣ ግልጽ ጨረታ ማስታወቂያ
### የጨረታ ቁጥር 05/2015

በአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት ግብርና ቢሮ የግብ/ ግብ/ገጠር ፋይናንስና አቅርቦት ዳይሬክቶሬት በፕሮጀክቱ በአየር ንብረት ማስተካከል የመሬት አያያዝ ፕሮግራም (CALM-P4R) በጀት ድጋፍ የተፋሰስ ልማት ሥራዎች በሚከናወንባቸው አካባቢ አገልግሎት የሚውል 3ኛ አካፋ 4ኛዶማ በግልጽ ጨረታ አወዳድሮ ለመግዛት ይፈልጋል፡፡

**ስለዚህ የሚከተሉትን መስፈርቶች የሚያሟሉ ተጫራቾች መወዳደር የሚችሉ መሆኑን ያሳውቃል።**

1. በዘርፉ እና ዘመኑ የታደሰ ህጋዊ የንግድ ፈቃድ ማቅረብ የሚችሉ፣
2. የግብር ከፋይ መለያ ቁጥር (TIN) ማቅረብ የሚችሉ፣
3. የግዥ መጠኑ ከብር 200,000.00(ሁለት መቶ ሺህ ብር)እና ከዚያ በላይ ከሆኑ የተጨማሪ ዕሴት ታክስ/ቫት ከፋይነት የተመዘገቡ መሆናቸውን የሚያረጋግጥ የምስክር ወረቀት ማቅረብ የሚችሉ።
4. ናሙና ማቅረብ የሚችሉ።
5. ተጫራቾች በጨረታ ለመሳተፍ ከላይ በተ.ቁ 1-4 የተጠቀሱትንና የሚመለከታቸውን ማስረጃዎች ከመጫረቻ ሰነዶቻቸው ጋር አያይዘው ማቅረብ አለባቸው።
6.ተጫራቾች የጨረታ ማስከበሪያ ዋስትና ለሎት ሁለት ብር 100,000.00 እና ጨረታውን ካሸነፈ በኋላ ለውል ማስከበረያ ያሸነፈበትን ጠቅላላ ዋጋ 25% በሁኔታ ላይ ያልተመሠረተ የባንክ ዋስትና፣ በማይሻር ሌተር ኦፍ ክሬዲት የቀረበ ዋስትና ጥሬ ገንዘብ ወይም የተረጋገጠ ቼክ ወይም የክፍያ ትዕዛዝ ለስድስት ወር ማስያዝ የሚችሉ።
7. ማንኛውም ተጫራች የጨረታ ሀሳቡን ቴክኒካል ዶክመንትና የዋጋ ማቅረቢያ (ፋይናሽያል ዶክመንት) ዋና እና ቅጅ በማለተ በተለያየ ፖስታ አሽጓ በግብርና ቢሮ የ ግብርና ግብአት ገጠር ፋይናንስ አቅርቦት ዳይሬክቶሬት ቢሮ ቁጥር 18 በተዘጋጀው የጨረታ ሳጥን ዘወትር በሥራ ሰዓት ማስታወቂያው በጋዜጣ ከወጣበት ቀን ጀምሮ እስከ 16ኛው ቀን 4.00 ሰዓት ድረስ ማቅረበ ይኖርበታል።
8 በጨረታው ለመሣተፍ የሚፈልጉ ተጫራቾች የጨረታ ሰነዱን የማይመለስ ብር 100.00/አንድ መቶ ብር/ በመክፈል አብክመ ግብርና ቢሮ ማግኘት ይችላሉ ።
9. ጨረታው ተጫራቾች ወይም ህጋዊ ወኪሎቻቸው በተገኙበት በግብርና ቢሮ የግብርና ግብአት ገጠር ፋይናንስ አቅርቦት ዳይሬክቶሬት ቢሮ ቁጥር 018 በ16ኛው ቀን 2015 ዓ.ም 4:30 ሠዓት ይከፈታል።
10. ቢሮው የተሻለ አማራጭ ካገኘ ጨረታውን በከፊልም ሆነ ሙሉ በሙሉ የመሰረዝ መብቱ የተጠበቀ ነው።
11.በጨረታው ለመሳተፍ የሚፈልጉ ስለ ጨረታው ዝርዝር መረጃ ከፈለጉ ቢሮ ቁጥር 18 ድረስ በአካል ወይም በፋክስ ቁጥር 0582208771 በመላክ በስልክ ቁጥር 0582205849/7048 በመደወል ማግኘት ይችላሉ፤
12. በማስታወቂያ ያልተገለፁ ነገሮች ቢኖሩም በግዥ መመሪያው መሰረት ተፈፃሚ ይሆናል።
13.የጨረታውን ማስታወቂያ በቢሮው ድረ-ገጽ Web site Address / WWW.amhboard gov .et መከታተል ይቻላል።

**የአማራ ብሔራዊ ክልላዊ መንግስት**
**ግብርና ቢሮ**
**ባህር ዳር**



### ግልፅ የጨረታ ማስታወቂያ

በአማራ ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት በምስራቅ ጎጃም ዞን በሸበል በረንታ ወረዳ የየዕድውኃ ከተማ ውሃና ፍሳሽ አገልግሎት ጽ/ቤት በ2015ዓ.ም በጀት ዓመት ለጽ/ቤቱ አገልግሎት የሠጡ ከእነጠጅ እስከ የዕድውኃ የተዘረጋ 3" ኢንች የብረት ቧንቧ በግልጽ ጨረታ አወዳድሮ መሸጥ ይፈልጋል።

**ስለዚህ መወዳደር የሚችል ህጋዊ ፈቃድ ያለው/ሳት/ መወዳደር የሚችል ሲሆን**

1. የዘመኑን ግብር የከፈለ።
2 የታደሰ ፈቃድና ቲን ያለው።
3. በአሮጌ ዕቃዎች ሽያጭና ግዥ ፍቃድ ማቅረብ የሚችል ።
4. ተጫራቾች በጨረታው ለመሳተፍ የሚመለከታቸውን ማስረጃዎች ፎቶ ኮፒ ከመጫረቻው ሰነዶቻቸው ጋር አያይዘው ማቅረብ ያለባቸው ሲሆን የድርጅቱን ሙሉ አድራሻ እና ማህተም መያዝ ይኖርበታል፡
5. የብረት ቱቦዎችን እራሱ ቆፍሮ አውጥቶ መውሰድ የሚችል።
6. ተጫራቾች የጫረታ ሰነዱን 100/አንድ መቶ ብር በመክፈል ገ/ግ/ፋ/ን/ስ/የስራ ሃደት ቢሮ ቁጥር 5 መግዛት ይቻላል።
7 ተጫራቾች የጨረታ ማስከበሪያ ዋስትና /ቢድቦንድ/ ለሚወዳደሩበት ብር ወይም የዕቃውን ጠቅላላ ዋጋ 10% በባንክ በተረጋገጠ የክፍያ ትዕዛዝ ወይም ሲፒኦ ወይም በጥሬ ገንዘብ ማስያዝ አለባቸው።
8. ተጫራቾች የሞሉበትን የጨረታ ሰነድ በፖስታ በማሸግ የዕድውኃ ከተማ ውሃና ፍሳሽ አገልግሎት ጽ/ቤት ገቢ/ግዥ/ፋይ/ንብ/አስ/ደ/የስራ ት ቢሮ ቁጥር5 በተዘጋጀው የጨረታ ሳጥን ማስገባት ይቻላል።
9 ጨረታው በአዲስ ዘመን ጋዜጣ ከወጣበት ቀን ጀምሮ ለ15 ተከታታይ ቀናት እስከ ቀኑ 11 ሰዓት ቆይቶ በ16ኛው ቀን ከጠዋቱ 3:00 ተጫራቾች ወይም ህጋዊ ወኪሎቻቸው በተገኙበት ይከፈታል፡፡
16ኛው ቀን ቅዳሜ እና እሁድ ወይም ሌላ በአል ከሆነ በሚቀጥለው የስራ ቀን በተመሳሳይ ሰዓት ይከፈታል። ጨረታው በሚከፈትከት ቀን ተጫራቾች ወይም ህጋዊ ወኪሎቻቸው ባይገኙም ጨረታው የሚከፈት ሲሆን ሁሉም ተጫራቾች በዕለቱ ለተላለፈው ውሳኔ ተገዢ ይሆናሉ።
10. ጽ/ቤቱ የተሻለ አማራጭ ካገኘ ጨረታውን በከፊልም ሆነ ሙሉ በሙሉ የመሰረዝ መብቱ የተጠበቀ ነው።
11. ተወዳድሮ ያሸነፈ ተጫራች አዝመራ እስኪነሳ ድረስ ውል መያዝና በ15 ቀን ውስጥ 75% የጠቅላላ ክፍያውን መክፈል አለበት።
12. ለበለጠ መረጃ በስ.ቁ 0582470222እና 058-247-02-00 ደውሎ መጠየቅ ይቻላል፡፡

**የየዕድውኃ ከተማ ውሃ ና ፍሳሽ አገ/ጽ/ቤት**